34383.doc

34421.doc

34428.doc

34788.doc

34945.doc

34988.doc

35003.doc

35051.doc

35095.doc

35207.doc

35651.doc

35695.doc

35791.doc

35962.doc

36280.doc

36496.doc

36505.doc

36575.doc

36740.doc

36886.doc

36887.doc

37015.doc

37186.doc

37231.doc

37375.doc

37639.doc

37665.doc

37879.doc

39789.doc

39905.doc

40638.doc

29363.doc

31906.doc

32865.doc

33200.doc

33368.doc

33369.doc

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 34383

ኅዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አለማው ወሌ

አመልካች፡- በሐይሉ መንገሻ - ጠበቃ በሃይሉ ፀጋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፈትለወርቅ ጥላሁን - በሌለችበት

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በውርስ ንብረት ይገባኛል ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የተጀመረውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብ/ክ/መ/ በሰሜን ሸዋ ዞን (መስተዳድር) በማማ ምድር በወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተችው ከሟች አክስቱ በውርስ ያገኘሁትን ቤት ከአግባብ ውጪ ይዞ ስለሚገኝ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ቤቱን ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታዬ ስር አድርጌ የምጠቀምበት ንብረቴ ነው፡፡ ያፈጀውን ቆርቆሮ በመለወጥና በማደስ፣የተናደውን ግንብ እንደገና በመገንባት የራሴ ንብረት በማድረግ ከሰላሣ(30) ዓመት በላይ የያዝኩት ነው፡፡ ክሱም በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ የሚሉትን ነጥቦች በማንሳት የተከራከረ ሲሆን፤ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፤ከአመልካች የቀረበውን የይርጋም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክር ውድቅ በማድረግ ቤቱ ለተጠሪ እንዲሰጥ ወስኖአል፡፡ ውሳኔውን በመቃወም በየደረጃው ይግባኝ የቀረበላቸው የሰሜን ሸዋ ዞን

ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለውም በሚል ይግባኙን ውድቅ አድርገዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ታሕሣስ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ባለመቅረብዋ በዚህ ሰበር ችሎት ያሰማችው (ያቀረበችው) ክርክር የለም፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አቤቱታ የቀረበበት ወሳኔ አመልካች ካቀረበው የይርጋ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አንፃር ሲታይ ያለውን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሰኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የወረዳ ፍ/ቤት ከሰጠው ብይን(ውሳኔ) ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪው ቤት ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ክስ እስከ መሰረተችበት 1998 ዓ.ም ድረስ በአመልካቹ ይዞታ ስር እንደሚገኝ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ አውራሼ ናቸው የምትላቸው ሴት (ወይዘሮ ወርቅነሽ ማንያዘዋል) የሞቱት በ1966 ዓ.ም እንደሆነ፣ተጠሪ የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣት ለፍ/ቤት ጥያቄ ያቀረበችና በዚህም መሰረትም የምስክር ወረቀት ያገኘችው በ1997 ዓ.ም መሆኑም በውሳኔው ላይ ተመልክቶአል፡፡ ይህም ማለት ተጠሪ ወራሽነቷንትዋ እንኳን ያረጋገጠችው አክስቱ እና አውራሼ የምትላቸው ከሞቱ ከ31 ዓመት በኋላ ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ሁሉ ዓመታት ቆይቶ የቀረበው የቤት ይገባኛል ጥያቄ (ክስ) በይርጋ ቀሪ አይሆንም የሚባልበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለው ነጥብ በቅድሚያ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

ከክርክሩ እንደተመለከትነው አመልካች የወ/ሮ ወርቅነሽ ማንያዘዋል ወራሽ አይደለም፡፡ ወራሽነኝ በማለት ለስር ፍ/ቤቶች አቅርቦት የነበረው ክርክር ከግራ ቀኝ ወገኖች ከቀረበው ማስረጃ እንጻር ታይቶ እና ተመዝኖ ውድቅ ሆኖአል፡፡ በመሆኑም

የተያዘው ጉዳይ በወራሾች መካከል የሚካሄድን ክርክር የሚመለከት አይደለም፡፡ በመራሾች መካከል የሚካሄድ ክርክር አይደለም ከተባለ ደግሞ የይርጋው መቃወሚያ ሊታይ የሚገባው "ስለውርስ (ስለአወራረስ)" በተመለከተ በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ አምስት ስር በሚገኘው ቁ. 1000 መሰረት አይደለም፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ በሌላው ክፍል ከሚገኘው አግባብነት ካለው ድንጋጌ አንጻር ሊታይ ስለሚገባም አግባብነት ያለው ድንጋጌ ለይቶ ማውጣት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 1677/1/ እንደተመለከተው ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም "ስለግዴታዎች" በተመለከተ በተደነገገው በፍትሐብሔር ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ በአንቀጽ 12 ስር ያሉ ደንቦች ይፈጸመባቸዋል፡፡ በእርግጥ ከግዴታው (ግዴታዎች) አይነት አንፃር ታይቶ የተለያ ደንብ ባለ ጊዜ በንኡስ ቁ./1/ የተቀመጠው ድንጋጌ ተፈጻሚ እንደማይሆን በንኡስ ቁ./2/ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው በዚህ መሰል ክርክር የተነሳውን የይርጋ መቃወሚያ ለመወሰን በተለይ አግባብነት የሚኖረው ደንብ የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ 12 ስር የሚገኘውን የይርጋ ደንብ ቁ. 1845 "ን" መጠቀሙ የግድ ይሆናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አመልካች አከራካሪውን ቤት በእጁ ይዞ ከ30 ዓመታት በላይ ሲጠቀምበት ቆይቶአል፡፡ ቤቱን የራሱ አድርጉ በማሰብም ጥገና ሲያካሂድለት እንደቆየ በክርክር አመልክቶአል፡፡ የይርጋ መቃወሚያ ያቀረበውም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት መቃመሚያውን ውድቅ ያደረገው ክሱ መቅረብ ከነበረበት የጊዜ ወሰን/ገደብ/አንፃር በማየት ሳይሆን፣ አመልካች ቤቱን የያዘው ወይም ሲጠቀምበት የቆየው በሌለው መብት ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡ በበኩላችን እንደምናየው ግን ይህን መሰል ምክንያት በሕጉ ያለ ወይም ታሳቢ የተደረገ አይደለም፡፡ የይርጋ ሕግ ግዴታ ይፈጸመልን የሚል ወገን ክሱን ማቅረብ ያለበት በሕጉ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማሳወቅ የሚደነገግ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ማለትም ከጊዜ ወሰን ያለፈ ሌላ

መስፈርት አይቀመጥለትም፡፡ በሕጉ የተቀመጠው የክስ(ጥያቄ) ማቅረቢያ የግዜ ወሰን ካለፈ ግዴታ እንዲፈጽም የተጠየቀው ወገን በመከላከያ ሊያቀርበው የሚችልና ከግዴታውም ነፃ የሚሆንበት ሕግ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የይርጋውን ሕግ በመከላከያነት አቅርቦታል፡፡ በፍሬ ነገር ረገድም አከራካሪው ቤት በፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 1845 ከተቀመጠው የጊዜው ወሰን (10 ዓመት) በላይ ለሆነ ከ30 ዓመታት በላይ በይዞታው ስር አድርጐ ሲጠቀምበት እንደቆየ አስረድቶአል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከ30 አመታት በላይ ቆይቶ የቀረበው የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ የማይሆንበት የሕግ ምክንያት የለም ማለት ነው፡፡ ስናጠቃልለው የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን የየርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረጉት በግልጽ የተቀመጠውን ሕግ በመተላለፍ በመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአማራ ብ/ክ/መ/በሰሜን ሸዋ ዞን የማማ ምድር ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 93/98 ግንቦት 25 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11164 የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5525 ሕዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበችው የቤት ይገባኛል ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 34421

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሠላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት - መንገሻ መኩሪያ ቀፈባ/ነ.ፈ.ጅ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ አህል ንግድ ድርጅት ሣምሶን ግርማ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብ/ክ/መንግሥት የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ አመልካች ከ10,000 ኩንታል በላይ ማከማቸት አቅም ያለው መጋዘንና ሦስት ቢሮዎች ያሉት ከ1971 ጀምሮ እየተገለገለበት ከቆየ በኋላ ከ1984 ጀምሮ እንዲያስረክብ ቢጠየቅ አላስረከበም፡፡

ስለዚህ ከ1984 ጀምሮ በየወሩ 1000 ብርx125= ወሮች 125,000 ብር እንድከፍል መጋዘኑንም እንዲያስረክብ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ መጋዘኑ የተጠሪ እንዳልሆነ እና በውል ያልተረከበ መሆኑን በመግለጽ መጋዘኑን ከ10 ዓመት በላይ መያዙን በመጠቀስ በፍ/ሕጉ/ቁ. 2024 መሠረት በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ልጠይቅ ይገባል ሲል ተከራክረዋል፡፡ በተጨማሪም ተጠሪ ጋር የኪራይ ውል የለንም የቀረበው ደብዳቤም

ቢሆን ክራዩ ይህን ያህል ያወጣል የሚል እንጂ የውል ስምምነት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የቤት ኪራይ ገንዘብ ጥያቄ በተመለከተ በውል ላይ የተመሠረተ ጥያቄ ነው? ወይስ አይደለም? ከሚለው መሠረታዊ የውል ሕግ መርህ ጋር ተያይዞ መታየት ይኖርበታል፡፡

አንድ ውል ሕጋዊ ውል ነው የሚባለው ውል ሰጭው ያቀረበውን የውል ስምምነት ውል ተቀባዩ ተቀብሎ አስገዳጅነት በሚኖረው የግዴታ ውል ውስጥ ገብተው ከሆነ ነው፡፡ ተጠሪ በየወሩ የቤቱ ክራይ በየወሩ ይህን ያህል ነው ብሎ ለአመልካች ማሣወቁ ብቻውን ውል አለ ለማለት አያስችልም፡፡ ስለዚህ የተጠሪ የኪራይ ገንዘብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ መጋዘኑን አስመልክቶ የተጠሪ ንብረት መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች ለተጠሪ መጋዘኑን እንዳያስረክብ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት ቅሬታቸውን ለጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያለተጠሪ ፍቃድ በመጋዘኑ መጠቀሙ ተረጋግጧል ይሁን እንጂ የሥር ፍ/ቤት ውል በግራ ቀኙ መሀል የለም በሚል ብቻ አመልካች አለ አግባብ መበልፀጉ እየታወቀ ማለፉ አግባብ አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካችን ክፍያ መክፈል አይገባም ሲል በነፃ ያሰናበተው ውሣኔ ተሸሯል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያለአግባብ የበለፀገበትን ከመስከረም 1/1988 እስከ ሰኔ 18/1996 የ105 ወር ተኩል በወር 1000 ብር 105,500 /አንድ መቶ አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው አመልካች በ25/3/2000 ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ በጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የኪራይ ውል የለም ተብሎ የስር ፍ/ቤት አመልካች በተጠሪ ንብረት ያለአግባብ በልጽገሃል በማለት አመልካች ይክፈል መባሉንና የፍ/ሕ/ቁ. 2024 አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም ጉዳዩን እንዳየነው አመልካች የተጠሪን መጋዘን ይዞት ሲጠቀምበት እንደነበር ይታወቃል የሥር ፍ/ቤቶች እንዳተቱት በግራ ቀኙ መሀከል የክራይ ውል ስምምነት እንደሌለ የሰበር ችሎትም የምስማማት ውሣኔ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተከራካሪዎች መሀከል ውል ባይኖርም አመልካች በተጠሪ መጋዘን ሲጠቀም መቆየቱን አልካደም፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪን መጋዘኑን አስረክበኝ ብሎት ከጠየቀው ቀን ወደኋላ ያለውን ያለ ፍቃድ እየተጠቀመበት ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

አመልካች ያለ አግባብ መበልፀጉን እንረዳለን አመልካች እንደሚለው መጋዘኑን ከ"10" ዓመት በላይ ይኸዋለሁ፣በ2024 መሠረት በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደተከፈለ ይቆጠራል ብሎ ቢከራከርም በዚህ ጉዳይ አለ አግባብ መበልፀግን አስመልክቶ በልዩ ሕጉ የ'2' ዓመት የይርጋ ዘመን ተደንግጎ ስለሚገኝ ወደ ጠቅላላ ሕጉ የይርጋ ዘመን የምንሄድበት ምክንያት የለም በ2024 መሠረት እንደተከፈለ የሚቆጠረው /የሚገመተው/ በግራ ቀኙ የክራይ ውል ቢኖር ነበር ስለሆነም የአመልካች ክርክር በሥር ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡ ወደ ዋና ፍሬ ነገር ስንመለስ ከወል ወጭ ኃላፊነትና ያለ

አግባብ መበለፀግ ተያያዥነት ያላቸው ነጥብ ስለሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2143 መሠረት መታየት የግድ ይላል፡፡

በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ አመልካች መጋዘኑን ያስረክብ በሚለው ነጥብ በመስማማት ነገር ግን ያለ ምንም ክፍያ እንዲሰናበት መወሰኑን አግባብ አይደለም በማለት አመልካች ያለ አግባብ ለበለፀገበት ከመስከረም 1/1988 እስከ ሰኔ 18 ቀን 1996 ያለውን ኪራይ 105,500 ብር /አንድ መቶ አምስት ሺ አምስት መቶ ብር/ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር ችሎትም በጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል አመልካች ሊከፍለው የሚገባው የፍ/ሕ/ቁ. 2143 መሠረት አመልካች በይርጋ የታገደውን ገንዘብ ብቻ ከህዳር 24 ቀን 1993 እስከ 1996 መዘገቡ ውሣኔ እስካገኘበት ድረስ መክፈል አለበት ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 176/96 ህዳር 6 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎዋል፡፡
2. አመልካች በአግባቡ መሠረት ከህዳር 24-93 እስከ 1996 ያለውን የመጋዘን የገንዘብ ክፍያ ይፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ኪሣራና ወጪ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 34428

ኅዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
አልማው ወሌ
ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ዑስማን ዒሳ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ከበደ ንዳው ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ልረከብ ጥያቄን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ክስ የመሠረተው በአሁኑ አመልካች እና በወረዳ 5 ቀበሌ 01 ላይ ሲሆን፣ ክሱም በቁጥር 543 የሚታወቀው ቤት ለሥራና ከተማ ልማት አጣሪ ቡድን አመልክቼ በማማረጫ ቅጽ ተሞልቶ ቤቱ እንዲለቀቅልኝ ተፈቅዶልኛል፡፡ ስለዚህ ቤቱን ተከራይ እና አከራይ በመሆን ይዘው የሚገኙ ተከሣሾች እንዲያስረክቡኝ ኪራዩንም እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ተከሣሾችም ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል፡፡ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ስልጣን የለውም፡፡ ቤቱ በመንግሥት ተወርሶሏል፡፡ ከሣሽ ባለቤት ለመሆኑ የሚያስረዳ የቤት ባለቤትነት ደብተር የለውም በሚሉት ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም በአንድ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የይርጋ እና የዳኝነት ስልጣን ክርክሮች ውድቅ ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከሣሽ ሞላሁት የሚሉት ቅጽ 004 የቤት ማማረጫ እንጂ የተወረሰ ቤት መመለሻ አይደለም

የሚል ምክንያት በመስጠት ቤቱ ለከሣሽ ሊለቀቅ አይገባም በማለት ወስኖአል። ከዚህ በኋላ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል። በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር ቤቱ ተጠሪ እንዲረከበው ወስኖአል። የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም በተመሣሣይ ሁኔታ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም ብሎአል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው።

በበኩላችንም አመልካች ታህሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ለተጠሪ እንዲመለስ በማለት የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው። በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

እንደምንመለከተው ግራ ቀኝ ወገኖችን እያከራከረ ያለው ጉዳይ የቤት ባለቤትነት መብትን መነሻ አድርጎ የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው። ክሱ የቀረበው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ለተቋቋመው ፍ/ቤት ነው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአስተዳደርነቱ የራሱ የሆኑ ፍ/ቤቶች አሉት። እንዚሁ ፍ/ቤቶች በሕግ የተቋቋሙ እንደመሆናቸው የሚኖራቸው የዳኝነት ስልጣንም እንደዚሁ በሕግ ተወስኖአል። በተያዘው ጉዳይ የክርክር መነሻ የሆነው ቤት በከተማው አስተዳደር ክልል የሚገኝ እንደመሆኑ በጥቅሉ ሲታይ የአስተዳደሩ ፍ/ቤቶች የክልል /የግዛት/ የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል ብሎ መገመት ይቻላል። ማንኛውም ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ ከማስተናገዱ በፊት በቅድሚያ ሊያረጋግጠው የሚገባው ጉዳይ ባቀረበው ክስ ላይ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆንኑን እንደሆነም የሚታወቅ ነው። የዳኝነት ስልጣን ሲባልም ከፍ ሲል የተጠቀሰው የክልል እና የስረ ነገር በሚል በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ነው። ይኸኛው ማለትም የስረ ነገር የዳኝነት

ስልጣን በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም ክሱን ያስተናገደው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በከተማ ቤት ላይ የባለመብትነት መብትን መሠረት አድርጎ በሚቀርበው ክስ ላይ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለው ጭብጥ በቅድሚያ ሊጣራ የሚገባው ነው፡፡

እንደሚታወቀው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ ንብረቶች ወይም መነሻቸው በዚሁ አስተዳደር ክልል በሆኑ እጅግ በርካታ አይነት ጉዳዮች ላይ ሰፊ የዳኝነት ስልጣን ያላቸው የፌ/ፍ/ቤቶች አሉ፡፡ ከዚህ ደግሞ መገንዘብ የሚቻለው በዚህ ረገድ በተለይ የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣንን በሚመለከት ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ የሚያገባ እንደሆነ ነው፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ያላቸው የዳኝነት ስልጣን በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41 በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ በዚህ አንቀጽ ለፍርድ ቤቶቹ የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በንዑስ አንቀጽ 1/ረ/ የተመለከተው የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግሥት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱት ጉዳዮችን የጠቃልላል፡፡ ለተያዘው ጭብጥ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌም ይኸው ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ድንጋጌ መተርጎሙ ተገቢ ይሆናል፡፡

ሕጉ /ድንጋጌው/ በግልጽ እንደሚያመለክተው ለክሱ መነሻ የሆነው ቤት የከተማው አስተዳደር የሚያስተዳድረው ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ብቻ ግን በቂ አይደለም፡፡ ቤቱ የመንግሥት ንብረት መሆን አለበት፡፡ ይህም ማለት ቤቱ የማን ንብረት ነው የሚል ወይም ስለቤቱ ባህብትነት በተመለከተ የሚነሳ ክርክር የለም፡፡ ክርክር ቢነሣ ሊሆን የሚችለው ከባለቤትነት መብት በመለስ ያሉትን ለምሣሌ ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱትን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ በከተማው ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቀውም ይኸው ማለትም በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው ብቻ ነው፡፡ ክሱ የባለሃብትነት ጥያቄ ወይም ክርክር የሚያስነሳ ከሆነ ግን ከፍ/ቤቶቹ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ውጪ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም

በተያዘው ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ክርክሩን የሰሙት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖራቸው ነው ለማለት ችለናል፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከዚህ አንፃር ቢታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መነሻነት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03024 በግንቦት 13 ቀን 99 ዓ.ም. እና በይግባኝ ሰሚው ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 04494 ጎዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. ታይቶ የተሰጡት ውሣኔዎች በሙሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የማይወድቅ በመሆኑ ፍ/ቤቶቹ ወደ ክሱ ስረ ነገር ገብተው ውሣኔ የሚሰጡት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 34788

ኅዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- የሚች አቶ ሰለሞን ሳሙኤል ወራሾች -ቀርቧል

እነ ወ/ሮ ማሪታ ሰለሞን/2/ - ጠበቃ ታደሰ ጉርሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ኑረዲን መሐመድ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወሰኗል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ጣልቃ ገቦች ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡

የአሁን ተጠሪ በሥር ተከሣሾች በነበሩት 1ኛ ንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ 2ኛ የወረዳ 5 አስተዳደር 3ኛ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ላይ ባቀረበው ክስ የድርጅት ቤት የሆቴል ንግድ ሕጋዊ ፈቃድ አውጥቼ የዘመኑን ፈቃዴን እያሳደስኩ ከኪራይ ቤቶች ተከራይቼ በምሰራው ሆቴል ቤት እየሰራሁ እያለሁ የሥር ተከሣሾች ቤቱን ያለአግባብ እንዳልሰራ አሸገውብኛል፡፡ ስለዚህ 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡኝ 3ኛ የሥር ተከሣሽ ከእኔ (ተጠሪ) ጋር የነበረውን ውል ሣያቋርጥ(ሳያፈርስ) ሌላ ውል በመፈፀ ያስገባቸውን ግለሰቦች እንዲያስወጣ ውላቸውንም እንዲሰርዝ፣ የቀረብኝን ጥቅምና የደረሰብኝ ጉዳት የመጠየቅ መብቴ ተጠብቆ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

https://chilot.me

1ኛ እና 2ኛ የሥር ተከሣሾች ለቀረበባቸው ክስ መልስ ሲሰጡ፡- የአሁን ተጠሪ ፍቃዳቸውን ያላደሱ በመሆኑ የጸና የንግድ ፍቃድ የላቸውም ፍቃዳቸው ተሰርዟል፡፡

ከተጠሪ ጋራ ያለን ግንኙነት ስለተቋረጠ የሚጠይቁት ጥቅም ሆነ መብት የላቸውም ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ስመልስ 2ኛ የሥር ተከሣሽ በበኩሉ የተባለውን ቤት በጋራም ሆነ በተናጥል አላሸግኩም ሲል መልሷል 3ኛ የስር ተከሳሽም በተመሣሣይ መልኩ ድርጊቱን እንዳልፈፀመ ክዶ ተከራክሯል፡፡

በዚሁ ጉዳይ የሥር ጣልቃ ገብ የአሁን ተጠሪ ይህን ቤት በሕጋዊ መንገድ ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ተረክበው በውላቸው መሰረት ይዘውት እንዳሉ ገልጸው የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን በመቃወም ተከራክረዋል፡፡

የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከሕግ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የንግድ ፈቃድ ባለማደሳቸው እና በወቅቱ የቤት ኪራይ ክፍያ ባለመፈፀማቸው ምክንያት በክራይ ይዘውት የነበረውን ቤት ሕግና ደንብ በሚያዘው መሰረት መብታቸውን አጥተዋል፡፡ ስለዚህ ይህን ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 33.2 መሰረት የመክሰስ መብት የላቸውም ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪም በተሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አስቀርቦ በማከራከር ካዩ በኋላ የሥር 1ኛ ተከሣሽ የአሁን ተጠሪን የንግድ ድርጅት ያሸገው ያለ አግባብ ነው 3ኛ የሥር ተከሣሽ ከአሁን ተጠሪ ጋር ያደረገው የቤት ክራይ ውል ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ከአሁን አመልካቾች ጋር በውል ላይ ውል በመፈፀም ቤቱን ያስረከባቸው በአግባቡ አይደለም የአሁን ተጠሪ እና የሥር 3ኛ ተከሣሽ የኪራይ ውላቸውን መቀጠል ይገባል በማለት የሥር ውሳኔን በመሻር ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁን አመልካቾች በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለከተማው ሰበር ሰሚ ለሆነው ፍ/ቤት ቅሬታቸውን በማቅረባቸው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በፍ/ቤቱ ውስጥ

https://chilot.me

ጉዳዩን የማየት ስልጣንን አስመልክቶ የሐሳብ ልዩነት በመፈጠሩ በልዩነት ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አብላጫው ድምጽ ምክንያቱን ሳያስቀምጥ “ምንም እንኳን የፌደራል መንግስት አካል የሆነው የኪ.ቤ.አ.ድ በዚህ መክገብ ተከራካሪ ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር የመስተዳድሩ አካላት በነበራቸው የአስፈፃሚነት ስልጣን በመሆኑና እነርሱ የወሰዱትን እርምጃም ተከትሎ የኪ.ቤ.አ.ድ በወሰደው እርምጃ የተከሰሰና ይህም አንድ ድርጊት በመሆኑ ጉዳይ የዚህ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው” በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ስህተት የለም በማለት የሰበር አቤቱታውን ሰርዞታል፡፡

አነስተኛ ድምጽም በጉዳዩ የተለየበትን ሐሳብ ሲያስቀምጥ፡- “በክርክሩ ጭብጥ ውስጥ ይህንን ቤት በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የኪራይ ቤቶች ድርጅት ቤቱን አላግባብ ለሦስተኛ ወገን አከራይቷል የሚል በመሆኑ በአዋጅ 25/88 መሰረት የሚኖርበት በፌደራል ፍርድ ቤት ከመሆኑም በላይ የክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትም በአዋጅ 36/95 አንቀጽ 41/1/ረ ላይ መስተዳድሩ በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ሥር የማይሸፈን በመሆኑ በከተማው ፍ/ቤት መታየቱ ከሥልጣን አካያ አግብብ አይደለም ሲል ልዩነቱን አስፍረዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 1 ቀን 2000 ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በከተማው ይግባኝ ሰሚና በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታቸውን አቅርቧል፡፡

ይህ የፌደራል ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ምክንያት በማድረግ ተጠሪምችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምተዋል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የወሰነው የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ይህን ነጥብ ከተነሳው ክርክር አቤቱታ ከተሰማው ውሳኔ እና ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

https://chilot.me

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክሱን ሲመሰርት የሆቴል ቤቱ ያለአግባት በመስተዳድሩ አካላት እና በቱሪዝም ቢሮ የታሸገበት መሆኑን ብቻ ሳይሆን የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የሆነውን የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ኪራይ እየከፈልኩ የምሰራበትን የሆቴል ቤት ነጥቆኝ ለሦስተኛ ወገን አከራይቶታል በሚል ምክንያት ነው፡፡

እኛም ተሻሽሎ የወጣውን የአዲስ አበባ ከተማ ታቸርተር አዋጅ ቁ. 24/1/ረ ስናይ የከተማው ፍ/ቤት ማየት የሚችለው የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን ነው፡፡ ሕጉ ይህን እያለና ዋና **የቤት** አስተዳደር (ባለቤት) ከተጠሪ ጋራ የውል ግኑኝነት እያላቸው በፌደራሉ ሥልጣን ክስ የሚወድቀውን ክርክር በከተማው ፍ/ቤት መታየቱ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለዚህ በሥር ፍ/ቤት በአበላጫ ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ በአናሳው ደምጽ ጉዳዩ የከተማው ፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም ያለው ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአ.አ.ከተማ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት መ/ቁ. 2633/91 ሐምሌ 22 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02703 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የከተማው ሰበር በመዝገብ ቁ. 05360 በ4/4/2000 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽሮአል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የአ/አ/ከተማ መስተዳድር ፍ/ቤቶች ይህን ክርክር የማየት ስልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪ እና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መቁ 34945

ህዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አብዱልቃድር መሐመድ

2. ሐጎስ ወልዱ

3. ሂሩት መለሰ

4. ተሻገር ገ/ስላሴ

5. ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ፡- ወ/ሮ መስታወት በላቸው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፡- አቶ ለገሠ ሣህሉ ጠ/መከተ ዳኜ ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍሉ ጉዳይ በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ሲታይ ቆይቶ ጉባኤው በ06/21/1998 ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ ይህንኑ ውሣኔ እንዲያጸድቅላቸው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ሲያመለክቱ አመልካች ግን ጉባኤው ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት መሠረታዊ የህግ ግንዛቤ የሌለው በመሆኑ የተሠጠውም ከፊል ውሣኔ ከጉባኤው ስልጣል ውጪ በመሆኑና የህግ ስህተቶችም ስላሉበት ጉዳዩን ፍ/ቤቱ ተረክቦ ውሣኔ ይስጥበት በማለት አስተያየታቸውን ሠጥተዋል፡፡ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ግን የአመልካችን መቃወሚያና ክርክር ወድቅ አድርጎ ውሣኔውን በማጽናት

የጋራ ናቸው ተብለው ውሣኔ የተሠጠባቸው ንብረቶችን ከተስማሙ በአይነት እንዲካፈሉ ካልተቻለ አንደኛው ለሌለኛው ልዩነቱን እንዲከፍል በማድረግ እንዲካፈሉ በዚህ ካልተስማሙ ንብረቶቹ በሐራጅ ተሸጠው ገንዘቡን እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው አመልካች ለተጠሪ ብድር ብር 700.000 ስለከፈልኩ ግማሹን ተጠሪ ይክፈሉ በማለት አቅርበውት የነበረውን የዳኝነት ጥያቄ ጉባአው ሣይቀበል እንዲውም አመልካች ለተጠሪ የዚህን ገንዘብ ግማሽ እንዲከፍሉ በማለት የሠጠውን ውሣኔ ብቻ በመሻር የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ የረር ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር የራሱ የህግ ሠውነት ያለው በስሙ መከሠስና መክሠስ የሚችል ድርጅት መሆኑ እየታወቀ እንዲካፈሉት መወሠኑ ለተጠሪ የግል ዕዳ ከጋራ ገንዘብ የተከፈለ ገንዘብ ለመሆኑ ምስክር ሣይሠማ ጥያቄው ውድቅ መደረጉ እንዲሁም ሌሌች የቤት ቁሣቁሶች በተመለከተ ማስረጃ ሣይሰማ መወሠኑ የህግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎታም የአመልካች አቤቱታ በሠበር ችሎት ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመን ተጠሪ ቀርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ስህተት ተፈጽሞበታል ከተባለው ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

በዚህ መሠረት ራሱን ችሎ የህግ ሠውነት ያለው ድርጅት በቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ እንዲከፋፈል መወሠኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ማስረጃ ሣይሠማ ውሣኔ ተሠጥቶበታል የተባለው የንብረት ክፍፍል አግባብ መሆን አለመሆኑን ችሎቱ መርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የረር ኃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር በንግድ ህጉ መሠረት የተቋቋመ እና የህግ ሠውነት ያለው መሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ የንግድ ማህበሮች የሚቋቋሙበት እና የሚፈርሱበት ሁኔታ ደግሞ በንግድ ህጉ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የተወሠነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ሊፈርስ የሚችልበት ምክንያቶች በንግድ ህግ ቁጥር 542 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ የንግድ ህጉ ድንጋጌ ሥር የተለከቱት ምክንያቶች ሲኖሩ ማህበሩ በፍ/ቤት አማካኝነት ይፈርሣል፡፡ ከዚህ ውጪ የንግድ ማህበሩ አባላት የህጉን ሥርዓት ሣይከተሉ በራሣቸው ወይም በሌላ አካል አማካኝነት ሊፈርስ የሚችልበት የህግ መሠረት የለም፡፡ በፍ/ቤት አማካኝነት ከፈረሠና ሂሣቡ ተጣርቶ የመጨረሻው ውጤት በሂሣብ አጣሪዎች ከታወቀ በኋላ ማህበሩ ከንግድ መዝገብ ተሠርዞ በህግ የተሠጠው መብቱ ቀሪ የሚሆንበትን ሥርዓት የንግድ ህጉ አስቀምጧል ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር የህግ ሠውነት ያለውና በራሱ ስም ህጋዊ ተግባራትን ሊፈፅም የሚችል ሊከስና ሊከሠስ የሚችል በመሆኑ የሠራቸው ህጋዊ ተግባራትም የተለያዩ ውጤቶች የሚያስከትሉ በመሆኑም ህጉ በተለየ ሁኔታ እንዲስተናገዱ አድርጓል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የማህበሩ ብቸኛ የአክስዩን ባለድርሻ ባልና ሚስቱ ቢሆኑ እንኳን እንደሌላ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ማህበሩን በዓይነት የሚካፈሉት ወይም በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን ሊከፋፈሉ የሚችሉበት የህግ መሠረት የለም፡፡ ስለሆነም የሽምግናልና ጉባኤው እንደሌላ ንብረት ማህበሩን እንዲከፍፈሉ የሠጠው ውሣኔ የንግድ ህጉን ያላገናዘበ ነው፡፡

የቀረውን ነጥብ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የመኖሪያና የጀምናዝየም ዕቃዎች ከቤቶቹ ጋር አብረው የተሸጡ መሆኑ በአግባቡ ሣይጣራ ተወስኖብኛል ያሉ ሲሆንም ከሽምግልና ጉባኤው ውሣኔ ቤቶቹ መሸጣቸውን የሚያረጋግጠው የፀሁፍ ማስረጃ ከቤቶቹ ጋር የቤትና የጅምግዝየም ዕቃዎች አብረው መሸጣቸውን የማያመለክት

በመሆኑ በቂ ማስረጃም ያልቀረበበት መሆኑን በማረጋገጥ ውሣኔ መስጠቱን ተመልክተናል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች እነዚህ የቤት እቃዎችና የጅምናዝየም ዕቃዎች ቤቱን የገዙት ግለሠብ ከቤቱ ጋር አብረው የገዟቸው ስለመሆናቸው ቀርበው እንዲመሠክሩላቸው በማስረጃነት የቆጠሯቸው መሆኑን ከሽምግልና ጉባኤ ውሣኔ ላይ ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ንብረቶች የሚንቀሣቀሱ ንብረቶች በመሆናቸው የንብረቶቹ ሽያጭ የግድ በፁሁፍ መደረግ ያለበት መሆኑ ወይም ንብረቶቹ ለመሸጣቸው ሊረጋገጥ የሚገባው በፁሁፍ / በሠነድ ማስረጃ ብቻ ለመሆኑ በህግ ተለይቶ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ በህግ በተለይ ሁኔታ እንዲረጋገጥ ካልተመለከተ በቀር አንድን ጉዳይ በማንኛውም አይነት ማስረጃ ማረጋገጥ እንደሚቻል ከፍ/ህ/ቁ.2002 እና 1677(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አመልካች የቤትና የጅምናዝየም እቃዎቹ ስለመሸጣቸው በሰው ምስክር ለማስረዳት እየጠየቁ ጉባኤው በቤት ሽያጭ ውሉ ላይ እነዚህ ንብረቶች ስለመሸጣቸው አልተገለፀም በማለት ክርክርራቸውን ውድቅ ማድረጉ የአመልካችን የመከላከል መሠረታዊ መብት የማያጣብብ ሆኖ አግኝተዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የረር ሃላፊነቱ የተወሠነ የግል ማህበር እና የቤትና የጅምናዝየም ዕቃዎችን በተመለከተ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሚያዝያ 22/1999 ዓ.ም. በመ/ቁ 55299 የሠጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ህዳር 12/2000 ዓ.ም. በመ/ቁ 55333 የሠጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. የረር ኃ/የተ/የግ/ማ በንግድ ህጉ በተለከተው መሠረት የሚፈርስና ሂሣቡ የሚጣራ ካልሆነ በቀር እንደሌሌቹ የባልና ማስት የጋራ ንብረቶች

ተገቢዎቹ በዓይነት የሚካፈሉት ወይም ተሸጦ ገንዘቡን የሚካፈሉት ንብረት አይደለም ብለናል፡፡

3. የቤትና የጅምናዝየም ዕቃዎችን በተመለከተ አመልካች በማስረጃነት የቆጠሯቸው ምስክር ቀርበው ከተሠሙ በኋላ ተገቢው ውሣኔ እንዲሠጥ ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343 (1) መሠረት ለፊ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡

4. ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 34988

ኀዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ሽፈራው አብርሃ ደገፉ ምሶኔ ጠበቃ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ሸዋዬ ይርጉ ጠበቃ አሰግደው አመነሸዋ

2. አቶ ብሩ ኢትሣ ጠበቃ አበበ ወርቁ

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የስር ተከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሥር ከሣሽ 2ኛ ተጠሪ የሥር ተከሣሽ ነበሩ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በ28/2/65 ጋብቻ የመሰረትን ሲሆን እኔ አሜሪካን ሐገር እያለሁ ሳላውቅና ሳልፈቅድ የጋራ የሆነውን ንብረታችንን 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች በመንደር ውል በሁለት መቶ ሺ ብር ሸጦብኛል፡፡

ስለዚህ በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68 መሰረት ውሉ እንዲሰረዝ፣ ጅምር ቤቱም እንዲመለስልኝ ሲሉ ጠይቋል፡፡

የስር አንደኛ ተከሣሽ እና የአሁን 2ኛ ተጠሪ የሆኑት (የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት) መልሳቸውን ሲሰጡ በውላችን እንቀጽ “6” ላይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ (ባለበቱ) ካልፈቀደች ውሉ የሚፈርስ በመሆኑና እሷም ያልተስማማች በመሆኑ ፍ/ቤቱ ውሉ ተፈፃሚነት

የለውም በማለት ውሣኔ ይስጥ በማለት መልስ ሰጥተዋል የሥር 2ኛ ተከሣሽ እና የአሁን 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ውሉ በይርጋ ይቋረጣል፡፡ ይህ ከታለፈ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ስለ ውሉ የማያውቁ ከሆነ በቃለ መሐላ ስር ሆነው ሊያስረዱ ይገባል፡፡

የጋራ ንብረታቸው ስለመሆኑ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም በማለት መልሳቸውን አቅርቧል፡፡

በዚህ መሰረት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበውን ክስ አግብብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 68/ሀ/ መሰረት የጋራ የሆነው ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ አንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ይህን የሚቃወም ወገን በዚሁ ሕግ አንቀጽ 69/1/ እና /2/ መሰረት ለፍ/ቤት የሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው መፍረስ የሚችልና ነገር ግን ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ በማንኛውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ በሁለት አመት በኋላ ሊቀርብ እንደማይችል ይገልፃል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ውል የተደረገው በግንቦት 17 ቀን 1991 ዓ.ም ሲሆን ክስ የቀረበው በግንቦት 12 ቀን 1996 ዓ.ም ከሁለት አመት በኋላ ስለሆነ በላይ በተገለጸው ሕግ አግባብ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡

አንደኛ ተጠሪም በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት ለከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን አቀረቡ፡፡

ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የሥር ፍ/ቤት መልስ ሰጭዎች የፈጸሙት ውል ሕጋዊ ሽያጭ ውል ነውን? የሚለውንና ውሉ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ይግባኝ ባይ በውሉ አልፈርምም ብሎ ይግባኝ ባይን ውሉ ያስገድዳል ወይ? የሚለውን ነጥብ አከራክረህ ውሣኔ ስጥበት ብሎ መዝገቡን መልሷል፡፡

የአሁን አመልካችም በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛው ችሎት ይግባኙን አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለትም ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በ348/1/ መሰረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ጥር 5 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ይህ የስበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ተሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የይርጋ ክርክሩ በከፍተኛው ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህን ነጠብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር፤አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ ስናዬው የስር ከሣሽ ወ/ሮ ሸዋዬ ይርጉ በአሜሪካን ሐገር እያሉ ባቤታቻው (የአሁን 2ኛ ተጠሪ) የጋራ ንብረታቸው የሆነውን ጅምር ቤት በግቦት 17 ቀን 1991 ዓ.ም በተደረገ ውል ለአመልካች በመሸጣቸው ምክንያት እኔ ሳላውቅና ሳልፈቅድ የተሸጠ ስለሆነ ውሉ ይፍረስ በማለት 1996 በፍ/ቤት ጥያቄ በማቅረባቸው ነው፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሥር ተከሣሽ በኩል የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ ክስ በይርጋ ተቋርጧል በማለት የሰጠው ብይን በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ “69” አኳያ ስናዬው አግብነት ነበረው፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከ/ፍ/ቤት የይርጋ ክርክሩ ሊስተናገድ የሚችለው በሕግ የሚፀና ውል በግራ ቀኙ መካከል ተደርጉ የነበረ ሲሆን ነው ውሉ ግን በሚመለከተው አካል ስላልተመዘገበ

የፀና ስላልሆነ በማይፀና ውል ላይ የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት ስለማይኖረው መሻር አለበት በማለት ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ገብቶ ወደ ታች ተመልሶ ይታይ ማለቱ ጉልህ የሥነ ሥርአት ግድፈት ያለው(የተፈጸመበት) ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ምክንያቱም የመቃወምያ ክርክር ከፍሬ ጉዳይ ክርክር በፊት የሚታይ ሲሆን የውሉ እጋዊነት ደግሞ በፍሬ ጉዳይ ክርክር የሚስተናገድ ስለሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ከመቃወሚያ ክርክር በፊት የውሉን አግባብነት አስመልክቶ ሊመረምር ይገባል ማለቱ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 40474 ጥቅምት 9 ቀን 1999 ዓ.ም እና ፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 27523 ኅዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽሮአል፡፡
2. በፌ/የመጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40210 በግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም የተወሰነው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. የይርጋ መቃወሚያው ታልፎ በፍሬ ነገሩ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ መወሰኑ አግባብነት የለውም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአስምት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 35003

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ አሸናፊ ዓብዱልቃድር ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ሽቶ ኢብራሂም/ 4 ሰዎች/ ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሟች አባታቸው በኑዛዜ ያወረሷቸውን ቤት ተጠሪዎች እንዲያካፈሏቸው ጠይቀዋል 1ኛ ተጠሪ የሟች ሚስት በሕይወት እያሉ የውርስ ንብረት ክፍፍል ሟች በኑዛዜያቸው ስለገለፁ ክፍፍሉ ሊፈፀም አይገባም በማለት ተጠሪዎች መልስ ሰጥተዋል ፍ/ቤቱም የውርስ ንብረት አጣሪ አቋቁሞ የውርሱ ንብረት እንዲጣራ አድርጎ የውርስ ንብረት የሆነው በሻሸመኔ ከተማ ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የሚገኝ ቁጥር 544 የሆነ በ500 ካ.ሜ. ላይ የሠፈረ ቤት መሆኑን ተረጋግጦ ቀርቦለታል፡፡ ከዚህም በኋላ ይኸው ቤት በባለሙያ ተገምቶ ግምቱ ብር 41,078.77 መሆኑ ተገልጿል፡፡ ፍ/ቤቱም 1ኛ ተጠሪ የሟች ሚስት በመሆናቸው የቤቱ ግማሽ የሣቸው ድርሻ ነው የግምቱን ግማሽ ግን አመልካችና ቀሪዎቹ ተጠሪዎች ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት በመጀመሪያ ለምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀጥሎም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኛቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል በመጨረሻም አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ለሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ነው የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ አባቱ ቦታ ላይ በራሴ ገንዘብ የሰራሁት ቤት ግምት ውስጥ አልገባልኝም ቤቱ በገበያ ዋጋ አልተገመተም የሚል ነው ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ መኖሩን በማመን ተጠሪዎች ቀርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ከተባለው ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት አመልካችና ቀሪዎቹ ተጠሪዎች ደግሞ የሚች ልጆችና ወራሾች ናቸው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የሚችና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ የቤቱ ግማሽ ለ1ኛ ተጠሪ ይገባል በማለት በሰጠው የውሣኔ ክፍል አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ ባለመኖሩ ውሣኔውን እንደተቀበሉት ይቆጠራል፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች በአባታቸው ቦታ ላይ በራሣቸው ገንዘብ የሠሩት ቤት ከግምት ውስጥ ሣይገባ የክፍፍል ውሣኔ እንደተሠጠ ገልፀዋል፡፡ ይህ ቤት በሚች ስም የተመዘገበና ቤቱ የአመልካች ለመሆኑ ምንም ማስረጃ ያልቀረበ ምስክርም ያለተቆጠረ መሆኑን የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡ በመሆኑም አመልካች ቤቱ በገዛ ገንዘባቸው የሠሩት መሆኑን ማስረዳት ሣይችሉ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው የአመልካች ቅሬታ የውርስ ንብረት በገበያ ዋጋ ሣይገመት በአነስተኛ ግምት ክፍፍሉ መፈፀሙ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ በሌላ አነጋጋገር የውርስ ንብረቱ

በወራሾች መሃከል እኩል አልተከፋፈለም የሚል ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ክስ ያቀረቡት የውርስ ንብረቱን በሚች ኑዛዜ መሠረት ለመካፈል ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹም የቤቱ ግማሽ የ1ኛ ተጠሪ ድርሻ መሆኑንና ቀሪውን የሚች ግማሽ ድርሻ ልጆቹ እኩል እንደካፈሉ በሰጡት ውሣኔ በግራ ቀኙ የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ ሚች ንብረቱን በዚሁ መሠረት እንዲካፈሉ የተናዘዙ መሆኑን ችሎቱ ግንዛቤ ወስዷል፡፡ ንብረቱን በዚሁ መሠረት ለመካፈልም የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የስር ፍ/ቤት የንብረቱ ዋጋ በመሐንደሶች የቀረበው ግምት ነው በማለት በዚሁ መሠረት ክፈፍሉን መወሰኑን ተረድተናል፡፡ የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ ነው ማለት የሚቻለው ግን ቤቱን ለመስራት የወጣው ወጪ /book value/ ብቻ ሣይሆን ይለቁንም ቤቱ በወቅቱ ለገበያ በቀረበ ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ /market value/ ነው በሥር ፍ/ቤት እንደተደረገው ቤቱ የተሠራበት ዋጋ ብቻ በባለሙያ ተገምቶ በቀረበው ግምት መሠረት ገንዘቡን መከፋፈሉ ንብረቱን የሚያስቀረው ወገን የበለጠ ጥቅም እንዲያገኝና በሌላው ወገን ላይ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ የእኩልነት መርህን የሚንድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የውርስ ንብረት ክፍፍሉ መፈፀም ያለበት በንብረት የገበያ ዋጋ መሠረት ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ንብረቱ ለመስራት የወጣውን ወጪ መሠረት በማድረግ ክፍፍሉን መወሰናቸው የእኩልነት መርህን የሚጥስ ሆኖ አግኝትነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት የመ/ቁ. ባልተጠቀሰ በ24/6/98 የሰጠው ውሣኔ የምዕ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09775 በ28/07/98 እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40405 በ4/9/98 የሰጡት ትእዛዞች እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 41006 በ07/04/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽሽሏል፡፡

2. **የውርሱ ንብረት በገበያ ዋጋ ተገምቶ በሚቀርበው ግምት መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈፀም በፍ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ጉዳዩ ለሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡**
3. **ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 35051

4/3/2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ኮ/ል አንተነህ አባተ --- ኮ/ር በትረ ጎርፉ

ተጠሪ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ - ዐ/ሕግ አውግቸው መኮንን

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ በሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ተሻሽሎ የወጣውን የወንጀል ሕግ ቁጥር 540 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ ጎዳር 10 ቀን 1999 ዓ.ም ከለሊቱ በግምት 6፡30 ሲሆን በጎንደር ከተማ ቀበሌ 02 እና 13 መገናኛ በተለምዶ ብልኮ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ የቡድን ጠብ ተነስቶ ጠቡን ያነስቱን ወደ ሕግ ቦታ ለመውሰድ በተፈጠረ አለመግባበት ተከሣሽ ለሥራ ታጥቆት በነበረው መሣሪያ አንድ ጥይት በመተኮስ ሟች ሲሣይ ገ/ሕይወት የተባለውን ግራ ሽንጡን መትቶ በመግደሉ በፈፀመው ተራ የሰው መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሣሽ ቀርቦ ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ 3 የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የሚች አስከሬን ምርመራ ውጤትም በጽሁፍ ማስረጃነት አቅርቧል፡፡

የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የዐቃቤ ሕግን የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ መርምሮ ተከሣሽ መከላከል የሚገባው መሆኑን በማመኑ እንዲከላከል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

ተከሣሹም በበኩሉ 3 የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን በጽሁፍ ማስረጃነትም በወቅቱ ጥይት የተተኮሰው ተከሣሽ ታጥቆት ከነበረው መሣሪያ ሣይሆን ከሌላ መሣሪያ የተተኮሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከፌዴራል ፖሊስ የተሰጠ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም በተከሣሽ በኩል የቀረበው የመከላከያ ማስረጃ የዐ/ሕግን ማስረጃ የሚያስተባብል አለመሆኑን በዝርዝር በመተቸት ተከሣሽ በተከሰሰበት ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ነው ብሎ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ተከሣሽ በ10 /አሥር/ ዓመት ጽኑ እሥራት ሊቀጣ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በዚሁ ጉዳይ በሌላ ግለሰብ ላይ የወንጀል ክስ መቅረቡ ተረጋግጦ ባለበት በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በሥር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ በአግባቡ ነውን? የሚለው ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ዐቃቤ ሕግ አቅርቦ ያሰማቸው 3 ምስክሮች በወቅቱ አመልካች ሚችን ጥይት ተኩሶ የመታው ስለመሆኑ እርስ በርሱ በሚደጋገፍ ሁኔታ የምስክርነት ቃል መስጠታቸውን ተገንዝበናል ሚችም በጥይት በመመታቱ ምክንያት ሊሞት እንደቻለም ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው የሐኪም አስከሬን ምርመራ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች በእለቱ የውግ ቁጥር 87331072 የሆነ መሣሪያ ታጥቆ እንደነበረ የጎንደር ከተማ ፖሊስ ማረገገጡንና ይሄው አመልካቹ ታጥቆት የነበረውና በእለቱ በጠቡ ቦታ ነበር የተባለ ሌላ የፖሊስ ባልደረባ ታጥቆት የነበረው ቁጥር Aw-5521 የሆነ መሣሪያ ሁለቱም ለፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ተልከው ከእነዚህ ሁለት መሣሪያዎች በየትኛው ጥይት እንደተተኮሰ ምርመራ ተደርጎ ውጤቱ እንዲገለጽ በተጠየቀው መሠረት አመልካች ታጥቆት ከነበረው ማሣሪያ እንዳልተተኮሰና ከሌላው መሣሪያ ጥይቱ እንደተተኮሰ ድርጊቱ ከተፈፀመበት ሥፍራ ከተገኘ የጥይት ቀለህ ጋር አገናዝቦ በመመር ሊረጋገጥ እንደቻለ የፍርንሲክ ምርመራ ክፍሉ ከደረሰበት የምርመራ ውጤት መረዳት እንደተቻለ ተገንዝበናል፡፡ ይህ በአመልካች በኩል የቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሣያገኝ የቀረው አመልካች ታጥቆት በነበረው መሣሪያ ጥይት ተኩሶ ሚችን ስለመምታቱ በዐ/ሕግ ምስክሮች የተነገረ በመሆኑ የባለሙያው አስተያየት በምስክሮች ቃል ላይ ጥርጣሬን ሊፈጥር አይችልም ይልቁንም አመልካች የፖሊስ ባልደረባ በመሆኑ እንዳይቀጣ በማሰብ በጊዜው ይዞት የነበረውን መሣሪያ በመቀየር ሌላ መሣሪያ እንዲመርመር በማስደረግ አመልካችን ለማዳን የተደረገ

ነው የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ የባለሙያ ማስረጃ ባለሙያው የሚደርስበት ውጤት /finding/ ሙያ አስተያየት /0pinion/ እንጂ በተራ ምስክር እንደሚነገር ፍሬ ነገር /fact/ ተደርጎ ሊወሰድ ስለማይችል አብዛኛውን ጊዜ የባለሙያ የምስክርነት ቃል ሙሉ ዕምነት የሚጣልበት ማስረጃ /conclusive proof/ የመሆን ብቃት የለውም ምክንያቱም ባለሙያው በመስኩ የሚኖረው የዕውቀት አድማስ ለምርመራው የሚታገዝበት መሣሪያ ዘመናዊነትና የጥራት ደረጃ በሚደርስበት መደምደሚያ ላይ የእራሱን የሆነ አሉታዊ ወይንም አዎንታዊ ውጤት ሊኖረው ስለሚችል ነው፡፡

በተያዘውም ጉዳይ በሶስቱ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች አመልካች በወቅቱ ታጥቆት በነበረው መሣሪያ አንድ ጥይት ተኩሶ ሟችን ስለመምታቱ የተነገረ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ታጥቆት በነበረው መሣሪያ ጥይት አልተተኮሰም ተብሎ በባለሙያው የተደረሰበት ድምዳሜ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ከባለሙያው ሙያዊ ብቃት አኳያ ከሚጠቀምበት የምርመራ መሣሪያ ብቃት አንፃር ሲታይ ባለሙያው የተሣሣተ ድምዳሜ ላይ እንደደረሰና በምስክሮቹ የተነገረውን ፍሬ ነገር ሊያስተባብል የሚችል አቅም ያለው ማስረጃ እንዳልሆነ መገንዘብ ቢቻልም በአመልካች ላይ የወንጀል ክስ ያቀረበው ዐቃቤ ሕግ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱን ተከትሎ የወንጀሉ ድርጊት የተፈፀመው በአመልካች ሣይሆን በሌላ ግለሰብ ዓማካይነት እንደተፈፀመና በዚህም ግለሰብ ላይ ጥፋተኛነትን ሊያረጋግጥ የሚችል በቂ ማስረጃ እንዳለው በማመን በዚሁ ግለሰብ ላይ በዚሁ ጉዳይ የወንጀል ክስ ማቅረቡን ተረድተናል፡፡ የዐቃቤ ሕግ መ/ቤትም መንግሥታዊ ተቋም እንደመሆኑ መጠን በመርህ ደረጃ ኃላፊነቱን በታማኝነት ይወጣል ተብሎ ይገመታል፡፡ ስለሆነም ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት የግድያውን ወንጀል የፈፀመው አመልካች ሣይሆን ሌላ ግለብ ነው በማለት ሌላ ክስ ማቅረቡና አዲስ ባቀረበው ክስም በቀድሞው ክስ

የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው ከነበሩት ሶስት ምስክሮች መካከል ሁለቱ በአዲስ ክስ በምስክርነት መቆጠራቸው ሲታይ አመልካች ሚችን 1 ጥይት ተኩሶ ሲመታው አይተናል ተብሎ አስቀድሞ በሶስቱ ምስክሮች ተነግሮ የነበረው የምስክርነት ቃል በከፍተኛ ሁኔታ ጥርጣሬ ውስጥ የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም በሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ሁኔታ በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኛነት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 17984 በ16/11/99 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መ.ቁ. 13861 በ30/3/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ 195/2/ለ/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በሚች ግድያ ጥፋተኛ ሊባል የማይገባው ስለሆነ በነፃ እንዲሰናበት ወስነናል፡፡
3. የጎንደር ማረሚያ ቤትም ከእሥር እንዲፈታው ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ 35095

ህዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ተረፈ ድሪባ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. የ፱ አለቃ ድሪባ ፈይሣ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ጥጋቧ አሰፋ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት ያደገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ሚያዚያ 10 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተጠሪዎች በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቀበሌ 10 የቤት ቁጥር 1454 የሆነና በካርታ ቁጥር 20266 ከሚታወቀው 300 ሜትር ካሬ ንብረታቸው ላይ ሦስት ክፍል ሠርቪስ ቤቶችን የያዘ 200 ካ.ሜትር ንብረታቸውን ሐምሌ 29 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ የቤት ሽያጭ ውል በብር 45,000.00 /አርባ አምስት ሺህ ብር/ እንዲሸጡላቸው ከሸያጩ ዋጋውም ብር

40,000/አርባ ሺህ ብር/ ከፍለው ቤቱንና የካርታውን ኮፒ መረከባቸውን ከቀረው ብር 5000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ውስጥም ብር 2000.00 /ሁለት ሺህ ብር/ ተጠሪዎች የወሰዱ በመሆኑና የንብረቱን ስመ ንብረት ማዛወር ሲገባቸው ይህንኑ አለመፈፀማቸውን በመዘርዘር ተጠሪዎች የቤቱን ቀሪ ዋጋ ብር 3000.00 /ሦስት ሺ ብር/ ተቀብለው የቤቱን ስመ ንብረት ለአመልካች እንዲያዛውሩና የገደብ መቀጫ ከእነወለዱና ከክሱ ውጪ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው የአሁኑ ተጠሪዎችም በተከሣሽነታቸው ቀርበው በሠጡት መልስ ውሉ መደረጉን አምነው ሆኖም የቤቱ ባለቤት የሆኑት 1ኛ ተጠሪ በውሉ ወቅት የአእምሮ በሽተኛ ስለነበሩ እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በህግ የተሰጠ የሞግዚትነት ስልጣን ስላልነበራቸው የ1ኛ ተጠሪ ሙሉ ፈቃደኝነት በሌለበት ሁኔታ የተደረገ ህገወጥ ውል በመሆኑ ሊፈርስ የሚገባው እንጂ ለመፈፀም የሚገደዱበት አለመሆኑን በማንሣት ተከራክረዋል የስር ፍ/ቤትም ክሱን ከሠማ በኋላ በእርግጥ በተጠሪዎች ሙሉ ፈቃደኝነት የተደረገ ውል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በቅድሚያ በመያዝ ይህንንም ለማጣራት በውሉ ወቅት የነበሩትን ምስክሮች አስቀርቦ ሠምቶ በነበረበት ሁኔታ የሠበር ሠሚ ችሎት በመ/ቁ 21448 ስለ ፍ/ሕ/ቁ 1723(1) ድንጋጌ ትርጉም የሠጠበት ውሣኔ መድረሱን በመግለጽ አመልካች እንዲፈፀምላቸው ክስ ያቀረቡት ውል ግራ ቀኙ በምስክሮች ፊት ያደረጉት ከመሆኑ በቀር በውል አዋዋይ ፊት ወይም በፍ/ቤት መዝገብ የተደረገ ውል ባለመሆኑ ሠነዱ የውል ረቂቅ እንጂ ውል ሊባል ስለማይችል ውል ሣይኖር ደግሞ የውል ግደታ እንዲፈፀም ክስ ማቅረብ አይቻልም የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ የአመልካች ክስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) ድንጋጌ አያሟላም በማለት ውድቅ አድርጐ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይኸው ፍ/ቤት

ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ታህሣስ 30 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሠበር አቤቱታ ማመልከቻ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በነበረው ክርክር ሻጮች ስመ ግብሩን በገዥ ስም እንዲያዛውሩ ክስ ከመቅረቡ በስተቀር በውሉ ላይ ምንም ዓይነት አለመግባባት የተፈጠረ ነገር ሣይኖር የሠበር ችሎት ውሣኔ ተጠቅሶ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ ውሉ ህጋዊነት አለው ስመግብሩ በአመልካች ስም ሊዛወር ይገባል ተብሎ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሠበር አቤቱታው ተመርምሮም በሠበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም የስር ፍ/ቤት ወደ ውሉ ይዘት መግባቱ ተገቢነት ያለው እንጂ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሊባል የማይገባ መሆኑን የሚያሣይ ነው አመልካች በበኩላቸው ሚያዝያ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጭብጥ የስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የማያሟላ ነው በማለት

ክሱን ውድቅ ከማድረግ አልፎ የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት በግራ ቀኙ መካከል ሐምሌ 29 ቀን 1993 ዓ.ም የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል መኖሩ የተካደ ጉዳይ አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩት የሽያጭ ውሉ ነፃ በሆነ ፈቃደኝነት የተደረገ አይደለም የሚል ምክንያት በማንሣት ሲሆን የውል ይፍረስልን ጥያቄም በህጉ አግባብ አላቀረቡም፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ግራ ቀኙ የውሉን መኖርና ፎርማሊቲ አስመልክቶ ክርክር ያላነሱ መሆኑን ነው እንዲህ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት በተከራካሪዎች ያልተነሣ መከራከሪያ ነጥብ በማንሣት ውሣኔ ለመስጠት የማያስችል የህግ ምክንያት የለም በፍ/ሕ/ቁ 1723(1) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ይዘት በተከራካሪ ወገኖች ባልተነሣበት የክርክር ሂደት ፍ/ቤቱ በራሱ አነሣሽነት ማንሣትን በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች መሠረት ጭብጥ ተደርጐ ያልተያዘን ነጥብ በመያዝ ውሣኔ ማሣረፍ የፍትሐብሔር ጉዳይ የክርክር አመራር ሥርዓት የሚፈቅደው አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት እየተገባው የውሉ መኖርና ፎርማሊቲ በተከራካሪዎች ባልተነሣበት ሁኔታ በዚሁ አነሣሽነት በማንሳት የቀረበውን ሠነድ የውል ረቂቅ ነው ወደሚለው ድምዳሜ መድረሱም ሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ የስር ፍ/ቤትን ትንታኔ በመቀበል በአመልካች በኩል የቀረበለትን ይግባኝ ሣይቀበለው መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተገቢነትን በዚህ ችሎት መመልከቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል አመልካች ተደርጓል በሚሉት የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ቤትና ቦታውን ተረክበው በይዞታቸው ስር የሚገኝ መሆኑን

ባቀረቡት ክስም ሆነ እስከዚህ የሰበር ችሎት ባደረጉት ክርክር ላይ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቤቱን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሠነዶ በሻጮች በኩል አልተሠጡኝም ወይም መሟላት የሚገባው ሠነድ ሁሉ በሻጮች እጅ ቀርቷል በማለት በክርክሩ ሂደት ያልገለፀ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች በተጠሪዎች በኩል ሣይፈፀም ቀርቷል የሚሉት ነገር የስመ ንብረቱ ዝውውር ጉዳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የሚስተናገደው በመንግሥት አስተዳደር ክፍል ነው እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሻጭ የሚፈጽመው የውልም ሆነ የህግ ግዴታ ተደርጐ የሚወሰድ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ በፍ/ሕ/ቁ/ 1195(1) ስር በተደነገገው አኳኋን በስራው ባለቤት የመንግሥት አስተዳደር ክፍል የሚስተናገድ ሲሆን የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዢቹ ንብረቱን እና አስፈላጊ ሠነዶችን ተረክቤአለሁ የሚል ወገን ውሉንና አስፈላጊ ሠነዶችን በመያዝ ለሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል በማቅረብ ተገቢውን ከማስፈፀም በቀር ሻጭን ለመክሰስ የሚያስችል የክስ ምክንያት የሌለው ነው፡፡ በክስ አቤቱታ የተገለፀው ፍሬ ነገር የማያስከስስ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ክሱ ተቀባይነት የለውም ተብሎ መወሰን የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231(1)(ሀ) ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ የገለፁት ፍሬ ነገርና በመጨረሻ የተጠየቀው ዳኝነት የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ክሱን ውድቅ በማድረግ ሊያስወስን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የስር ፍ/ቤት በውሉ መኖርና ፎርማሊቲ በግራ ቀኙ ክርክር ሣይቀርብበት በራሱ ጊዜ ማንሳቱ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ በዚህ ረገድ የሠፈረው ትችት ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የስም ይዛወርልኝ በመሆኑ የክስ ምክንያት ስለማይኖረው ክሱ ውድቅ ሊሆን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 68148 ሠኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም ተሠጥት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57902 ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ በፀናው ውሣኔ ውል የለም የተባለው ትችት ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ይኸው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል ይፃፍ፡፡
2. በአመልካች የክስ አቤቱታ የተገለፀው የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት የሌለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ የሠጠው የውሣኔ ክፍል በውጤት ረገድ ተገቢ በመሆኑ ይኸው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መጋቢት 04 ቀን 2000 ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ
5. መዝገቡ ያለቀለት በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የ ሀ ሳ ብ ል ዩ ነ ት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ በአብላጫው ድምጽ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በህግ የሚፀና ውል አለ በማለት በሰጠው ውሣኔ የምስማማ ሲሆን በሁለተኛው ማለትም አመልካች ያቀረበው የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት የሌለው ነው በማለት በሰጠው ውሣኔ የማልስማማ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

አመልካች ተጠሪዎች በውል የሸጡልኝን ቤት ስመ ንብረት እንዲዛወሩ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በቂ የክስ ምክንያትና የህግ ድጋፍ ያለው ጥያቄ ነው፡፡ የአመልካች ጥያቄ ተጠሪዎቹ የባለቤትነት ደብተር በስሜ አሠርተው ይስጡኝ የሚል አይደለም፡፡ የአመልካች ጥያቄ ተጠሪዎች የቤቱን ባለሀብትነት ወደ እኔ ለማዞር መፈፀም ያለባቸውን አስፈላጊ ተግባራት እንዲፈጽሙና በውል የገቡትን ሀላፊነት እንዲወጡ ይወሰንልኝ የሚል ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

የአመልካች ክስና ጥያቄ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም በማለት በመጀመሪያ ደረጃ አንድ የማይንቀሣቀሥ ንብረት የሸጠ ሰው በህግ የተጣለበትን ግዴታና ሀላፊነት መመርመርና በሁለተኛ ደረጃ የተሸጠውን ንብረት ባለሀብትነት ከሻያጭ ወደ ገዥ እንዲዛወር የሚያደርገው የአስተዳደር ክፍል በሻጭ በኩል እንዲሞሉና እንዲፈጽሙ የሚፈልጋቸውን ተግባራት መለየትና ከዚህ አንፃር ሻጭ ግዴታውን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም የሚለውን ጭብጥ መወሰን ያስፈልጋል፡፡

የማይንቀሳቀስም ንብረት የሸጠ ሰው በውሉ መሠረት ያለበት ግዴታና ሀላፊነት በሁለት የህግ ክፍሎች ተዘርዝሮ እንደሚገኝ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የማይንቀሣቀስ ንብረትን ሽያጭ ልዩ ባህሪ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ህግ አውጭው ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2875 እስከ ፍታብሔር ህግ ቁጥር 2895

የተደነገጉት ልዩ ድንጋጌዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ስለ ሽያጭ የተደነገጉት የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ናቸው። ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2876 እስከ 2895 የተደነገጉት ድንጋጌዎች የማይንቀቀስ ንብረት ሽያጭ ልዩ ባሕሪ በተለያየ መንገድ የሚፈፀሙ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭዎች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸውን ልዮ ደንቦች የሚደነግጉ ሲሆኑ እነዚህ ድንጋጌዎች የሻጭንና የገዥን ዝርዝር ግዴታና ሀላፊነት አይደነግጉም። ስለሆነም ህግ አውጭ በሽያጭ ሒደቱ የገዥና የሻያጭን ሀላፊነት አስመልክቶ በልዩ ድንጋጌዎቹ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ የሚመራው በዚሁ ህግ የአንድ ነገር ባለሀብትነትን ማስተላለፍ ስለሚመለከቱ ውሎች በተደነገገው አንቀጽ በተመለከተው ደንብ መሠረት እንደሆነ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2875 በግልጽ ደንግጓል። ከዚህ አንፃር ሲታይ የማይንቀሣቀሥ ንብረት የሸጠ ሰው የፍታብሐር ህግ ቁጥር 2879 መሠረት የንብረቱን ሰነድና ማስረጃ ለገዥ በመስጠቱ ብቻ በሺጭ ውሉ መሠረት መወጣት የሚገባውን ግዴታና ሀላፊነት ሙሉ በሙሉ ተወጥቷል ለማለት አይቻልም። የሺያጩ ሀላፊነት ሰነዶችን አሳልፎ ከመስጠት ያለፈና ከዚያም በላይ እንደሆነ በፍታብሔር ህጉ በአምስተኛ መጽሐፍ ስለ ሽያጭ የተደነገጉ ድንጋጌዎች በማየት ለመረዳት ይቻላል።

ስለሆነም በእኔ እምነት የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው በፍታብሐር ሕግ ቁጥር 2875 እና በፍታብሐር ህግ ቁጥር 2273 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሸጠውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብትነት ለገዥው የማዛወር ግዴታ አለበት። ይኸም የሻጭ የንብረቱን ባቤትነት ለገዥ የማዛወር ግዴታ በምን መልኩ መፈፀም እንደሚገባው ህግ አውጭው ‹‹ ሻጩ የሸጠውን ነገር የማያስነካ ውጤት ለገዥው ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ለመፈፀም ግዴታ አለበት›› በማለት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2281 በግልጽ ደንግጓል።

በእኔ እምነት የአመልካች ጥያቄ ተጠሪዎች የገዙትን ቤት ባለሀብትነት ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን እንዲፈጽሙለት ያቀረበ ነው። ስለዚህ የክርክሩ ጭብጥ ተጠሪዎች (ሻጮች) ለአመልካች (ለገዥ) የሸጡትን የማይንቀሳቀስ ንብረት (ቤት) ባለሀብትነት ለማዞር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን በመፈፀም ግዴታቸውን ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም የሚለው መሆን ይኖርበታል። የማይንቀሣቀሥ ንብረት ይዞታ ለገዥ አሳልፎ በመስጠትና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሰነዶች ለገዥ በማስተላለፍ ብቻ ሻጭ የንብረቱን ባሐብትነት ለገዥ ለገዣ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን በመፈፀም ግዴታውን ተወጥቷል። ማለት አይቻልም።

ምክንያቱም የቤቱን ባለሃብትነት ከሻጮች (ተጠሪዎች) ወደ አመልካች (ገዥ) የሚያዛውረው አስተዳደር ክፍል የተሸጠው ቤት ተጠሪዎች በህጋዊ ይዞታቸው ላይ የሰሩት መሆኑን ከሚመለከተው አካል በተሰጣቸው የግንባታ ፈቃድና በከተማው አስተዳደር በፀደቀ ፕላንና ዲዛይን መሠረት የተሠራ መሆኑን በባለሙያ አሳይተው ማረጋገጫ እንዲያቀረቡ በተሸጠው ቤት ሲከፈል የሚገባው የጣሪያ፣ የአፈር ግብር፣ የሊዝ ኪራይ ዋጋ እና የመሳሰሉት ክፍያዎች ፈጽመው ያጠናቀቁ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ቤቱ ከማናቸውም ዕዳና እገዳ ነፃ ስለመሆኑ ከሚመለከተታቸው አካላት ማስረጃ እንዲያቀረቡና በመጨረሻም ቤቱን በአመልካች የሸጡ መሆኑን ከታተመ የስም ማዛወሪያ ቅጽ ላይ ቀርበው እንዲፈርሙ ይጠይቃል።

ሻጮች ቀርበው ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆኑ ገዥ ቤቱን በህግ በሚፀና ውል የገዛ መሆኑንና በውሉ መሠረት ሌሎች አስፈላጊ ፎርማሊቲዎች ተሟልተውና ተጣርቶ የቤቱ ስመ ንብረት ለገዥ እንዲዛወር በፍርድ ቤት የተሰጠ ትእዛዝ ወይም ውሣኔ የአስተዳደሩ ክፍል ይጠይቃል።

ሻጮች ቀርበው ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆኑ ገዥ ቤቱን በህግ በሚፀና ውል የገዛ መሆኑንና በውሉ መሠረት ሌሎች አስፈላጊ ፎርማሊቲዎች ተሟልተውና ተጣርቶ የቤቱ ስመ ንብረት ለገዥ እንዲዛወር በፍርድ ቤት የተሰጠ ትእዛዝ ወይም ውሣኔ የአስተዳደሩ ክፍል ይጠይቃል፡፡

ተጠሪዎች ለአመልካች ሰርቪስ ቤት የሸጡት ከነባር ይዞታ ቦታቸው ቀንሰው ሲሆን አመልካች የገዛው ቤት ባለሀብትነት በከተማ አስተዳደሩ የሚመዘገበው ተጠሪዎች የቦታው ካርታና ፕላን እንዲሻሻል በማድረግ ለአመልካች ለገዛው ቤትና ይዞታ ካርታና ፕላን አውጥተው ሲሰጡትና ሌሎች ክፍያዎችን አሟልተው ከፍለው ቤቱን ከእዳና ዕገዳ ነፃ መሆኑን ማረጋገጫ ሲያቀርቡና ቤቱን ለአመልካች የሸጡ መሆኑን ለአስተዳደር ክፍል በማቅረብ በስም ማዞሪያ ቅጽ ላይ ሲፈርሙ ነው፡፡ ተጠሪዎች የካርታና ፕላን ማሻሻያ አላሰሩም፡፡ የጠቅላላውን ቦታ ካርታና ፕላን ኮፒ ሰነድ አመልካች እንዲሰጡት ከክርክራቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች እንኳንስ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2281 መሠረት የቤቱን ባለሀብትነት ለአመልካች ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ሊፈጽሙ ቀርቶ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2879 በሚደነግግው መሠረት የቤቱን ባለሀብትነት በማዛወር የሚረዱ ህጋዊ ማስረጃዎች ባልሰጡበት ሁኔታ የአመልካች ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም መባሉ ተገቢ ነው ብዬ አላስብም፡፡ የአስተዳደሩ ክፍል በአመልካች ስም የባለቤቱን ባለሀብትነት በማዛወር ማስረጃ የሚሰጡ በመጀመሪያ ተጠሪዎች የቤቱን ባለሀብትነት ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ሲፈጽሙ ነው፡፡ ተጠሪዎች የቤቱን ባለሀብትነት ለአመልካች ለማዛወር መስፈፀም የሚገባቸውን ተግባራት ሁሉ የፈፀሙ ስለሆኑ አላስረዱም በተቃራኒው ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር የቤቱን ባለሀብትነት ለአመልካች ለማዛወር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች ተጠሪ የቤቱን ሽያጭ በውሉ መሠረት እንዲፈጽሙና ስመንብረቱን ለአመልካች ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን እንዲፈጽሙ የቀረበው ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2875 በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2273 ንዑስ አንቀጽ 2 በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2281 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2879 መሠረት የቀረበ ስለሆነ በቂ የሆነ ተጠሪዎችን የሚያስከስስ ምክንያት አለው፡፡ ተጠሪዎች የሸጡትን ቤት ስመንብረት (ባለሀብትነት) ለአመልካች ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታና ሀላፊነት አለባቸው በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰበር መ/ቁ 35207

ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዲልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወጋገን ባንክ - ነ/ፈጅ ጋዲሣ ታሬሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- መቂ ማዘጋጃ ቤት በሌለበት የሚታይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ 5ኛ ተከሣሽ ነበር፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ተጠሪ በአንድ የቦታ ይዞታ ላይ ተደራራቢ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) በስር ፍ/ቤት አንደኛ ተከሣሽ ለነበሩት ለአቶ ቡሽራ ጅማ ሠጥቶ እኚሁ ግለሰብ እነዚህን በአንድ ይዞታ ላይ በተደጋጋሚ የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በዋስትና በማስያዝ ከአመልካች ባንክ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ብድር መውሰዳቸውን ተጠሪ በተደጋጋሚ በተሰጡ የምስክር ወረቀት ላይ አመልካች የተፈራረመውን የመያዣ ውል በማይንቀሣቀስ ንብረት መዝገብ ላይ በመመዝገብ ለአመልካች የጽሑፍ ማረጋገጫ መስጠቱንና በዚህም ምክንያት ብድሩ ተለቆ ከተወሰደ በኋላ ተበዳሪው ብድሩን ባለመክፈላቸው በህጉ በተሰጠው ስልጣን መሠረት አመልካች

ቤቶቹን ለመሸጥ ዝግጅት ሲያደርግ ቤቶቹ በመያዣነት ይዘናል ከሚሉት ባንኮች መካከል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሐራጅ ለመሸጥ ማስታወቂያ ማውጣቱ በመዘርዝር ቤቶቹ ቢሸጡ በአመልካች ለሚደርሰው ጉዳት ተጠሪ ተጠያቂ እንዲባል ሐምሌ 22 ቀን 1994 ዓ.ም የተፃፈ ክሰ በተጠሪ ላይ በመመስረቱ ነው፡፡ ተጠሪም በስር ፍ/ቤት ቀርቦ በሠጠው የመከላከያ መልስ አመልካች በጠየቀው መሠረት ቤቶቹና ቦታዎቹ ከእዳና እገዳ ነፃ መሆናቸውን በማረጋገጥ መፃፉ እውነት መሆኑን ከሣሽ ብድር ከመስጠቱ በፊት ንብረቶቹ በካርታ ልክ መሆናቸውን ማረጋገጥ የአመልካች ግዴታ መሆኑን የካርታ ለውጥ ተደረገ የሚገባለው ሐስት መሆኑንና ለመያዣ ተያዙ የተባሉ ቤቶችም ሣይለወጡ መኖራቸውን በውሎች ላይ የቤቶቹ ቁጥርና ግምታቸው መቀመጡ አመልካች በቦታዎቹ ላይ ተገኝቶና ቤቶቹን አስገምቶ ማስቀመጡን እንደሚያሣይና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቤቶቹ ጨረታ ለማውጣቱ ማስረጃ አለመቅረቡንና የእነዚህ ቤቶች ቁጥርና የአመልካች መያዣዎች ቁጥር ተመሣሣይ አለመሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የሰር ፍ/ቤትም ተጠሪ ይዞታቸው የተቀየረ ካርታዎችን በማዘጋጀት በሌሎች ባንኮች እንዲያዙ ስለማድረጉ አመልካች ማስረጃ አላቀረበም በማለት ተጠሪ አላፊነት የለበትም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዮን ከመረመረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፊጅ ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረበው የሠበር አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ

ይገባዋል ተብሎ ለተጠሪ የፍ/ቤቱ መጥሪያ ተልኮለት ከተቀበለ በኋላ መልሱን ይዞ ባለመቅረቡ መልሱን በጽሁፍ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ ለአቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ ለብድር ገንዘቡ አላፊነት የለበትም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት አመልካች ለመያዣነት ይገፎዋለሁ የሚላቸው በመቂ ከተማ የሚገኙ ቤቶች ከእዳና ዕገዳ ነፃ መሆናቸውን ተጠሪ በጽሑፍ ያረጋገጠለት መሆኑ አመልካች የብድሩን ገንዘብ ባለመክፈሉ የተነሣ በህጉ በተሰጠው ስልጣን መሠረት መያዣዎችን ለመሸጥ ሲንቀሣቀስ ዕዳና ዕገዳ የለባቸውም የተባሉት ቤቶች ካርታና ፕላናቸው ተቀይሮ ለኢትዮጵያ ንገድ ባንክ ዕዳና ዕገዳ የሌለባቸው መሆኑ ተገልጾለት በመያዣነት ከያዛቸው በኋላ በጨረታ ለመሸጥ ማስታወቂያ ያወጣባቸው መሆኑ መገለፁን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍ/ቤት በአመልካች የተገለፀው ፍሬ ነገር በማስረጃ አልተደገፈም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የስር ፍ/ቤት ድምዳሜ የአመልካች ክስ ሙሉ በሙሉ በማስረጃ አልተደገፈም የሚል ይዘት ያለው መሆኑ ሲታይ በውሣኔ አሠጣጥ ሂደት ጠቃሚ መስሎ በታየ ጊዜ በፍ/ቤት ሊፈፀም ስለሚገባው የማስረጃ ማጣራት ሂደት ያላገናዘበ ነው አንድ ክስ ዳኛን ሊያሣምን የሚችል ብቃት ያለው ማስረጃ /Prima facie evidence/ ተደግፎ መቅረብ ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ላይ ጥብቅ መሆኑን በዚህ ረገድ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመመልከት መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የማስረጃ ምዘናውም በጥንቃቄ ሊከናወን የሚገባው መሆኑን ያስረዳል፡፡ ፍ/ቤት የከሣሽን ክስ

የሚደግፍ አግባብነት ያለው ማስጃ ቀርቦ እያለ በደፈናው ማስረጃ አልቀረበም በሚል ምክንያት መወሰን አይችልም፡፡ ይልቁንም በትክክለኛ ፍትህ ለመድረስ ያመቸው ዘንድ በሥነ ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች የተሰጡትን ሥልጣኖችን በመጠቀም የማስረጃ ምዘናው የጠራ እንዲሆን በማስረጃ አቀራረብ ተገቢውን ሚና ሊጫወት ይገባል፡፡ በሌላ አገላለጽ በትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 257 እና 264 ድንጋጌዎችም ይህንኑ ያስረዳሉ የእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማም የፍርድ ሂደቱን የተሟላ ማድረግ መሆኑ ይገመታል፡፡

እጃችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በመያዣ ይገፍአቸዋለሁ የሚላቸው ቤቶች እና ሌሎች ባንኮችም በመያዣነት ይዘዋቸዋል የተባሉት ቤቶች ካርታና ፕላን መቀያየሩ እስከተረጋገጠ ድረስ በእርግጥም ካርታና ፕላኑ የተቀያየረባቸው ቤቶችና ቦታዎች አንድ መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው በስር ፍ/ቤት በጭብጥነት ተይዞ በአመልካች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች አግባብነት ጥንካሬና ክብደትን በመመልከት እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ ሲባል ተገቢው ማጣራት ተደርጐ ውሣኔ መሰጠቱን የክርክሩ ሂደትና የስር ፍ/ቤት የውሣኔ አሠጣጥ አያሣይም፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካች ክስ በማስረጃ አልተደገፈም ከማለት ውጭ ለዚሁ መነሻ ያደረው ምክንያት ግን ግልጽነት የጐደለው እና በበቂ የህግ ምክንያት የተመረኮዘ አይደለም፡፡ አጠቃላይ የፍርድ ሂደቱ ተገቢው ማጣራት ሳይደረግ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ ሲታይ የፍርድ ሂደቱ ያልተሟላ ነው በሚል ምክንያት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በለማት የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ችሎት እምነት መሠረት የፍርድ ሂደቱ የተሟላ ይሆን የነበረው ለአንድ ቦታ ሁለት ካርታ ተሠጥቷል አልተሠጠም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ በአመልካች በኩል ከቀረቡት የጽሑፍ ሠነዶች በተጨማሪ አንድ ገለልተኛ

መሐንዲስ ባለሙያ በቦታው ተመድቦ ሙያዊ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ቢደረግ ነበር፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህንኑ ሣይፈፀም ለአመልካች ማስረጃዎች የሠጠው መደምደሚያ አሣማኝነት ባለው ትንታኔና በበቂ የህግ ምክንያት ያልተደገፈ ሲሆን ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማረም ጉዳዮ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት መመለስ ሲገባው የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14460 ሠኔ 06 ቀን 1998 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 26644 ህዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የስር ፍ/ቤት የፍርድ ሂደት የተሟላ አይደለም ብለናል፡፡
3. የስር ፍ/ቤት ለአንድ ቦታ ሁለት ካርታ ተሰጥቷል አልተሠጠም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ አንድ ገለልተኛ መሐንዲስ ባለሙያ መድቦ ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በኋላ በተጠሪ አላፊነት እና የአላፊነት መጠን ላይ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዮን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ
4. አመልካች ወጪና ኪሣራ የራሱን ይቻል ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 35651

ጎንደር 4 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አብርሃ አባተ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ውብዓለም በሪሁን ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠተው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 71710 ሰኔ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 58316 ታህሣስ 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በመጠየቃቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት ቀርቦ ከተጠሪ ጋር በነበረን የቤተሰብ ግኑኝነት በእንግድነት በቤቴ ለሶስት ወር ያህል እንድታርፍ ፈቅጀላት ከቤቴ በእንግዳነት ከገባች ብኋላ እንድትወጣልኝ ስጠይቃት ለመውጣት ፈቅደኛ አይደለችም፡፡ ስለዚህ በይዞታየ ላይ ሁከት እየፈጠረችብኝ ስለሆነ ቤቱን ለቃ እንድትወጣ ወሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርባ ከአመልካች ጋር በጋብቻ አብረው የሚኖሩና ልጅም የወለዱ መሆኑን በመግለጽ ከጋራ ቤቱ እንድወጣ

ያቀረበው ክስ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክራለች፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካች ሚስት ናት ወይስ አይደለችም የሚለውን ጭብጥ በመያዝና የተጠሪን የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጋብቻ መኖሩን ባያረጋግጡም አመልካችና ተጠሪ ከሶስት ዓመት በላይ እንደ ባልና ሚስት ከጋብቻ ውጭ አበረው የኖሩ ስለሆነ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 102 መሰረት ክርክር የተነሳበት ቤት የጋራ ቤት ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት እኔ ከጠየቅሁት ዳኝነት በመውጣት ጭብጥ መስርቶ ስለእኔና ተጠሪ ግኙኝነትና የጋራ ንብረት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ በህተት ነው፡፡ ተጠሪ ህጋዊ ሕጋብቻ አለኝ በማለት ክስ አቅርባ በሌላ መዝገብ እየተከራከርን ባለንበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ባልተጠየቀ ዳኝነት በአቋራጭ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ ስላልሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሏ እኔ ካቀረብኩት ክርክር በመነሳት የሥር ፍርድ ቤት የያዘው ጭብጥና የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ ስለዚህ አቤቱታው ውድቅ በማድረግ ያሰናብተኝ በማለት መልስ ያቀረበች ሲሆን አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የመሰረተው ጭብጥና የሰጠው ውሣኔ ተገቢነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በሥር ክስ ያቀረበው ተጠሪ ለሶስት ወር ያህል በቤቱ እንድትጠለል በእንግድነት አስጠግቻት ነበር፡፡ አሁን ግን ከቤት አልወጣም

ስላለችና ቤተሰቤን እየረበሸች ስለሆነ ከቤቱ እንድትወጣ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ሲሆን ተጠሪ በበኩሏ ከአመልካች ጋር በአንድ ቤት መኖር የጀመረችው በእንግድነት ተጠግታ ሣይሆን ከተጠሪ ጋር የጋብቻ ግኑኝነት ስላላት መሆኑን ጠቅሳ ቤቱም የጋራ ንብረቱ ስለሆነ ለቅቂ አልወጣም በማለት ተከራክራለች፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ጭብጥ የሚመሰርተው በክሳሽ በኩል የቀረበውን ክስና ማስረጃ በተከሳሹ በኩል በምክንያት ከቀረበው መልስ ጋር በማገናዘብ መሆኑን ከፍታብሔር ሥነ ሥርአት 255 ንኡስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦና በፍትብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 215 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የዳኝነት ክፍሉ የጠየቀው ተጠሪ ከቤቱ በእንግድነት ገብታ አልወጣም በማለት ሁከት እየፈጠረችብኝ ስለሆነ ከቤቱ እንድትወጣ በማለት ነው፡፡ አመልካች የጠየቀውን ይህንን ጥያቄ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ በመካድ ከቤት የገባሁት በሕጋዊ መንገድ በሚስትነት ነው በማለት ተከራክራለች ይህንንም የሚያሣዩ ማስረጃዎችን አቅርባለች፡፡ ስለሆነም በመዝገቡ መያዝ የሚገባው መሰረትዊ ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች ቤት ውስጥ በሕገወጥ መንገድ በመግባት ሁከት እየፈጠረች ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ መሆን ነበረበት፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በህጋዊ መንገድ በቤቱ ውስጥ የገባችና የምትኖር መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ተጠሪ የፈጠረችብህ ሁከት የለም፡፡ ቤቱንም ለቅቃ እንድትወጣ ያቀረበከው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን በመዝጋት ማሰናበት ነበረበት፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች መኖሪያ ቤት የገባችው በሕጋዊ መንገድ በመሆኑ ቤቱን ለቅቃ እንድትወጣ በአመልካች በኩል የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢና ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት ውሣኔ ነው፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ቀጥታ ጭብጥ ሆኖ ያልቀረበለትንና ተጠሪ ከቤቱ እንድትወጣ ትእዛዝ ይሰጥልኝ የሚለውን የአመልካችን ጥያቄ ተጠሪ ለማስተባበል ያቀረቀበችውን መከራከሪያ መነሻ

በማድረግ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ስላለው ግኑኝነት ጭብጥ በመያዝ ውሣኔ መስጠቱ የይዘትና የሥነ ሥርአት ሕግ ስህተት የፈፀመ መሆኑን ያሣያል።

የመጀመሪያ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያላትን ግኑኝነት ያነሣቸው አመልካች ያቀረበባትን ክስ ለመከላከል ነው። ተጠሪ ፍርድ ቤቱ ከአመልካች ጋር ያላትን ግኑኝነትና የጋራ ንብረት ሁኔታ እንዲወሰንላት ከፈለገች በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 215 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ በመክፈል የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ማቅረብ ነበረባት። ተጠሪ የሥነ ሥርአት ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት የተከሳሽ ከሳሽነት ባላቀረበችበትና አመልካችም በተጠሪ በኩል የሚቀርበው ጥያቄ በተሟላ ሁኔታ የመከላከያ መልስና ማስረጃ አቅርቦ ባልተከላከለበት ሁኔታ ተጠሪ የአመልካችን ክስ ተገቢ አለመሆኑን ለማሣየት በአጋጣሚ የነሳችውን የመከራከሪያ ሐሳብ ራሱን እንደቻለ ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ አድርጐ በመመልከትና የጉዳዩ ዋና ጭብጥ አድርጐ በመያዝ የሰጠው ውሣኔ ጉልህ የሆነ የሥነ ሥርአት ግድፈት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

በሁለተኛ ደረጃ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን ግኑኝነትና የጋራ ንብረት ጥያቄ ተጠሪ ዳኝነት ጠይቆ በሌላ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 43428 ግራ ቀኙ እየተከራከሩበት ያለ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል። ይኸ ከሆነ ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት አቅርባ በመካከላቸው ስላለው ግኑኝነትና የጋራ ሐብት ሁኔታ ውሣኔ እንዲሰጥላት ብትጠይቅ እንኳን ጉዳዩ ቀድሞ በጀመረው ችሎት በኩል ታይቶ መወሰን ያለበት መሆኑን በመግለጽ በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 7 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት መዝገቡን የመዘጋት ግዴታ አለበት። ስለዚህ ጉዳዩ በሌላ ችሎት በመታየት ላይ መወኑን እያወቀ ዳኝነት ያልተጠየቀበትንና በአጋጣሚ የተነሳውን ጉዳይ በዋና ጭብጥነት ይዞ መወሰኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሕግ ድንጋጌ የተላለፈና መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የሰራ መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ አግኝተነዋል።

በሶስተኛ ደረጃ አመልካች ባቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ መነሻ ተጠሪ ያቀረበችው መልስና መከራከሪያ በአመልካችና ተጠሪ ግኑኝነት እና የጋራ ንብረት ጥያቄ የሚወሰን ሣይሆን የልጆችን የልጅነት ሁኔታ ጭምር የሚነካና ራሱን የቻለ ክስና ማስረጃ ቀርቦበት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሰረት ታይቶ መወሰን ያለበት ጉዳይ ነው ስለሆነም ተጠሪ አመልካች ያቀረበውን ክስ ለመከላከል ባነሳችው መከራከሪያ በጭብጥነት በመያዝ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የልጆችን ሁኔታና ሌሎች ክርክሮችን የማይፈታ ውሣኔ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከላይ የተገለፁትን ስህተቶች በይግባኝ አይቶ እንዲታረሙ ማድረግ ሲገባው የአመልካችን ይግባኝ ሙሉ በሙሉ መሰረዙ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ የፈጠረችበት ሁከት የለም ቤቱንም ለቅቃ መውጣት የለባትም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ሆኖም የሥር ፍርድ ቤት ዳኝነት ከተጠየቀበት ጉዳይ በመውጣት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት በግብረስጋ ግኑኝነት አብሮ የመኖር ህጋዊ ግኑኝነት አለ ቤቱም የጋራ ንብረት ነው በማለት የሰጠው የውሣኔው ክፍል ብቻ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት በማሻሻል ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ የፈጠረችው ሁከት የለም፡፡ ቤቱንም ለቅቃ የምትወጣበት ምክንያት የለም በማለት የሰጡውን የውሣኔ ክፍል አጽንተናል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ እንደባልና ሚስት ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግኑኝነት አብረው የሚኖሩ ናቸው፡፡

ክርክር የተነሳበት ቤትም የጋራ ንብረታቸው ነው በማለት የሰጠውን የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. ይኸ ውሣኔ ተጠሪና አመልካች በመካከላቸው ያለውን ግኑኝነት የጋራ ንብረት ጥያቄና የልጆች ሁኔታ በመዝገብ ቁጥር 43428 ከመቀጠል ወይም በሌላ ሁኔታ መብታቸውን እንደ አዲስ ከመጠየቅ የሚገድባቸው አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ክርክር ያወጡትን ወጭ ግራ ቀኞቸው ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ ይኸ ውሣኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ኅዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 35695

ጎንደር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አሰማማው

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ አቃቤ ሕግ አውግቸው መኮንን

ተጠሪ፡- አቶ ተመስገን አዲስ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 15071 ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ለወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 የሰጠው ትርጓሜና ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ የሰጠውን ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች ተጠሪ 1996 ያወጣውን የኤፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንኡስ አንቀጽ 3 በመተላለፍ በቸልተኝነት ያሽከረክር በነበረው አይሱዙ መኪና እማሆይ ሙሉነሽ ደላላ የተባሉትን ገድሏል በሚል ክስ አቅርቦበታል፡፡ ይህ የወንጀል ክስ በሚታይበት ጊዜ ተጠሪ የዋስ መብቱ ተጠብቆ ከውጭ እየቀረብኩ እንድከራከር ይፈቀደልኝ በማለት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያመለከተ ሲሆን አመልካችን ወክሎ የሚከራከረው አቃቤ ሕግ በበኩሉ በተጠሪ ላይ የተጠቀሰው አንቀጽ እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ

https://chilot.me
ስለሆነ በወንጀሉም የሰው ሕይወት ለሕልፈተሞት የተዳረገ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 መሰረት የዋስ መብት የሚያስፈቅድ ባመሆኑ በእስር ሆኖ እንዲከራከር ትእዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ የዋስ መብት የማያስፈቅድ መሆኑን በመግለጽ የተጠሪን የዋስትና መብት ከጥያቄ ውድቅ አድርጐታል፡፡ ተጠሪ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄውን አስመልክቶ የሰጠውን ብይን በመቃወም ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ሕግ አውጭው የደነገገው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ሆነ ተብሎ የሚፈጸሙ በሰው መግደለ የተከሰሱ ሰዎችን የዋስ መብት ለመከልከል እንደሆነ የሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌውን በ1949 ዓ.ም ከወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንግጌ ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም፣በአዲሱ የወንጀል ሕግ የቅጣቱ መጠን እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ቢሆንም የሥነ ሥርአት ሕጉን ያወጀው ሕግ አውጭ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀሙ ሰዎችን የዋስ መብት የመከልከል ሐሳብ ያልነበረው በመሆኑ ተጠሪ የብር 2000/ሁለት ሺህ ብር/ ዋስ አቅርቦ እንዲለቀቅ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይኸ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕግ አተረጓጐምና የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የተከሰሰበት ጉዳይ እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ እያለና በወንጀሉም የሰው ሕይወት ለሕልፈት የተዳረገ መሆኑ በክሱ ውስጥ ተገልፆ እያለ እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች በተሟሉበት ሁኔታ ተከሳሹ በዋስትና ወረቀት እንደማይለቀቅ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጐ እያለ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል መፈፀም የዋስትና መብት አያስነፍግም የሚል ትርጓሜ በመስጠት ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል

https://chilot.me
የሚል የሰበር አቤቱታ አርቧል። ተጠሪ በበኩሉ በዋናው ጉዳይ ጥፋተኛ ስለተባልኩ አቤቱታው ውድቅ ይደረግ በማለት ተከራክሯል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ደረጃ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል። መዝገቡን እንደመረመርነው በኤፌዴሪ የወንጀል ሕግ የተሻሻሉና የተለወጡ ሁኔታዎች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ያላቸውን ተፈፃሚነትና ፍርድ ቤቶች ሊከተሉት የሚገባ የሕግ አተረጓጎም ምን መሆን አለበት? የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጓሜ ተገቢ ነው ወይስ አይደም የሚሉትን ነጥቦች መመርመር ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በኤፌዴሪ የወንጀል ሕግ መሰረታዊ የይዞታና የቅጣት ለውጥና መሻሻል የተደረገባቸው የወንጀል አይነቶች ያሉ መሆኑ አያከራክርም። ከወንጀል ሕጉ ጐንለጐን የወንጀል ሥነ ሥርአት ሕግ ተሻሽሎ አለመውጣቱ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያነሳቸውን የመከራከሪያ ሐሳቦችና ጥያቄዎች እንዲነሱ ክፍተት የሚፈጥር ስለመሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል። ሆኖም ሕግ አውጭው በአዲስ የወንጀል ሕግ ያወጣቸውና ያሻሻላቸው ጉዳዮች ባሉበት ሁኔታ በቀጥታ ከነበረው የሥን ሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ተጣምረው ተፈፃሚ እንዲሆኑና እንዲተረጐሙ ፍላጐትና ሐሳብ አለው ተብሎ መወሰድ ይኖርበታል። ስለሆነም በአዲሱ የወንጀል ሕግ ቅጣታቸው ከፍ ብሎ የተደነገጉ ወንጀሎች የዋስትና ጥያቄና ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የሚቀርቡ የሥነ ስርአት ጥያቄዎች 1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የነበረውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባትና ትርጓሜ መስጠት ሣያስፈልግ የሥነ ስርአት ህጉን ከአዲሱ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በቀጥታ አጣምሮ በማየት መወሰን ይኖርባቸዋል።

https://chilot.me

ከዚህ አንፃር አዲሱ የወንጀል ሕግ ከመውጣቱ በፊት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ብቻ ያስቀጣ የነበረው በቸልተኝነት ሰው የመግደል ወንጀል በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንኡስ አንቀጽ 3 እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ይሕ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላል ወይስ አያሟላም የሚለውን በመመዘን ብቻ መወሰን ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1949 በወጣው የወንጀል ሕግ የነበረውን ሁኔታ መነሻ በማድረግ የሰጠው የሕግ ትርጓሜ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርአት ሕግ ቁጥር 63 ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላና የዋስ መብት የማያስፈቅድ ሆኖ አያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ በዋስ እንዲለቀቅ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15071 ታህሣስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዘገብ ቁጥር 2077 ጎዳር 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. አመልካች በዚህ ፍርድ ቤት ያወጣውን ወጪ ራሱ ይቻል ብለናል ይህ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጎዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የሰበር መ/ቁ 35791

ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዲልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ መሠማ አሊ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ተናኜ አስገልጠው - ከጠ/ክፍሌ አሰፋ ጋር ቀረቡ

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ በዚሁ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች የቤታቸው አካል የሆነውን ማዕድቤት ያላግባብ ስለያዘባቸው እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ቤቱን በ28/12/85 ዓ.ም በተደረገ ውል የገዙት መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በፍ/ቤቱ በተደረገው የቃል ክርክር በውሉ ላይ ያልፈረሙ መሆኑን በመግለጽ ፊርማውን ክደዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ፊርማው የማን እንደሆነ እንዲጣራ ለፌ/ፖ/ፎ/ም መምሪያ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ የሠጠ ሲሆን መምሪያውም ፊርማው የተጠሪ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ተጠሪ በውሉ ላይ የፈረሙ መሆኑ ስለተረጋገጠና ውሉ በህግ ፊት አይፀናም የሚል መከራከሪያ ያላቀረቡ በመሆኑ ለአመልካች የሰጡትን ቤት እንዲመለስላቸው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ውሉ በፍ/ህ/ ቁጥር 1723(1) መሠረት ስላልተደረገ ውሉ

እንደረቂቅ የሚቆጠር ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች ውሣኔውን ተቃውመው ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቀርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ያልተነሣን ክርክር መሠረት አድርጐ መወሰኑ ስህተት ነው ክሱም የቀረበው ከ14 ዓመት በኋላ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ የውሉ ህጋዊነት ላይ ያነሱት ክርክር ሣይኖር ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት አድርጐ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት አቤቱታው ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ተጠሪ ቀርበው መልስ ሠጥተዋል፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔና ከህጉ አኳያ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ ክስ ያቀረቡት አመልካች የቤታቸው አካል የሆነው ማድቤት ያለአግባብ ስለያዘባቸው እንዲለቁላቸው ነው፡፡ አመልካችም ክርክር የተነሳበትን ቤት በ28/12/85 ዓ.ም ገዝተው የያዙት መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ በማስረጃነት በቀረበው ውል ላይ ያለውን ፊርማ ግን ተጠሪ ክደዋል ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ በውሉ ላይ የሠፈረውን ፊርማ ከመካዳቸው በቀር በውሉ ህጋዊነት ላይ ያነሱት ሌላ ክርክር የለም፡፡ ከሠበር አቤቱታ በሠጡት መልስ የውሉን ህጋዊነት አንስተው አለመከራከራቸውን አልካዱም፡፡ የተጠሪ ክርክር ክርክሩ ባይነሳ እንኳን ፍ/ቤቱ አስገዳጅ የሆነውን የህግ ድንጋጌ አንስቶ ከመወሰን አይታገድም በተለይ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) መሠረት በስር ፍ/ቤት ያልተያዘ ወይም ያልተነሣ የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ጭብጥ አንስቶ ሊያከራክርና ውሣኔ ሊሰጥበት ይችላል በማለት ነው፡፡ ይሁን

እንጂ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 329(1) እንደሚያመለክተው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተነሣ ክርክርና ያልቀረበ አዲስ ነገር ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ሊቀበለው አይችልም፡፡ በመሆኑም በሥር ፍ/ቤት ተከራካሪዎቹ ያላቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ውሣኔ መስጠት አይችለም፡፡ ተጠሪ የጠቀሱት የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2)ም ቢሆንም በሥር ፍ/ቤት ከነበረው ክርክር አኳያ ፍ/ቤት ሊወሰን ሲገባው ያልወሰነው ጉዳይ ካለና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባ ነበር ብሎ ካመነ ተከራካሪዎቹ በይግባኝ ደረጃ ባያነሱትም ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችለው ድንጋጌ እንጂ በተከራካሪ ወገኖች ያልተነሣን ክርክር አንስቶ ውሣኔ ለመስጠት የማያስችለው ስልጣን አይሰጠውም፡፡

በመሆኑም በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ውሣኔ መስጠት ይችላል በማለት ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ከክርክሩ ሂደት ተጠሪ በውሉ ላይ ያለውን ፊርማ ከመካዳቸው በቀር በሙሉ ህጋዊነት ላይ ያቀረቡት ክርክር እንዳልነበረ ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍ/ቤትም ባደረገው ማጣራት ከሽያጭ ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በሺያጭ ውሉ ላይ ያቀረቡት ብቸኛ ክርክር በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በተጠሪም ያልተነሣውን የውሉን ህጋዊነት በጭብጥነት ይዞ የሚወስንበት የህግ መሠረት ባለመኖሩ የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ ማድረጉ ስህተት ያለው ሆኖ አላገኘነውም በተቃራኒው ግን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያልተከራከሩበትን ጉዳይ መሠረት አድርጐ መወሰኑ የሥነ ሥርዓት ህጉን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57324 በ12/02/2000 የሠጠው ፍርድና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34212 በ21/05/2000 የሠጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10835 በ30/9/99 የሠጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ ይዘውታል በማለት እንዲመልሱላቸው የጠየቁትን ቤት ለአመልካች ያስተላለፉት በሽያጭ በመሆኑ ክሣቸው ተቀባይነት የለውም
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 35962

ኅዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሠልጣን አባተማም

አመልካች፡- አለምነው ደምሴ - ከጠ/ደሣለኝ አለሙ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ጀማነሽ አብዲ (8 ሰዎች) - ቀረቡ

ፍ ር ድ

ለአቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተጀመረ ነው፡፡

በሥር ፍ/ቤት ክሣሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ከተከሣሾች ከ1-3 ያሉት (ተጠሪዎች) ላይ ቤት መግዛታቸውን ገልፀው ተጠሪዎቹ የሸጡትን ቤት ባለሃብትነት የሚያስረዱ ካርታ ደብተር፣የግብር ክፍያ ሰነዶችና የመሣሰሉ ሰነዶች እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎችም በሰጡት መልስ ቤትና ቦታውን መሸጣቸውን አምነው ካላቸው ይዞታ ላይ ቀንሰው የሸጡ በመሆኑ ለተሸጠው ይዞታ የተለየ ካርታ፣ደብተር ወይም የተለያዩ ሰነዶች ስለሌለ ሊሰጧቸው የማይችሉ መሆኑን ገለፀዋል፡፡ በሌላ በኩል ከ4-8 ያሉት ተጠሪዎች ጣልቃ ገብተው ቤቱን የሥር ተከሣሾች የመሸጥ ሆነ የመለወጥ ስልጣን የላቸውም፣ ቤቱ የኛ የወራሾች እንጅ የተከሣሾች አይደለም ብለው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የሺያጭ ውሉ ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት ስላላሟላ ፈራሽ ነው ፈራሽ በሆነ ወይ ተጠሪዎች ሊገደዱ አይገባም በማለት ወስኗል ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ውሉ እንዲፈርስ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ ሣይኖር ውሉ እንዲፈርስ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ክርክር የተነሣበትን ቤት ከሥር ተከሣሾች(ከ1-3ኛ ካሉት ተጠሪዎች) ስለገዙ ተጠሪዎቹ ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችና ማስረጃዎች እንዲያስረክቧቸው ጠይቀዋል የስር ፍ/ቤትም የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የሰጠው ውሉ ሕጉ በሚጠይቀው መሰረት ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት አልተደረገም በማለት ነው፡፡ ከመዝግቡ ሂደትና ከግራ ቀኙ ክርክር ለክርክር ምክንያት የሆነው የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ሕ/ቁ.1723 መሰረት በዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት የተደረገ አለመሆኑን መገንዘብ ችለናል፡፡ አመልካችም ተጠሪዎች እንዲገደዱ እየጠየቁ ያሉት በዚህ በህጉ አግባብ ያልተቋቋመውን ውል መሰረት አድርገው ነው፡፡ ውሎች ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ ሕግ ሆነው አስገዳጅነት የሚኖራቸው ደግሞ በህጉ አግባብ እስከተቋቋሙ ድረስ ለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1731/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በህጉ አግባብ ባልተቋቋመ ውል መነሻነት ተዋዋይ ወገን እንዲገደድ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም በእርግጥ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በጽሁፍ ከመደረጉ በተጨማሪ በዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት እስከተደረገ በህግ ፊት ውጤት ያለው ስለሚሆንና ስለማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ከሚመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ. 2879/1/ ሥር ገዢው የገዛውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ሃብትነት በስሙ ለማዛወርና በማይንቀሣቀስ ንብረት መዝገብ ለማግፍ እንዲችል ሻጩ የንብረቱን ሰነድና ማንኛውንም ማስረጃ ሁሉ ሊሰጠው እንደሚገባ ስለተመለከተ ሻጩ ይህንን ግዴታ እንዲወጣ ማስገደድ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግን በአመልካችና በከፊል ተጠሪዎች መሃከል የተደረገው ውል በሕግ ፊት ውጤት ያለው ባለመሆኑ በዚህ ውል መሰረት ተጠሪዎቹ እንዲገደዱ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ግን በስር ፍ/ቤት ክስ መስርተው የነበሩት አመልካች ሲሆኑ ያቀረቡትም የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪዎች ቤቱን የሚመለከቱ ማንኛውም ሰነዶች እንዲያስረክባቸው ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በየትኞቹም ተከራካሪ ወገኖች ውል እንዲፈርስ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ ባለመኖሩ ፍ/ቤቱ በዝርዝር ባልቀረበ ወይም በግልጽ ባልተጠየቀ ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠቱ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 282/2/ የሚቃረን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 17449 በሰኔ 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58180 በጥር 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽለዋል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤት በሥር ከሣሽና ተከሣሾች(በአመልካችና ከ1-3 ባሉት ተጠሪዎች) መሐከል የተደረገው ውል ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው የውሣኔ ክፍል ተሺሯል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይንበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 36280

ጎዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ደምሴ ደበል ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጫላ በዳሶ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሰበር የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ለመዝገብ ቁጥር 978/84 ሐምሌ 9 ቀን 1983 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 07748 ታህሣስ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታለምልኝ በማለት መጋቢት 3 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በከሳሽነት በመቅረብ መስከረም 8 ቀን 1976 ዓ.ም በተባ፩ የሽያጭ ውል በወረዳ 18 ቀበሌ 27 የሚገኘውና ቁጥሩ 018 የሆነው ቤት በብር 55,000(ሃምሣ አምስት ሽህ ብር) በተጠሪ ወኪል አማካኝነት ገዝተው የቅድሚያ ክፍያ ብር 15,000(አስራ አምስት ሺህ) ከከፈሉ በኋላ ቀሪውን ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ በተደጋጋሚ ቢጠይቁ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ስለዚህ ቀሪውን ብር

40,000(አርባ ሺህ) የገደብ መቀጫ ብር 5000 (አምስት ሽህ ብር) ከጥቅምት 20 ቀን 1976 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ያቀረበው ክስ ነው፡፡

ተጠሪ በውሉ ላይ ያልፈረምኩ ስለሆነ ልገደድ አይገባም የውሉ ላይ ያለው የገዥ ፊርማ የእኔ ወኪል ፊርማ አለመሆኑ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክፍል ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በውሉ የምገደድበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ ጋር ውል አለኝ በማለት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ ወኪል ፊርማ አለመሆኑ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ የተረጋገጠ በመሆኑ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል ተፈጽሟል ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ስለዚህ ቀሪ ክፍያ ይከፈለኝ በማለት ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በበኩሉ የቤት ሽያጭ ውል ለማስረዳት ያቀረበው ሰነድ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 በውልና ማስረጃ ፊት ያልተደረገ በመሆኑ የሰበር ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21448 በሰጠው ውሣኔ መሰረት ሕጋዊ ውጤት የሌለው ረቂቅ ስለሆነ የአመልካች ይግባኝ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህ ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት አለበት፡፡ ውሉም ውጤት የለውም ከተባለ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1815 መሰረት የቤቱን ምትክ ተጠሪ እንዲያስረክበኝ መወሰን ነበረበት በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የቤት ሽያጭ ውል አልተዋዋልኩም፡፡ ለማስረጃነት ያቀረብኩትም ሐሰተኛ ሰነድ በመሆኑ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ከተጠሪ ጋር የቤት ሽያጭ ውል የተፈፀመ መሆኑንና ቀሪ ክፍያ የቀረባቸው መሆኑን በግልጽ ያቀረቡትን ክስ ለማስረዳት ያቀረቡት የቤት ሽያጭ ውል ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ ወይም የተጠሪ ወኪል አለመሆኑ በፖሊስ የምርመራ ክፍል ተረጋግጧል ከዚህም የምንረዳው አመልካች በእኔና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ በማለት ያቀረቡትን ክስ ለማስረዳት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2007 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተቃውሞ የቀረበበትና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2008 መሰረት ተመርምሮ በሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ ወይም ወኪል አለመሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ያልፈረመበት ተአማኒነት የሌለው የውል ሰነድ በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መወሰኑ ምንም አይነት የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

በሌላ በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ጭብጥ አድርጐ በመያዝ ውሣኔ የሰጠው ተጠሪ በውሉ ላይ በወኪሉ አመካኝነት በመፈረም የውል ግዴታ ውስጥ ገብቷል ወይስ አልገባም የሚለውን ነጥብ ሆኖ እያለና አመልካችም ይግባኝ ያቀረቡት የተጠሪ ወኪል በውሉ ላይ አልፈረመም የውሉ ሰነድ ተዓማኒነት የለውም በሚለው ነጥብ ላይ ሆኖ እያለ ከጉዳዩ ጋር ግኑኝነት የሌለውን የሰበር መዝገብ ቁጥር 21448 በመጥቀስና በተጠሪዎች በኩል በመቃወሚያነት ያልተነሳውን የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 በመጥቀስ ወስኗል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ የደረሰበት መደምደሚያ የሚነቀፍ ባይሆንም በመዝገቡ የጠቀሰው የሰበር መዝገብ ውስጥ የተሰጠው የህግ ትርጉም በዚህ ጉዳይ የማይሰራና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 በተከራካሪዎች የመቃወሚያ ነጥብ

ሆኖ ባልተነሳበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ራሱ ማንሳቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ የተስማማበትና በወኪሉ አመካኝንት የውል ግዴታ የገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑና የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ታአማኒነት የሌለው መሆኑ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ስለተረጋገጠ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ የሽያጭ ውል መኖሩ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የሕግ ምክንያትና ትንታኔ አሻሽለን በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ምክንያትና ትንታኔ ተሻሽሏል፡፡ ግልባጩ ይተላለፍ፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡ ግልባጩ ይተላለፍ፡፡
3. አመልካች ተጠሪ ቀሪ የቤት ዋጋ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት ኅዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 36496

ጎዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉ አወቀ - ጠበቃ አለልኝ ምህረቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ በላይ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሺያጭ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች መስከረም 30 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ በአሁኗ ተጠሪ ላይ በሰሜን ጐንደር አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም ተጠሪ ጥቅምት 11 ቀን 1991 ዓ.ም በተፃፈ ውል ጐንደር ከተማ ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 242 የቦታ ስፋት 106. 76 ካ.ሜ የካርታ ቁጥር 5715/85 የሆነውን ቤትና ቦታ በብር 30,000.00/ሰላሳ ሺህ ብር/ ሸጠውላቸው ስመ ንብረቱን ያላዞሩላቸው መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ስመ ንብረቱን እንዲያዛወሩ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪም በተከሣሽነታቸው ቀርበው የቀረቡት የከሣሽ ማስረጃዎች የሚያሣዩት ውሉ ከመፈጸሙ በፊት ስለአከፋፈሉ ሁኔታ ስምምነት መደረጉን በመሆኑ ስምምነት ሣይኖር ክፍያ መፈጸም ስለማይቻል የከሣሽ የመክሰስ መብት የሌለ መሆኑና ውሉን ተገደው ለመፈጸምም በይርጋ የሚቋረጥ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብነት፣በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ ከሣሽ ጋር የፈፀሙት

https://chilot.me

ውል አለመኖሩን አለ ቢባል እንኳ ከሣሽ መክፈል የነበረባቸውን ቀሪ ገንዘብ ከፍለው ሣይጨርሱ የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ ማቅረባቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑንና ውሉም በፍ/ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውልን ለማማዋል ስልጣን በተጠሰው ፊት የተደረገ ባለመሆኑ በሕግ ፊት የሚፀና አለመሆኑንና ከከሣሽ የተቀበሉትን ብር 11,000.00 /አስራ አንድ ሺህ ብር/ ለመመለስ ፈቃደኛ ስለሆኑ ውሉ ቀሪ ሁኖ ገንዘቡን ለከሣሽ እንዲመልሱ ይደረግላቸው ዘንድ ዳኝነት በመጠየቅ መከራከራቸውን የሚያሣዩትን ነጥቦችን አንስተው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማና ጥቅምት 11 ቀን 1988 ዓ.ም የቤት ሽያጭ ውል መደረጉን የሚያሳይ ዋናውን ኮፒ ከአስቀረበ በኋላ በተጠሪ በኩል የቀረቡትን መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ በማድረግ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል የተፈፀመ በመሆኑ በሽያጭ ውሉ መሰረት የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤትና ቦታ ተጠሪ በአመልካች ስም ሊያዛውሩ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኗ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይሕው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለፍ/ሕ/ቁ. 1723 የሰጠውን ትርጓሜ በምክንያትነት በመጥቀስ በግራ ቀኙ መካከል በሕግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል የለም ወደሚል ድምዳሜ በመድረስ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የቤቱን ስመንብረት ተጠሪ ለአመልካች የማዛወር አላፊነት የለባቸውም በማለት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ መጋቢት 12 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ያሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- የሽያጭ ውሉ ከተደረገ በርካታ ጊዜያት ያስቆጠረ ከመሆኑም በላይ ግዴታቸውን ያልተወጡት ተጠሪ መሆኑ እየታወቀ የውሉ

https://chilot.me
አብዛኛው ክፍል በተፈፀመበት ሁኔታ የሰበር ችሎቱ ውሣኔ የላግባብ ተይዞ የአካባቢውን ወግና ባሕል እንደሁም በግራ ቀኙ መካከል ያለውን መተማመን ባላገናዘበ ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ የተጠሪ ወኪል ቀርበው ግንቦት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ በመልሣቸውም በሕግ ፊት የሚፀና ውል አለመኖሩን ከቤቱ የሽያጭ ገንዘብ የተከፈለው ብር 11,000.00 (አስራ አንድ ሺህ) ብቻ ሁኖ አመልካች ጠቅላላውን ገንዘብ ከፈልኩት ለሚሉት ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ተጠሪ ለአመልካች ያላስከረከ ከመሆኑም በላይ ቤቱ የተጠሪ ብቻ ሣይሆን የሌሎች ሰዎችም የጋራ ሐብት መሆኑን፣በቦታው ላይ አመልካች የገነቡት ግንብታም ሕገ ወጥ መሆኑንና ግንባታው በመንገድ ማስፋት ምክንያት በከፊል ፈርሶ ካሣውን ተጠሪ መቀበላቸውም ሕጋዊ ባለቤት አመልካች አለመሆናቸውን የሚያሳይ መሆኑንና በውሉ መሰረት ተጠሪ የፈፀመችው ግዴታ አለመኖሩን በማንሣት የአመልካች የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሁኖ ሊወሰን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ሰኔ 18 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ የተጠሪ ወኪል ያነሷቸው መከራከሪያ ነጥቦች ተቀባይነት የሌላቸው፣ከፊሎቹም በስር ያልተነሱና እዚህ ሰበር ችሎት ሊነሱ የማይገባ መሆናቸውን በመዘርዘር እና የሰበር አቤቱታቻውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በስር ፍ/ቤት አመልካች በቤት ሽያጭ ውል መሰረት ስመ ንብረት እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት በግልጽ ጠይቀው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት

https://chilot.me
የፍ/ሕ/ቁ. 1723/1/ን መሰረት በማድረግ በሕግ ፊት ሊፀና የሚችል የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ቤት ለአመልካች መሸጣቸውን በግልጽ ክደው አለመከራከራቸውን ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች የተቀበሉትን ብር 11,000.00(አስራ አንድ ሺህ) መልሰው ውሉ ቀሪ ነው እንዲባልላቸው በመግለጽ መከራከራቸው በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ውል መኖሩን አምነው የሚከራከሩ መሆናቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ተጠሪ የቤት ሽያጭ ውሉ የሕጉን ፎርም የማያሟላ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለት በሕጉ አግባብ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ያለመኖሩን የክርክሩ ሂደት ያስገነዝባል፡፡

በመሆኑም ተጠሪ የውሉን መኖር በግልጽ ባልካዱበት ሁኔታ እና የውሉን ፎርማሊቲ አስመልክቶ በሕጉ አግባብ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ባላቀረቡት የክርክር ሂደት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ሕ/ቁ. 1723/1/ ን መሰረት በማድረግ በሕግ ፊት የሚፀና የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት መወሰኑ የሕግ መሰረት የለውም፡፡ የቤት ሽያጭ ውል ስለመኖሩ በግራ ቀኙ መካከል በግልጽ መካካድ በሌለበት ሁኔታ ፍ/ቤት የፍ/ሕ/ቁ. 1723/1/ ን በመጥቀስ ውሣኔ መስጠት ተከራካሪዎች ጭብጥ ያላደረጉትን ጉዳይ በጭብጥነት ይዞ እንደመወሰን የሚቆጠር ሲሆን ይህ ደግሞ ከፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246-248 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ተቀባይነት የሌለው የፍትሐብሔር ጉዳይ ክርክር አመራር ነው፡፡

የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤትና ቦታ ሽያጭ ስመ ንብረት እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ነው፡፡ አመልካች ከስር ፍ/ቤት ጀምረው እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጥብቀው የሚከራከሩት ቤቱን በመረከብ እየተጠቀሙ የሚገኙ መሆኑን በተጠሪ በኩል ሊፈጸም የሚገባውና የቀረው ጉዳይ ስመ ንብረቱን ማዞር ብቻ

https://chilot.me
መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ ደግሞ የሚከናወነው/የሚስተናገደው/ በመንግስት አስተዳደር ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም ሻጭ ነው የተባለው ወገን የሚፈጽመው የውልም ሆነ የሕግ ግዴታ ያለበት ጉዳይ ተደርጐ የሚወሰድ አይደለም፡፡ የመንግስት አስተዳደር ክፍል የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሐብትነት በማወቅ ለአንድ ሰው የባሐብትነት የምስክር ወረቀት የሚሰጥ አካል ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1195/1/ በግልጽ ደንግጓል፡፡ ይህንኑ የስራ ድርሻ የሚያከናውነውም አስፈላጊ የውልም ሆነ የሕግ ሰነዶች ሲቀርቡለት መሆኑ ይታመናል፡፡ ከዚህም አኳያ የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዝቼአለሁ የሚል ወገን ይህንኑ ንብረት የሚመለከት አለኝ የሚለውን ውልና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን በመያዝ ለሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል በማቅረብ የንብረቱን ግዥ እንዲያውቅለትና ስመሃብቱን የሚያሣይ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ከዚህ መብት ውጪ ሻጩን የውል ወይም የሕግ ግዴታ አለበት በማለት የስም ዝውውሩን እንዲፈጽም ለመክሰስ የሚያስችል የክስ ምክንያት አይኖርም በከሣሽ የክስ አቤቱታ ላይ የተገለፀው ፍሬ ነገር የማያስከስስ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ክሱ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231/1ሀ/ ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ክሱ ውድቅ መደረግ ሲገባው የስር ፍ/ቤት በሽያጭ ውሉ መሰረት ተጠሪ የስም ዝውውሩን ሊፈጽሙ ይገባል ማለቱ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማረም በክሱ አቤቱታ የተገለፀው ፍሬ ነገር የማያስከስስ ነው በማለት መወሰን ሲገባው የውሉ መኖር በግልጽ ባልተካደበት ሁኔታ ስለውሉ ፎርማሊቲ በማንሣት ውል የለም ሲል መደምደሙ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ የውሉን መኖር በግልጽ ስላልካዱና በግልጽ ያልተካደ ነገር ደግሞ እንደታመነ የሚቆጠር ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 83 እና 235/1/ ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለሚያስገነዝቡ የሽያጭ ውል የለም መባሉ ያላግባብ ነው፡፡

https://chilot.me
ይሁን እንጂ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ወይም ስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ውድቅ መሆን የነበረበት ነው ተብሎ መወሰን የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚም መሰረት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13988 የካቲት 04 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጐንደር አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16926 ሐምሌ 19 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የስም ዝውውሩ በተጠሪ ሊፈጸም ይገባል ሲል የሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
3. የአመልካች የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ ሻጭ የሆኑትን ተጠሪ የሚያስከስስ የክስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሐሳብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አስብሎ በሰጠው ውሣኔ የምስማማ፣ሲሆን በሌላ በኩል አመልካች የቤቱ ስመ ንብረት እንዲዛወርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም በማለት በሰጠው ውሣኔና በደረሰበት መደምደሚያ ባለመስማማት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

https://chilot.me

አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት በውል፣ የገዛ ሰው ሻጩ የቤቱን የባለቤትነት መብት እንዲያስተላልፍለት የሚያቀርበው ጥያቄ በቂ የሆነ የሕግ ድጋፍና የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው በውል የገባውን ግዴታ የሚወጣው ምን ምን ተግባራትን በመፈጸም እንደሆነና በአገራችን የማይንቀሣቀስ ንብረት ባቤትነት ከአንዱ ወደ ሌላው ማዛወር የአስተዳደር አካላት እንዲሚሉ ከሚጠይቋቸው ሁኔታዎች ጋር በአንድነት መመዘንና መመርመር ይገባቸዋል፡፡ የሚል እምነት አለኝ፡፡

1. የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው በውል የገባውን ግዴታ ለመፈፀም ምን ምን ተግባራት የማከናወን ግዴታና ኃላፊነት እንዳለበት ለመረዳት ይህንኑ በማስመልከት ተፈፃሚነት ያላቸውን የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የተደነገገውን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2876 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2895 የተደነገጉት ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ የሚመራው የፍታብሔር ሕጉ የአንድን ነገር ባለሐብትነት ማስተላለፍን ስለሚመለከቱ ውሎች በተደነገገው አንቀጽ በተመለከተው ደንብ መሰረት እንደሆነ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 ይደነግጋል፡፡

   ሕግ አውጭው የማይንቀሣቀስ ንብረት ያለውን ልዩ ባህሪና የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነትን በሽያጭ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ ሊደረጉ የሚችሉ የተለያዩ አይነት የሽያጭ ውሎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እነዚህን ልዩ ሁኔታዎች ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ልዩ የሆኑ ደንቦችን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2876 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2895 ደንግጓል፡፡ እነዚህ ልዩ ድንጋጌዎች የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭን አስመልክቶ ልዩ ትኩረት የሚሹና የተለየ ደንብ እና ሥርአት ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችን የሚቆጣጠሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ

https://chilot.me
የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ሲፈጸም የሻያጭና የገዥውን ግዴታና ሐላፊነት በተሟላ ሁኔታ የሚዘረዝሩና የሚደነግጉ አይደሉም፡፡

ስለሆነም የማይንቀሣቀስ ንብረት ሲሸጥ የሽያጩንና የገዥውን ዝርዝር ግዴታና ሐላፊነት ለመረዳት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 በተደነገገው መርህ መሰረት በፍታብሔር ሕጉ አምስተኛ መጽሐፍ ስለሽያጭ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መመርመርና እንደ አግብብነታቸው ተፈፃሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ መሰረታዊ መርህ በመነሳት የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ግዴታና ሐላፊነት ስንመዝነው የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው በዋነኛነት

- የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ሙሉ በሙሉ ለገዥ የማስረከብ
- የሸጠውን የማይነቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት ለገዥው ያማዛወርና
- በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ ለሚገኙ አንድ አንድ ጉድለቶች

ዋቢ የመሆን ግዴታ እንዳለበት ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2273 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው በሽያጭ ውሉ መሰረት ግዴታውን ተወጥቷል ለማለት የሚቻለው በፍትብሔር ሕግ ቁጥር 2879/1/ በተደነገገው መሰረት የማይንቀሣቀስ ንብረት የሚመለከቱ ሰነዶች ለገዥ በመስጠቱ ብቻ ሣይሆን የማይንቀሣቀሰውን ንብረት ባለሐብትነት ለገዥው ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን በተሟላ ሁኔታና በትጋት ሲወጣ ጭምር ነው፡፡ ይህ የሽያጭ መሰረታዊ ግዴታና ሐላፊነት እንደሆነ ሕግ አውጭው ግልጽና አስገዳጅ በሆነ መንገድ “ሻጩ የሸጠውን ነገር የማያስነካ መብት ለገዥው ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ለመፈጸም ግዴታ አለበት” በሚል መንገድ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2281 በግልጽ ደንግጓል፡፡ ከዚህም የምንረዳው የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው የፍትብሔር ሕግ ቁጥር 2274 በሚደነግገው መሰረት ንብረቱን ለገዥ ለማስረከቡና በፍታብሔር ሕግ

https://chilot.me

ቁጥር 2879 ድንግጌዎች መሰረት የማይንቀሣቀሰውን ንብረት የሚመለከቱ ሰነዶችና ማስረጃዎች ለገዥ በመስጠቱ ብቻ በሽያጭ ውሉ መሰረት ግዴታና ሐላፊነቱን ተወጥቷል ብሎ ለመደምደም የማይቻል መሆኑንና ከዚህ ተግባራት በተጨማሪ ሽያጭ የማይንቀሣቀሰውን ንብረት ባለሐብተነት ለገዥው ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ በእሱ በኩል መፈፀም ያለባቸው ሌሎች ተግባራትን የመፈጸም ግዴታና ሐላፊነት ያለበት መሆኑን ነው፡፡

2. ይህንን መሰረትዊ ጉዳይ በመያዝ ወደ ሁለተኛው ነጥብ ስንሸጋገር በአገራችን በውል አዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት ያልተደረገን የቤት ሽያጭ ውል መሰረት በማድረግ የንብረቱን ባለሐብትነት ከሽያጭ ወደ ገዥ ለማዛወርና ለማስተላለፍ የአስተዳደር አካላት እንደሚሉት የሚጠይቋቸው ሁኔታዎች በተለይም በሽያጭ በኩል እንዲፈፀም የሚፈልጉት ቀሪ ተግባራት ምንድን ናቸው የሚለውን በውል መመርመርና ማየት ያስፈልጋል፡፡ ስልጣን ያለው የአስተዳደር አካል በሽያጩ ስም የነበረውን የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በመሰረዝ በገዥው ስም የማይንቀሣቀሰውን ባለሐብትነት የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት ደንብና ሥርአት በአስተዳደር ክፍል ደንብና የአሰራር መመሪያ የሚወሰን ስለመሆኑ በፍትብሔር ሕግ ቁጥር 1195 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡

በአማራ ክልል የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች (የጎንደር ከተማ አስተዳደር) ጭምር የቤት ሽያጭ ውል የተፈጸመው በውል አዋዋይ ወይም በዳኞች ፊት ባለሆነ ጊዜ ገዥ የውል ሰዱንና የንብረቱን ባለሐብትነት የሚመለከቱ ሻጭ የሰጠውን ሰነዶችና ማስረጃዎች ይዞ በመቅረቡ ብቻ የቤቱን ባለሐብትነት በሽያጭ ወደ ገዥ የማያዛውሩ መሆኑንና በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የቀረበውን የሽያጭ ውል ትክክለኛና ታአማኒነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥና ሻጭ በእርግጥ ቤቱን

https://chilot.me

ለገዥ የሸጠ መሆኑን ለመረዳት ሻጩ ወይም ለዚህ ተግባር የወከለው ሰው በግንባር በመቅረብ ንብረቱን ለገዥ የሸጠ መሆኑን ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው የስም ማዛወሪያና የባለቤትነት ማስተላለፊያ ቅጽ ላይ በመፈረም የሽያጭ ውሉን የፈፀመ መሆኑን እንዲያረጋግጥ እንደሚጠይቁ በአማራ ክልል ያሉ የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች አሰራር ደጥብ በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሽያጭ ወይም ለዚሁ ተግባር በሸያጭ የተወከለው ሰው ይህንን ተግባር ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆኑ ገዥ በሕጋዊ መንገድ የቤቱን የገዛ መሆኑን እና በውሉ መሰረት አስፈላጊ የሆኑ አስተዳደራዊ ተግባራት እንዲፈጸሙለት የፍርድ ቤት ውሣኔ ወይም ትእዛዝ እንዲያቀርብላቸው የአስተዳደር አካላቱ የሚጠይቁ መሆኑን የከተማ አስተዳደሮች እና ማዘጋጃ ቤቶችን የአሰራር መመሪያ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ክርክሩ የተነሳበት ቤት የሚገኝበት የጐንደር ከተማ አስተዳደር እና በሌሎች ከተሞች የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሐብትነት ከሸያጭ ወደ ገዥ የሚያዛውሩት ሽያጭ ቀርቦ በስም ማዛወሪያ ቅጽ ላይ በመፈረሙ ብቻም አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሽያጭ ቤቱን እና ሌሎች ግንባታዎችን የገነባው የከተማ አስተዳደር በሰጠው ቦታና ባገኘው የግንባታ ፈቃድ መሆኑ በባለሙያ በማሣየት ማረጋገጫ ሲያቀርብ ሽያጭ መክፈል የሚገባውን የቦታ ግብር የጣሪያ ግብር የሊዝ ክራይ ዋጋ እና በከተማው አስተዳደር ፈቃድ ውጭ የሰራው ግንባታ ካለ ያለፈቃድ በመሥራቱ መክፈል የሚገባውን የመቀጫ ገንዘብ አጠቃልሎ የከፈለ መሆኑን ከሚመለከታቸው አካላት ማስረጃና ማረጋገጫ ሲያቀርብና በአጠቃላይ የተሸጠው ቤት ከማናቸውም እዳና እግድ ነፃ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን አሟልቶ ሲያቀርብ ነው፡፡

https://chilot.me

ስለሆነም በተግባር እየተፈፀሙ ያሉ ተግባሮችንና የማይንቀሣቀስ ባለሐብትነት ከሺያጭ ወደ ገዥ ለማዛወር የከተማ አስተዳደሮች የሚከተሉትን አሰራር ስንመለከት ሺያጭ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2879 መሰረት የቤትና የቦታውን ካርታና ፕላንና የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለገዥ በመስጠቱና ቤቱን በማስረከቡ ብቻ፣የቤቱን ባለሐብትነት ከሽያጭ ወደገዥ ለማዛወር የሚያስፈልጉ አስፈላጊ ተግባራትን በተሟላ ሁኔታ ተወጥቷል ብሎ ለመደመደም የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስመዘነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሰረት የቤቱን ስመንብረት እንድታዛውርና በውል የገባችውን ግዴታ እንድትፈጽም ይወሰንልኝ በማለት ያቀረባቸው የክስ ማመልከቻ መሰረታዊ ባህሪና ይዘት የቤቱ ሺያጭ የሆነችው ተጠሪ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2281 በሚደነግገው መሰረት ከላይ የዘረዘርኳቸውንና ሌሎች የቤቱን ባለሐብትነት ለማዛወር የሚያስፈልጉ ተግባራትን እንድትፈጽም ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ይስጥልኝ የሚል መሰረታዊ የሆነ የመብት ጥያቄ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

3. የጐንደር ከተማ አስተዳደር በሽያጭ ስም የነበረውን የቤቱን ባቤትነት የምስክር ወረቀት በማስመለስ በገዥ ስም አዲስ የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በቅድሚያ ሽያጭ በተራ ቁጥር 2 የዘረዘርኳቸውን የቤቱን ባለሐብትነት ወደ ገዥ ለማዛወር ማሟላት የሚገባቸውን ሁኔታዎች ሲያሟሉ ነው፡፡ የቤቱን ባለቤትነት ወደ አመልካች የሚዛወረው በመጀመሪያ ተጠሪ ቦታውን ቤቱን እንደዚሁም ሌሎች ግንባታዎች በከተማው ፕላንና በተሰጣቸው የግንባታ የሥራ ፈቃድ መሰረት ያከናወኑ መሆኑን በባለሙያ አሳይተው ማረጋገጫ ሲያቀርቡና በቤቱ ላይ የሚፈለጉ ማናቸውም ውዝፍ ክፍያዎች ከአጠናቅቀው በመክፈል ቤቱ ከማናቸውም እዳና እገዳ ነፃ መሆኑን

https://chilot.me

የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2301 ድንጋጌዎች መሰረት ለአመልካች ሲሰጡ እንደዚሁም በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2281 መሰረት ተጠሪ የሸጠችውን ቤት ባለሐብትነት በማያስነካ ሁኔታ ለአመልካች ለማስተላለፍ ጐንደር ከተማ አስተዳደር በመቅረብ አስተዳደሩ ባዘጋጀው የስም ማዛወሪያ ቅጽ ላይ በመፈረም ግዴታና ሐላፊነቷን ስትወጣ ነው፡፡

ተጠሪ እነዚህን ተግባራት በተሟላ ሁኔታ ያልፈጸመችና ለመፈጸምም ፈቃደኛ ያልሆነች መሆኗን በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር ያሣያል፡፡ የአመልካች ክስና ጥያቄም ተጠሪ እነዚህን የቤቱን ባለሐብትነት ወደ እኔ ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉና የጐንደር ከተማ አስተዳደር በሽያጭ በኩል እንዲሟሉ የሚፈልጋቸውን ሁኔታዎች እንድታሟላ ውሣኔ ይሰጥልኝ የሚልና ይህም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2281 መሰረት የቀረበ ጥያቄ ሆኖ እያለ አብላጫው ድምጽ “አመልካች ያቀረበው የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ ተጠሪን የሚያስከስስ የክስ ምክንያት የለውም” በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ ከዘረዘርኳቸው የከተማ አስተዳደር መኖሪያ ቤት ደንቦችና የሽያጭን ግዴታ የሚዘረዝሩ የፍትብሔር ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ስመዝነው አሳማኝ ሆኖ ስላላገኘሁት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በእኔ እምነት ፍርድ ቤቶች ሺያጭ በውሉ መሰረት ግዴታውን እንዲፈጽምና የቤቱን ባለሐብትነት እንዲያዛውር ትእዛዝ ይሰጥልኝ በሚል መንገድ የሚቀርቡ ክሶችን ተቀብለው ማስተናገድ አለባቸው፡፡ በሽያጭና በገዥ መካከል የሚደረገውንም ክርክር በመስማት ሺያጭ ቤቱን ለገዥ ከማስረከብና የቤቱን ባለሐብትነት የሚያረጋጋጡ ሰነዶችን ለገዥ መስጠቱ ብቻ ሣይሆን የቤቱን ስመንብረት ለገዥ ለማስተላለፍ አስተዳደር አካላት በሽያጭ በኩል እንዲፈፀሙ የሚጠይቁትን ሌሎች ተግባራት በትጋት የፈፀሙ መሆኑን መመርመርና የቤቱን ባቤትነት ወደ ገዥ ለማስተላለፍ መፈፀም የሚገባቸውን ማናቸውም አስፈላጊ ተግባራት ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆኑ ሽያጭዎች

https://chilot.me

በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2281 መሰረት ይህንን ግዴታና ሐላፊነታቸውን እንዲወጡ ውሣኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ ከወዲሁ የክስ ምክንያት የለውም በሚል መንገድ ውድቅ የሚያደርጉ ከሆነ የቤት ሽያጭ ውልን በማስፈፀም በተለይም የቤትን ባለሐብትነት ከሽያጭ ወደ ገዥ የማስተላለፍ ሒደት ውስጥ ግዴታቸውን ለመወጣት ፈቃደኛ በማይሆኑ ሽያጮች እንዲስተጓጐልና ጉዳዩ በእንጥልጥል እንዲቀር ክፍተት የሚፈጠርበት ሁኔታ ይኖርል ብየ አስባለሁ፡፡

ስለሆነም አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በገባችው የቤት ሽያጭ ውል መሰረት እንድትፈጽምና የቤቱን ባለሐብትነት እንድታዛውር ውሣኔ ይሰጥልኝ በሚል መልክ ያቀረበችው ጥያቄ ከላይ ከዘረዘረኩት መሰረታዊ ሐሳብ አንፃር መታየት ይኖርበታል፡፡ ይኸ የአመልካች ጥቄም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 መሰረት በማድረግ ተጠሪ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2273 ንኡስ አንቀጽ 2 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2301 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2281 በተደነገገው መሰረት ስመንብረቱን ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተገባራትን እንድትፈጽም በፍርድ ታይቶ እንዲወሰንላት ያቀረበችው ጥያቄ በመሆኑ ተጠሪን የሚያስከስስ በቂ የሆነ የክስ ምክንያት አለው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ለአመልካች የሸጠችውን ቤት ባሐብትነት ለአመልካች ለማዛወር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ግዴታና ሐላፊነት አለባቸው በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 36505

ኅዳር 4 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃደር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ባዩሽ ክፍሌ - ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ብርሌ ቢምር ቀርበዋል

2. ወ/ሮ አስካለ ሽንቁጤ ወኪል ነኝ በማለት 1ኛ ተጠሪ ቀርበዋል

ጉዳዩ ለምርመራ በተቀጠረው መሰረት ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተንበታል፡-

ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 34261 ኅዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 61882፣ታህሳስ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል በሚል ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤቱ ከሳሽ፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ይግባኝ ባይ ሆነው እየተከራከሩ የመጡ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ በስር ፍርድ ቤቱ ተከሳሾች በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ደግሞ መልስ ሰጭዎች በመሆን እየተከራከሩ የመጡ ናቸው፡፡

የአሁኑ አመልካች ጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘቱ ተከሳሾች ቤት ሸጠውልኝ ሲያበቁ በሚመለከተው አካል ቀርበው ቤቱን በስሜ ሊያዛውሩልኝ ስላልቻሉ የቤቱን ስመ ርስት በስሜ እንዲያዛውሩልኝ ይወሰንልኝ ወጪና ኪሳራም ሊከፍሉኝ ይገባል የሚል ሲሆን ተከሳሾችም የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው ቤቱን መሸጣቸው አምነው ቤቱ በስማቸው ላለማዛወር አንቅፋት የሆኑት ከሳሽ ራሳቸው እንጂ ተከሳሾች እንዳልሆኑ ገልጸዋል፡፡

አከራካሪው ቤት ይገኝበታል የተባለው የክፍለ ከተማው መሬት አስተዳደር ተጠይቆ በሰጠው መልስ ከሳሽ ገዛሁ የሚሉት የመሬት ስፋት 300 ካ.ሜ ሲሆን ይህንንም ተከሳሾች ካላቸው ጠቀላላ የቦታ ስፋት 419 ሜ.ካ ውስጥ ቀንሰው የሸጡላቸው በመሆኑ በአፈፃፀሙ ረገድ ግን ቀሪው 119 ካ.ሜ ስለሚሆንና ሕጋዊ ካርታ ለመስጠት ግን ከ150 ካ.ሜ ማነስ ስለማይገባው በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የተፈፀመውን ውል መሰረት በማድረግ የስም ማዛወሩ ተግባር ለመፈጸም እንዳልቻለ አረጋግጧል፡፡

የፌዴራል ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም ከሳሽ በዚህ ነጥብ ላይ በተከሳሾች ክስ የማቅረብ መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚል ጭብጥ በመያዝ በፍ/ብ/መ/ቁ. 34261 ኅዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሰረት ውልን ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ቀርቦ እንዳልተመዘገበ ወይም ደግሞ በፍርድ ቤት ፊት የተፈፀመ ባለመሆኑ በተለይም ደግሞ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መሬት በዚህ መልክ ውል መፈፀሙ ሕጋዊነት እንደሌለውና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ. 21448 በሰጠው ትርጉም የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት ሊሆን ስለማይችልና አስፈላጊ ከሆነም ጥያቄው ወደ ሚመለከተው የመሬት አስተዳደር አካል

በቀጥታ መቅረብ ያለበት በመሆኑ ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ጥያቄያቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 33/2/ መሰረት ውድቅ አድርጓል።

ከላይ የተቀመጠውን ፍርድ በመቃወም ስር ከሳሽ የነበሩት ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በኮ/ቁ. 61882 ታህሳስ 23 ቀን 2000 ዓ.ም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል።

የሥር ፍርድ ቤቶቹ ውሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው በማለትም አመልካች የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሕጋዊና ግራ ቀኙ ወገኖች የተማመኑበት ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቱ በክርክር ያልቀረበለት ጭብጥ በማንሳት ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሰረት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ አተረጓጎም ስህተት ነው፤ በውላችን መሰረት ቦታው አስረክበውኝ ከ300,000 ብር (ሦስት መቶ ሺህ ብር) በላይ ተጨማሪ ወጪ አፍሰሽበት ቤቱ ለብዙ ቤተሰቦቼ መኖሪያነት ውሏል፤ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶቹ ውሳኔዎች መስረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆናቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/መሰረት ተሽረው የስም ዝውውሩ እንዲፈፀም ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው የሚጠይቅ ነው።

ተጠሪዎችም ግንቦት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው ጥቅምት 20 ቀን 1997 ዓ.ም እና ጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፉ ውል በየካ ክፍል ከተማ፣ቀበሌ 19 የሚገኘውን በካርታ ቁጥር 147/1605/11/1371 የሚታወቀውን ቁጥር 636 የሆነውን ቤታቸውን ለአመልካች መሸጣችን አይካድም፤ ካርታውም ሰጥተናቸው በሲሚንቶ ማውጫ ስላስያዙት ክፍለ ከተማ በፈለገው ወቅት ሊያቀርቡት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ከፍለ ከተማውም መመሪያ እንደማይፈቅድለት በመግለጽ ካርታውን

ሳይቆርጥልን ቀርቷል፣በእኛ በኩል የተፈፀመ ስህተት የለም፤የውሉ ሕጋዊነት በተለይም ካርታው በስማቸው ለማዘጋጀት የሚቻል መሆኑን አለመሆኑን ሳያጣሩ አስቀድመው በቦታው ላይ ከፍተኛ ወጪ ማፍሰሳቸው የራሳቸው ስህተት ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶቹ ሕግን ተከትለው የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ማለታቸው ትክክል ስላለልሆነ ከሚመለከተው አካል ክርክራቸውን ቢቀጥሉ የተሻለ በመግለጽ ከቀረበባቸው ክስ እንዲሰናበቱ ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልሳቸው የክፍለ ከተማው መሬት አስተዳደር በሌሎች ጉዳዮች በ100 ካ.ሜ እና በ74 ካ.ሜ የቦታ ስፋት ካርታ እያዘጋጀ ለተጠቃሚዎች ካርታ በተግባር እየሰጠ እንደሆነ የሚታወቅ ሆኖ በአሁኑ አከራካሪ ቤት በ119 ካ.ሜ እና በ300 ካ.ሜ የቦታ ስፋቶች ካርታ እንዳላዘጋጅ አሰራር ይከለክለኛል ማለቱ ከእውነት የራቀ በመሆኑ ስም እንዲያዛውር ይገደድልኝ ካሉት ሐሳብ ውጭ ሌላው በአቤቱታቸው ከዘረዘሩት ተመሳሳይ ስለሆነ ደግሞ ከመዘርዘር ታልፏል፡፡

እንግዲህ የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ እንደመጣው ሆኖ ይህ ችሎትም፡-

1. በተከራካሪ ወገኖች በቤት ሽያጩ ውል መተማመን እያለና መከራከሪያ ነጥብ ሆኖ ሳይቀርብለት በራሱ አነሳሽነት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 በማንሳት በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የቤት ሽያጭ ውል የለም ማለቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?
2. በዚህ ክርክር የቤቱ ስም በስማቸው እንዲዛወርላቸው አመልካች እያቀረቡት ያለው ጥያቄ ተገቢነት አለው ወይስ የለውም? ቤቱ የሚገኝበት የመሬት

አስተዳደር አካል በዚህ መዝገብ ተገድዶ የቦታው ስም በአመልካች እንዲመዘገብ ማስገደድ ይቻላል ወይስ አይቻልም?

የሚሉትን ጭብጦች በመመስረት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርመሯል፡-

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በተከራካሪ ወገኖቹ መካከል የአከራካሪው ቤት ሽያጭ ማከናወናቸው ተማምነውና ቤቱንም ወደ ገዥ(አመልካች) አስረክበው እያለ የስር ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሰረት ሊፀና የሚገባው አይደለም ብሎ ማጠቃለሉ ሲታይ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 አላማ የሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ. 21448 ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትርጉም በተዋዋይ ወገኖች መካከል በህግ ፊት የሚጸና ውል እንዲኖር ለማድረግ ነው፤ስለሆነም ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አንቀጽ የተፈፀመን ጉድለት መሰረት አድርገው ራሳቻውን የመከላከል መብታቸውን በተውበት አኳኋን ሌላ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው የሚገባ ውሉን ተቀባይነት የሚያስገኝ ሁኔታ በሌለበት በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በውል አዋዋይ ያልተመዘገበ ወይም በፍርድ ቤት ፊት ያልተፈፀመ ነው በማለት ውሉን ውድቅ ማድረጉ ተገቢነት የለውም፤ የውሉ ይፍረስልኝ ጥያቄ ባልቀረበለት ሁኔታ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ትርጉም በዚህ ክርክር በቀጥታ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ያልሆነ ምክንያት በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች እንዲሸጡላቸው ያመኑና የቤቱም ካርታ ለገዥ እንዳስረከቡ በተለይም ደግሞ አከራካሪው ቦታ ለገዢው ቀርሰው እንዳስረከቧቸውና ገዢም (አመልካች) በገዙት ቤት ላይ ተጨማሪ ወጪ አውጥተው እየተጠቀሙበት እንደሚገኝ ከክርክሩ መረዳት ይቻላል፤ይህ የሚያሳያው ደግሞ ተጠሪዎች በእነሱ ዘንድ የሚፈለግባቸውን ግዴታዎች እንደተወጡ ነው፤ከዚህ የቀረ ነገር ቢኖር አመልካች የቤቱ ስም ወደ እርሳቸው እንዲዛወርላቸው

የሚመለከተውን አካል በጠየቁበት ጊዜ የቦታና ቤት ስም የማዛወርን አሰራር መመዘኛዎች አላሟላም በማለት በአመልካች ስም ያለማዛወሩ ነው። ተጠሪዎች ከእነሱ የሚፈለጉባቸውን ሰነዶች በቅንነት ለአመልካች እስካስረከቡ ድረስ ስም ተገድደው ሊያዛውሩልኝ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት ያለው ነጥብ አይደለም፤ይህንንም ጭብጥ የሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ. 21792 ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ትርጉም የሰጠበት ነው፤ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶቹ ይህንንም ትርጉም እንደ ምክንያት በመውሰድ አመልካች የአከራካሪው ቤት ስም ተጠሪዎች በስማቸው ተገድደው እንዲያዛውሩላቸው የመጠየቃቸው አግባብነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ መሰረት የክስ ምክንያት የላቸውም በማለት ክሳቸውን ውድቅ ማድረጋቸው ትክክለኛ በመሆኑና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፤አከራካሪው ቤት የሚገኝበት የመሬት አስተዳደር አካል ተገድዶ ስም ይዛውርልኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ሲታይም ከመጀመሪያውኑ በዚሁ አካል ላይ ያቀረቡት ክስ በሌለበት ሁኔታ ይህንን ጥያቄ ማስተናገዱ አግባብነት ያለው ባለመሆኑ ከዚህ አኳያ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አልተቀበላቸውም።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 34261፣ኅዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61882 ታህሳስ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ ምክንያታቸውን በማሻሻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ፀንቷል፤ ይፃፍ።
2. በአከራካሪው የቤት ሽያጭ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የሽያጭ ውሉ በማድረጋቸውን እየተማመኑ ባሉበትና የውሉ ይፍረስልኝ ጥያቄ በተጠሪ

ባልቀረበበት ሁኔታ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሰረት በማድረግ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚፀና ውል የለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ምክንያት ተገቢነት የለውም፡፡ ይሁን እንጂ አከራካሪውን የቤት ሽያጭ መዋዋላቸው አምነው ቤቱንና ካርታውን ተጠሪዎች ለአመልካች አስረክበው ባሉበት ሁኔታ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የተገደው ስም ያዛውሩልኝ ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ መሰረት የክስ ምክንያት የለውም ማለታቸው በአግባቡ ስለሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀብሎታል፡፡

3. አመልካች በሚመለከተው የመሬት አስተዳደር አካል ያቀረቡት ክስ በሌለበት ሁኔታ ተገድዶ ስም እንዲያዛውርልኝ ይታዘዝልኝ ማለታቸው አግባባነት ስለሌለው ይህ ፍርድ ቤት ጥያቄያቸውን አልተቀበለውም፤
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ችሎት ባደረጉት ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፤ ክርክሩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 36575

ኅዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ደራ አስፋው ቀረቡ፡፡

መልስ ሰጪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ማረኝ አልቀረቡም፡፡

መልስ ሰጪ አድራሻቸው በውል ተለይቶ የማይታወቅ በመሆኑ የተካሣ መጥሪያውን ለማድረስ እንዳልቻሉ አመልካች በቃለ መሐላ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ለመልስ ሰጭ ጥሪው በምትክ መጥሪያ /በጋዜጣ/ ተደርጓላቸዋል ይሁን እንጂ አልቀረቡም፡፡ ስለሆነም በጥሪው መሠረት መቅረብ ባለመቻላቸው በሰበር ደረጃ የጽሁፍ ክርክር የማቅረብ መብታቸው የታለፈ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡንም መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነቱ በመ/ቁ. 03263 የካቲት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት የአሁን አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

ጉዳዩም በአጭሩ እንደሚተለው ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭ በድሬደዋ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ ሆነው ባለቤቴን ለማስታማም ወደ አዲስ አበባ በሄድኩበት ወቅት ከባለቤቴ ጋር በጥገኝነት ይኖር የነበረው የአሁን አመልካች ቤቱንና በቤቱ ውስጥ የነበሩትን ዕቃዎች በያዝ ለመልቀቅ

ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለሆነም ቤቱንና የቤት ቁሳቁሶችንም እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

በሰበር ደረጃ ክርክር ያስነሳውን የቤቱን ይዞታ በሚመለከት የአሁን አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ቤቱን በይዞታ ያደረገው የቤቱ ባለቤት ከሆነው ከእራሱ ቀበሌ ጋር ባደረገው የኪራይ ውል መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ የአሁን መልስ ሰጭ የመጀመሪያው ተከራይ ሚስት መሆናቸውን መሠረት አድርጎ ባል በሞት ከተለየ የተከራይነት መብቱም ለሚስት እንደሚገባ ከአዋጅ ቁጥር 07/1967 የወጣውን አዋጅ መንፈስ በመንተራስ የአሁን አመልካች ከቀበሌው ጋር ያደረገውን ውል ቀሪ አድርጎ ቤቱ ለመልስ ሰጭ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በይግባኝ ሁለቱንም ወገኖች ካከራከረ በኋላ በፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በየደረጃው በተሰጡት ውሣኔዎች ላይ አመልካች ቅር ተሰኝቶ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በማመልከት ውሣኔዎች እንዲሻርለት በመጠየቁ ነው፡፡

መልስ ሰጭ በአድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ ያለመቻላቸውን አመልካቹ በቃለ መሃላ በተደገፈ አቤቱታ በማረጋገጡ በመጨረሻው የመጥሪያ ዘዴ በጋዜጣ እንዲቀርቡ ጥሪ የተደረገላቸው ቢሆንም ባለማቅረባቸው በእርሳቸው በኩል የቀረበ የጽሑፍ ክርክር የለም፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል እንደመረመርነውም አመልካች ክርክር ያስነሳውን ቤት በባለቤትነት ከሚያስተዳድረው ከቀበሌው ጋር ባደረገው የኪራይ ስምምነት መሠረት በይዞታው ለማድረጉ የተለየ ጉዳይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የቤቱ ባለቤት ቤቱን በማስተዳደር ረገድ ባለው ሥልጣን እና ኃላፊነት መሠረት ይህንኑ ቤት ለአመልካች ማከራየቱ እና አመልካችም በተለከራይነቱ ውል ማድረጉ እስከተረጋገጠ ድረስ ይህ ውል በሁለቱ

ተዋዋይ ወገኖች ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል ፀጋዊ ተግባር ነው፡፡ መልስ ሰጭ የቤቱ ባለቤት የሆነው አከራይ ባለው ደንብና ሥርዓት መሠረት በሚስትነቷና አብራ ኗሪ ከሆነች የተከራይ ቀደምትነት ውብቷ ለእርሷ እንዲሰጣት አከራዩን ከምትጠይቅ በቀር የቤቱ ባለቤት የሆነው ቀበሌ በአከራይነት ሥልጣኑ ከአሁን አመልካች ጋር ያደገው የኪራይ ውል ተሰርዞ የተከራይ መትነቱ ወደ እኔ ይዙርልኝ የሚል አቤቱታ በፍርድ ቤት የሚቀርብ መብትም አልበራትም፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች እያሉም የሥር ፍ/ቤት የአዋጅ ቁጥር 47/67ን ዓላማና መነሻ ሀሳብ መመርመሩም አስፈላጊ ተግባር እንዳልነበረም ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የአሁን መልስ ሰጭ በቤቱ ባለቤት እና በአሁን አመልካች መካከል የተደረገውን የኪራይ ስምምነት ለማስፈረስ የሚያበቃ ከሕግ የመነጨ መበት ሳይኖራት ባቀረበችው አቤቱታ መነሻ የኪራይ ውሉ ተሰርዞ ቤቱ ለመልስ ሰጭ ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቁጥር 02294 በ3/12/99 እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03263 በ12/6/2000 ዓ.ም. የሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የአሁን አመልካች ከኪራይ በመነጨ መብት በይዞታ ያደረገውን ቤት የአሁን መልስ ሰጭ በፍርድ ለማስለቀቅ የሚያስችላት መብት የላትም ብለናል፡፡

   ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

https://chilot.me

የሰበር መ.ቁ. 36740

ህዳር 23/2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሠላሴ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ዓብዱል ዋሀብ ኢብራሂም ጠ/ገ/ማርያም ገ/እግዚአብሔር

ተጠሪ፡- 1. ወ/ት መሰለች ከፍያለው } ቀረቡ ጠበቃ መኮንን አምቦ

2. አቶ ሰለሞን ከፍያለው }

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ከሣሾች ሲሆኑ አመልካች ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ከሣሾች ባቀረቡት ክስም የከሣሾች አባት በከፍተኛ 24 ቀበሌ 13 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 2011 የሆነውን ቤት በ3/13/1980 ዓ.ም በተዛፈ የወለድ አገድ ውል በብር 29,000 ለ10 አመት ለአመልካች/ተከሣሽ ያስያዙት ሲሆን የከሣሾች አባት በ21/6/89 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ አመልካች ገንዘባቸውን ወስደው ቤቱን እንዲያስረክቡን ብንጠይቃው ፈቃደኛ ስላልሆኑ ገንዘቡን ተቀብለው ቤቱን ያስረክቡን፣ ማስጠንቀቂያ ከደረሣቸው ጊዜ ጀምሮ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሥር ተከሣሽ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ፤ በ3/13/1980 የተደገውን ውል መሠረት በማድረግ የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል፣ 8 ዓመት ያለፈ የቤት ኪራይ ጥያቄም ቢሆን በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ይህ ቢታለፍ ግን

በ3/13/1980 የወለድ አገድ ውል ተደርጎ ቤቱንና ቤቱን የሚመለከቱ ሠንዶች ተረክቤአለሁ፡፡ ከዚህም በኋላም ለግለሰብ ቤት እንዲሸጥ ስለፈቀደ የተጠሪዎች ወላጅ አባትና ባለቤታቸው ነሐሴ 06/1988 በተፃፈ ውል በአ.አ ከተማ መስተዳድር የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ተፈራርመን የቤት ሽያጭ ውል ፈጽመናል፣ ስለሆነም የወለድ አገድ ውሉ በሽያጭ ውል ስለተተካ ሊከሱኝ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የሽያጭ ውሉ በ6/12/88 መደረጉን ቢገልፁም የተመዘገበው ግን 17/03/1991 ነው፡፡ ውሉ በተመዘገበበት ቀን ደግሞ የከሣሾች አውራሽ በህይወት አልነበሩም በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሽያጭ ውል ላይ የተጠሪዎች አባት ሊፈርሙ የማይችሉ በመሆኑ የሽያጭ ውል ፈርመናል የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የግራ ቀኙ ግንኙነት በ3/13/80 ዓ.ም የተደረገው የመያዣ ውል ነው በማለት ተጠሪዎች የሚፈለግባቸውን ብር 29,000 ለአመልካች ሲከፍሉ አመልካች ቤቱን ለተጠዎች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ፤ የሽያጭ ውል የተፃፈው በ6/12/1988 ሲሆን የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ በኃላፊ የተመራበትና የተፈረመበት የተዋዋይ ወገኖች የምስክሮች ፊርማና መታወቂያ የተረጋገጠው በዚሁ ቀን ቢሆንም የዕዳና እገዳ እስከሚሠራ የፎርማሊቲ ስርዓቱና ክፍያ መፈፀሚያው ተቋርጦ እንደገና ማጣራት ተደርጎ በ1991 ዓ.ም ተረጋግጦ ወጭ ሆኗል ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ውል በፊቱ ሲደረግ አረጋጋጭ እንጂ ውል መዝጋቢ አካል ባለመሆኑና ውል በፊቱ የተደረገው በ6/12/1988 ዓ.ም በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ አመልካች ቤቱን በሕጋዊ ውል የያዙት በመሆኑ ሊያስረክቡ አይገባም፤ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ደግሞ በዚህ ውሣኔ ላይ ቅር ተሰኝተው ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የሽያጭ ውል የተደረገው መቼ ነው የሚለውን ጉዳይ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሠበር አቤቱታውን የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪዎች በአመልካችና በተጠሪዎች አውራሽ መሃከል ያለው የወለድ አገድ ውል ነው ሲሉ አመልካች ደግሞ ከወለድ አገድ ውሉ በኋላ የቤት ሽያጭ ውል ተደርጓል በማለት ተከራክረዋል ተጠሪዎች የሽያጩ ውል ተደረገ የተባለው አውራሻችን ከሞቱ በኋላ በመሆኑ የሽያጭ ውል የለም ሲሉ አስተባብለዋል፡፡ ችሎቱም የሽያጭ ውሉ መቼ ነው የተደረገው የሚለውን አግባብ ካለው ሕግ ጋር አናዝቦ መርምሯል፡፡

አንድ ውል ፍፁም ነው የሚባለው ተዋዋዮቹ በተስማማ አካኋን መፍቀዳቸውን ገልፀው ሲገኙ መሆኑ ከፍ/ሕ/ቁ. 1680/1/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ውል አቅራቢው በቃልም ሆነ በጽሁፍ በማያጠራጥር ሁኔታ ግዴታ ለመግባት መፍቀዱን ካሣወቀና ውል ተቀባዩም በተመሣሣይ መልኩ የውል ድርድሩን መቀበሉን ካሣወቀ በሁለቱ መሐከል ስምምነት መደረጉን ከፍ/ሕ/ቁ. 1681 መረዳት ይቻላል በእርግጥ ጉድለት የሌለበት ፈቃድ ከመስጠት በተጨማሪ ሕጉ ልዩ የሆነ የሚጠበቅ አፃፃፍ ፎርም እንዲኖር ካስገደደ ይኸው የአፃፃፍ ሥርዓት መሟላቱ በውሉ ሕጋዊነት ሌለው መሠተታዊ ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ተዋዋዮች ነፃ ፈቃዳቸውን ከመስጠታቸው በተጨማሪ

ውሉን ሕጉ በሚያዘው የአፃፃፍ ሥርዓት ሊመሠርቱ ይገባል፡፡ ለመሣሌ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ውሉ በጽሁፍ ከመደረጉ በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በዳኛ ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ. 1723/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው የቤት ሽያጭ ውል መደረግ ያለበት በጽሑፍ ብቻ ሣይሆን ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በዳኛ ፊት ጭምር ነው፡፡ ውሉ በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት እንዲደረግ ያስፈለገበት ዋነኛ አላማም የተዋዋዮቹ ማንነት ያላቸው ችሎታና መብት ነፃ ፈቃዳቸውን መስጠታቸውን ውሉ የተደረገበትን ቀንም ለማረጋገጥ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪዎች አውራሽ እና አመልካች ውላቸውን በ6/12/1988 ዓ.ም በተፃፈ ሰነድ አዘጋጅተው ሁለቱም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርበው መፈረማቸው የምስክሮቹም ማንነትና ፊርማ በዚሁ ውሉ በተፃፈበት ቀን መረጋገጡን ከክርክሩ ሂደት ተረድተናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ አውራሽና አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያደረጉት በ6/12/1988 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ ግራ ቀኙ ውሉን በ6/12/1988 የፈፀሙ ቢሆንም ቤቱን የሚመለከቱ ዕዳና እገዳ ለማጣራትና ክፍያ ለመፈፀም የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በውሉ ላይ ማህተም ሣያሣርፍበትና የፕሮቶኮል ቁጥር ሰጥቶ ሣያረጋግጥበት የተወሰነ ጊዜ ማለፉን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ አስተዳደራዊ ጉዳዮች እስኪከናወኑ ድረስ በውሉ ላይ ማህተም ሣያርፍበት መቆየቱ ወይም የፕሮቶኮል ቁጥር ሣይሰጠው መዘግየቱ ውሉ እንዳልተደረገ የሚያስቆጥረው ነው ለማለት አያስችልም፡፡

በሌላ በኩል ሠነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው የመንግሥት መ/ቤት ከሆነ ሰነዱ የተፃፈበት እርግጠኛ ቀን ነው የሚባለው የፃፈበት ወይም የተቀበለበት ቀን

በመሆኑ /የፍ/ህ/ቁ.2015/ሀ/ን ይመለከታል/ የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የሸያጩን ውል ያፈራረመበትና ሰነዱን የተቀበለበት ነሐሴ 6/1988 ዓ.ም የሰነዱ ትክክለኛ ቀን ተብሎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ሻጭና ገዢ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሸያጭ ውልን የተፈራረሙበት ቀን ተረጋግጦ እያለ ውሉ ተደረገ ሊባል የሚችለው በዚህ ቀን ሣይሆን አንዳንድ የአስተዳደር ጉዳዮች ተጣርተው መ/ቤቱ ማህተም ያደረገበት ቀን ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62466 በ22/02/99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33198 በ3/07/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 50414 በ18/11/1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ አመልካች ቤቱን በ6/12/88 ዓ.ም በተደረገ የሸያጭ ውል የያዙት በመሆኑ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቡ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡

4/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ 36886

ህዳር 30 ቀን 2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

አመልካች ወ/ሮ ኤልሣቤጥ ወዳጆ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- እነ ወ/ሮ ፍቅርተ ደበበ (6 ሰዎች) - ጠ/ታመነ ጫላ ቀረበ

<u>ፍ ር ድ</u>

በሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ንብረት ባደረጉት ኑዛዜ መሠረት የውርስ ንብረቱን ለማከፋፈል የውርስ አጣሪ ተቋቁሞ የውርሱን ንብረት አጣርቶ ሪፖርቱን በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤትም በመ/ቁ 64782 ጉዳዮን ሲያይ ቆይቶ ተከታታይ ትእዛዞች ሠጥቷል ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነውም ትእዛዝ ሐምሌ 12/1999 ዓ.ም የተሰጠው ነው በዚህ ቀን በዋለው ችሎት የውርስ አጣሪው የኪራይ ገቢን በተመለከተ በ25/3/99 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን አስተያየት መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ትእዛዝ ሠጥቷል ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነውም ትእዛዝ ችሎት የውርስ አጣሪው የኪራይ ገቢን በተመለከተ በ25/3/99 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን አስተያየት መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ትእዛዝ ሠጥቷል አመልካች በዚህ ትእዛዝ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ውድቅ በማድረግ

አመልካችን አሰናብቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው የአመልካች ዋና ቅሬታም ሚች በኑዛዜአቸው በቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘው ቤት ተሸጦ ገንዘቡ ለተናዘዙላቸው ወገኖች እንዲከፈልና ተራፊው ለቁርባን እንዲሆንላቸው በግልጽ ተናዘው እያለ ፍ/ቤቱ ግልጽ የሆነውን ኑዛዜ ከፍ/ሀ/ቁ 910 እና ከሚች ፍላጐት ውጪ በመተርጐም የሰጠው ትእዛዝ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአመልካችን አቤቱታ ለመመርመር ጉዳዩ ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማድረጉ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ የሠጡ ሲሆን ------ አመልካሪች አሁን የሠበር አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ላይ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ የሠጠው ጥቅምት 1/1999 ዓ.ም ሲሆን አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በግንቦት 24/1999 ዓ.ም ውሣኔ ላይ አመልካች ለሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ የለም በዚህ በኋላ የመ/ደረጀ ፍ/ቤት ውሣኔ ከሰጠ ከ 1 አመት በላይ ቆይተው ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለትና በአማራጭም ሌሎች ክርክሮች በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም ምንም እንኳን በሠበር ችሎት ያስቀርባል ያለበት ነጥብ በፍሬ ጉዳይ ላይ ቢሆንም አመልካች የሥር ፍ/ቤት ለኑዛዜው በሠጠው ትርጉም ላይ የሰጠውን አቤቱታ ህጉ በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ ውስጥ አቅርበዋል ወይ? የሚለውን በቅድሚያ ተመልክቷል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በሠበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ትእዛዝ የተሰጠው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሐምሌ 12/1999 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ዕለት ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሠጠው የውርስ አጣሪው የኪራዩን ገንዘብ አስመልክቶ ባቀረበው ሪፖርት ላይ ነው፡፡ አመልካች አሁን ለሠበር አቤቱታው በገለፁት ነጥብ ላይ ፍ/ቤቱ በ12/11/1999 ዓ.ም የሠጠው ትእዛዝ የለም ይልቁኑ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የሠበር አመልካች በሠበር አቤቱታቸው ላይ

ባቀረቡት ነጥብ ላይ ውሣኔ የሠጠው ጥቅም 01/1999 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ደግሞ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በመ/ቁ 53556 በ24/09/1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት የይግባኝ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አንድ የሠበር አቤቱታ በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት የሚቀርበው ደግሞ የሠበር አቤቱታ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ በተሰጠ በ90 ቀናት ውሰጥ እንደሆነ በአ/ቁ 25/88 አንቀጽ 22(ሀ) ሥር ተመልክቷል፡፡ አመልካች አሁን የሰበር ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ ደግሞ የመጨረሻ ውሣኔ ካገኘበት ከ24/09/1999 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ዘጠና ቀናት ውስጥ ለሠበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል ነበር ነገር ግን አመልካች ይህን ሣያቀርቡ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የኪራይን ገቢ አስመልክቶ የሰጠውን ትእዛዝ መነሻ በማድረግ በዚህ ሠበር ችሎት የቀረቡት ጥያቄ በህጉ የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ጠብቆ ያልቀረበ በመሆኑ ከጅምሩም ቢሆን አቤቱታቸው ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው አይደለም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

አመልካች የሠበር አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ከተወሰነ ከዘጠና ቀናት በላይ ቆይተው ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 36887

ኀዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልጋነሽ አበበ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ገብሩ እሸቱ ገብሬ ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ወርቂት እሸቱ ሁሴን ቀርበዋል

ጉዳዩ ከተመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በጠ/ፍ/የፍ/ይ/መ/ቁ. 1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካቾች መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በመጠየቃቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ የአሁኗ አመልካች ከሳሽ፣የአሁኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ የአሁኑ ተጠሪዎች ይግባኝ ባይ እንዲሁም የአሁኑ አመልካች መልስ ሰጭ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ስር ከሳሽ ጥቅምት 28 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘቱ ተከሳሾች በኩታበር ከተማ፣ቀበሌ 01 የሚገኘውን በ500 ካ.ሜ ያረፈውን ሁለት ክፍል የቆርቆሮ ቤት በመስከረም 13 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ሸጠውልኝ ገንዘቡንም ሙሉ በሙሉ ተቀብለው እያለ ቤቱን

https://chilot.me
እንዲያስረክቡና ስመ ንብረትነቱም ስላላዞሩልኝ ተገደው እንዲያስረክቡኝና ስመ ንብረቱም በስሜ እንዲያዞሩልኝ ውሳኔ ይስጠኝ የሚል ነው፤ውሉ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮም የቤቱን ኪራይ በወር ብር 60(ስድሳ ብር) ሂሳብ የ26 ወራት ይክፈሉኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሾችም በሰጡት መልስ ስልጣኑ የወረዳ ፍ/ቤት በመሆኑ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ የማከራከር ስልጣን እንደሌለው እንደተቃወሙና ውሉ ፈጽመን ገንዘቡን ከተቀበልን በኋላ ውሉ እንዳፈረስንና ገንዘቡን እንዲወሰዱ ለከሳሹ ቢያሳውቋቸውም ገንዘባቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም፤ በመሆኑም የውሉ ይፈፀምልኝ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም ብለዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን እንደሚያይና በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ ውል መኖሩ የታመነ በመሆኑና እንደውሉ ላለመፈፀም ያቀረቡት ምክንያት ተቀባይነት ስለሌለው ተከሳሾች ውሉን ተገደው እንዲፈጽሙ፣ስመ ንብረት በከሳሽ ስም እንዲያዞሩ እንዲሁም የቤቱ ኪራይ ብር 1500 ለከሳሽ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱ በሰጠው ፍርድ ቅሬታ በማሳደር ስር ተከሳሹቹ ወደ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ.1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በግራ ቀኙ ወገኞች ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ወደ ደቡብ ወሎ አስ/ፍ/መምሪያ የውልና ማስረጃ አካል ቀርቦ በመጣራት ላይ እያለ የቆመ በመሆኑና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት ያልተፈፀመ በመሆኑ በመካከላቸው የሚጸና ውል እንደሌለና ተዋዋዮቹ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ይመለሱ፣ ስለሆነም ይ/ባዮች የነበሩ የአሁኑ ተጠሪዎች ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) ለመልስ ሰጪ የነበሩት የአሁኗ አመልካች እንዲመልሱ ወስኗል፡፡

ይህ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካች መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ውሉ በጽሁፍና በምስክሮች ፊት

https://chilot.me

የተፈፀመና ለምዝገባም ወደሚመለከተው አካል ቀርቦ እያለና ተጠሪዎች ውሉ ማድረጋቸውና ብር 5000(አምስት ሺህ ብር) ወስደው እንደነበር አምነው እያለ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1723/1/ መሰረት በማድረግ ውሉ በአዋዋይ ፊት አልተመዘገበም በሚል አተረጓጎም ውል የለም ማለቱ ተገቢ አይደለም፣ በመካከላቻው ውል መኖሩን አምነው ባለመመዝገቡ ብቻ ውል የለም ብለው ለመከራከር ለሚቃጡ ተከራካሪዎች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ አያገለግልም የሚል ሆኖ ተጠሪዎች በሰጡት መልስም ውሉ በሚመለከተው ያልተመዘገበና በእንጥልጥል የቀረ በመሆኑ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለ እንዲጸድቅላቸው ጠይቀዋል።

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ በአጭሩ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ የሰበር ችሎትም፣በመካከላቸው ውል አድርገው እንደበር እያመኑ የቤት ሽያጩ በውልና ማስረጃ ባለመመዝገቡ ብቻ ምክንያት በማድረግ ውላቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት በማድረግ ተቀባይነት የለውም ሊሉ ይችላሉ ወይስ አይችሉም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በማስቀመጥ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል።

የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል እንዳካሄዱና ተጠሪዎች የሸያጩ ጠቅላላ ገንዘብ ብር ለተጠሪዎቹ እንደሰጡ ሲገለጽ ስር ተከሳሾት የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎችም ውል አድርገው የነበር ቢሆንም በውልና ማስረጃ የተመዘገበ ባለመሆኑ የሰጧቸው ገንዘብ ብር 5000 (አምስት ሺህ ብር) እንዲወስዱ ቢጠይቋቸውም ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቤቱን እንደሚያስረክባቸው ገለጸዋል፤ በዚህ የተጠሪዎች መልስ ከአመልካች ጋር የቤቱን ሽያጭ ውል አድርገው እንደነበር እንጅ ውሉ በመካከላቸው እንዳልነበረ ፈጽሞ የሚክዱ አይደለም። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 21448 ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ እና 2878 አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል እንደነበር አምነው በውልና ማስረጃ አካል ባለ መመዝገቡ ብቻ ውል የለም፤ ብለው ለሚቃወሙ ተከራካሪዎች የሚያጠቃልል አይደለም

https://chilot.me
፤በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት የሚከናወነው የምዝገባ ዋና አላማ በተዋዋይ ወገኖች የቤት ሽያጭ ውል ለመኖሩ በማስረጃነት እንዲያገለግል ሆኖ ውል ማድረጉና ገንዘብም ተቀብሎ እንደነበር አምኖ ውሉ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት ብቻ መቃወሙ ከላይ ከተቀመጠው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ዓላማ የሚሄድ አይደለም፤ስለሆነም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፤ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በሕግ የሚጸና የቤት ሽያጭ ውል አለ ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 013132 ሐምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፤የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በጠ/ፍ/የፍ/ይ/መ/ቁ. 1051/99 የካቲት 05 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ስር ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች በስር ተከሳሽ የአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የቤት ሽያጭ ውል መፈጸም ጉዳይ በሚመለከት ተጠሪዎቹ የውሉ መኖር አምነው የተከራከሩ በመሆናቸው በውልና ማስረጃ ያልተመዘገበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ መሰረት መቃወም አይችሉም፤የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ሁኔታ የሰጠው አተረጓጎም ተገቢነት የለውም፤ስለሆነም ተጠሪዎች አከራካሪውን ቤት ለአመልካች ያስረክቡ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፤ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

የሰበር መ/ቁ 37015

ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዲልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ቢኒያም ያሲን - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ታደሰ ታፈሠ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዮ የንብረት ህግ ድንጌጋዎችን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በቢሸፍቱ ከተማ ቀበሌ 11 በ911 ካ.ሜ ቦታ ላይ ተመዝግቦ የሚታወቀውን ቦታ እና ንብረት ከወ/ሮ ብርቅነሽ በሻ ጋር በመሆን የአሁኑ አመልካች የወ/ሮ ብርቅነሽ ልጅ ባለቤት በመሆናቸው ይህንኑ ቤት ሲሰሩ ድንበር መተላለፋቸውን ለሠሩት ቤት ከቢሸፍቱ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ትእዛዝ ቢላክላቸውም ቀበሌ ውንና ተጠሪን ሁከት ፈጥረዋል በሚል ምክንያት በመከሰስ አመልካች ቦታውን ከህግ ወጪ ሲጠቀሙ መቆየታቸውን ዘርዝረው በአመልካች በይዞታው ላይ የተፈጠረው ሁከት እንዲቆም ይወሠንላቸው ዘንድ ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተባፊ የክስ ማመልከቻ በአሁኑ አመልካች ላይ በአዳአ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነታቸው ቀርበው ይዞታው ተወስደ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ አስራ ሁለት ዓመት ጊዜ ያለፈው በመሆኑ ክሱ በይርጋ ውድቅ ሊሆን እደሚገባ በይዞታው ላይ ተጠሪ

መብት የሌላቸው መሆኑንና ሌሎች የፍሬ ነገር መከራከሪያ ነጥቦችን በማንሣት ተከራክረዋል የስር ፍ/ቤትም ተገቢውን ማጣራት ለማድረግ ጥረት ከአደረገ እና ተገቢው ምላሽ ከሚመለከተው አካል አለመገኘቱን መሠረት በማድረግ የተጠሪ ክስ በማስረጃ አለመደገፉን በምክንያትነት ይዞ ከሣሽ ተከሣሽን ለመክሰስ ምክንያት የለውም ሲል ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ጉዳዮ በይግባኝ የቀረበለት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ እና ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በኋላ የአሁኑ አመልካች እስከ 21.88 ካ.ሜ ድረስ ድንበር ማለፋቸው ተረጋግጧል በማለት በቦታው ላይ የተሠራው ቤት ተነስቶ ለተጠሪ ሊለቀቅላቸው ይገባል በማለት ወስኖ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኝ ሠሚ እና ሠበር ሰሚ ችሎቶችም በአሁኑ አመልካች በኩል የቀረበላቸውን ይየግባኝና የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ አጽንተውታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 03 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ በቦታው ላይ ያላቸውን መብት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሣይኖራቸው ከአስራ ሁለት ዓመታት በኋላ የመሠረቱት ክስ ተቀባይነት ማግኘቱ ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም የይርጋ ጥያቄ ታልፎ ድንበር ተጥሷል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሠበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪም ቀርበው ሠኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች ቦትውን ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ያገዙ ከማለታቸው ውጪ አያያዙ ህጋዊ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር ወይም

ማስረጃ አለመኖሩን ይርጋውን በተመለከተም ተጠሪ ለተገቢው አካል ቅሬታ አቅርበው አመልካች የሠሩትን ቤት እንዲያፈርሱ ቢታዘዝም የሁከት ይወገድልኝ ክስ በተጠሪ ላይ አመልካች መስርተው በክርክር መቆየታቸውን ሲታይ የይርጋውን ጊዜ የሚያቋርጠው መሆኑን በመዘርዘር የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው አመልካች በበኩላቸው የተጠሪን የሠበር መልስ በመንቀፍና የሠበር ቅሬታ ነጥቦቻቸውን በማጠናከር ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቀርበዋል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊመረመር ይገባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ በአመልካች ተያዘብኝ የሚሉት ቦታ የተወሰደበት ጊዜ 1984 ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ክስ የመሠረቱት ደግሞ ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም ሆኖ የአስራ ሁለት ዓመታት ጊዜ ማለፉን በማመን በወቅቱ ግን ተቃውሞ ሲያሠሙ እንደነበር በመግለጽ የሚከራከሩ መሆኑን ተረድተናል፡፡ የስር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ያደረገው የከሣሽ ክስ ለመክሰስ የሚያስችል አይደለም በሚል ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ማስረጃውን ከተገቢው አካል በማስቀረብ ከተመለከተ በኋላ የይርጋ ክርክሩን በማለፍ ፍሬ ጉዳዮን በመመርመር ወስኗል፡፡

በመሠረቱ የፍታብሔር ጉዳይ ክርክር የሚመራው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ነው ይኸው የሥነ ሥርዓት ህግ በተከራካሪ ወገኖች በኩል በሚቀርቡት የመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ነጥቦች ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክር ከመገባቱ በፊት ተገቢው ብይን ሊሰጥበት እንደሚገባ በአንቀጽ 244(1) ስር ደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት ጉዳዮን የዘጋው የከሣሽ ክስ በማስረጃ አለመደገፉን በመጥቀስ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዮን በማስረጃ መደገፉን የሚያምንበት ሁኔታ አለ ካለ በይርጋው ላይ የቀረበውን ክርክር ያለፈበት ምክንያት የማይታወቅ እና ሥነ ሥርዓታዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የይርጋው ክርክር ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህም መሠረት የተጠሪ ይዞታ በአመልካች የተያዘው በ1984 ዓ.ም ነው ከተባለ ተጠሪ በይዞታው ላይ ያላቸውን መብት ለማስከበር ከአስራ ሁለት ዓመታት በኋላ ክስ መመስረታቸው በፍ/ሕ/ቁ 1149(2) ድንጋጌ አኳያ ሲታይ ተቀባይነት የሚያገኝበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ይዞታውን ለማስከበር የሚቀርበው ክስ የጣልቃ መግባቱ ድርጊት በተፈፀመ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ተጠሪ የአስራ ሁለት ዓመታት ጊዜ ማለፉን ሣይክዱ የአመልካችን ድርጊት በመቃወም ለሚመለከታቸው አካላት ተቃውሞ ሲያሰሙ እንደነበር በመግለጽ መከራከራቸው ይህንኑ ከመቼ ጊዜ ጀምረው ሲፈጽሙ እንደነበር ካለመታወቁም በላይ የይርጋውን ጊዜ ለማቋረጥ የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዮን የመሩበት አካሄድ ሥነ ሥርዓታዊ ካለመሆኑም በላይ የደረሱበት ድምዳሜ ህጋዊ ባለመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል የሚከተለውንም ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በምሥራት ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 08883 ጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት በመ/ቁ 50826 ታህሳስ 08 ቀን 2000 ዓ.ም በዚሁ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት ደግሞ በመ/ቁ 61927 መጋቢት 03 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአደአ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0094 ጥቅምት 15 ቀን 1998 ዓ.ም ተሠጥቶ የነበረው ውሣኔ ምክንያቱ ተለውጦ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ
3. የተጠሪ የይዞታ ማስከበር ጥያቄ በሁለት ዓመት ይርጋ የታገደ በመሆኑ አመልካች 21.88 ካ.ሜ ስፋት ያለውን ቦታ ሊለቁ አይገባም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 37186

ኀዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አለማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ቁምነገር ምናሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሪት ሂሩት ለማ ቀረቡ

2. አቶ ፈቃደ ለማ ቀረቡ

3. ወ/ሪት ፍቅርተ ለማ

መዝገቡ የቀረበው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16181 ጥቅምት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 61796 ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበው አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አባቴና ተጠሪዎች የአያቴ የአቶ ለማ ወልደማሪያምን ወራሾች ናቸው፡፡ አባቴ በሞት ከዚህ አለም የተለየ በመሆኑ በውርስ ንብረት ክፍያ ለአባቴ ደርሶት የነበውን በወርዳ 5 ቀበሌ 29 ቁጥሩ 203 የሆነ ቤት እንዲያስረክቡኝ ብጠይቃቸው ፈቃደኛ ስላልሆኑ ቤቱን እንዲለቁና ለእኔ

እንዲያስረክቡ በማለት አመልካች የጠየቀ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ የውርስ ንብረት ክፍፍሉ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት ያልተመዘገበ ስለሆነ ህጋዊ ውጤት የለውም የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 (1) በመጥቀስ የውርስ ንብረት ክፍያው ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤትም የፊደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ አመልካች ያቀረብኩት ጥያቄ መታየት ያለበት በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት መሆን ሲገባው አላግባብ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ መጥቀሱና ጥያቄዬ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስለሆነ በሰበር ሊታረም ይገባዋል በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረቡትን ክርክር ፍርድ ቤቱ ብይን ያልሰጠበት በመሆኑና በውርስ ንብረት ክፍያ ስምምነቱ ፊርማ የለውም የሚል መቃወሚያ ያነሣን በመሆኑ በሥር የተሰጠው ውሣኔ ፀንቶ እንዲያስናብተን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በግራ ቀኙ በኩል የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪዎችና የአመልካች አባት የሟች የአቶ ለማ ወልደማሪያም የውርስ ንብረት ለመካፈል ያደረጉት ስምምነት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት በውል አዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ያልተደረገ ስለሆነ ሕጋዊ ውጤት የለውም ተብሎ

የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ መመርመርና መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በጭብጥነት የያዘው ነጥብ ለመመለስ በውርስ ሕግ ውስጥ ስለ ውርስ ንብረት የአከፋፈል ሥርአት የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የሚች ውርስ የሚከፋፈለው በወራሾቹ ስምምነት መሰረት መሆን እንዳለበት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1079 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ድንግጌው ወራሾች የሚያደርጉት ስምምነት በተለየ ፎርም መሆን የሚያስፈልገው ወይም በውል አዋዋይ ፊትና በፍርድ ቤት መደረግ እንዳለበት አይደነግግም፡፡

የሚችን የውርስ ንብረት ለማካፈል የሚደረግ ስምምነት ለዳኞች ቀርቦ መጽደቅ ያለበት በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ብቻ እንደሆነ ከውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የሚች ወራሾች የሚችን ውርስ ለመካፈል ለመስማማት ካልቻሉ አንደኛው ወራሽ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1082 እስከ 1089 የተደነገጉትን የክፍያ ደንቦች መሰረት በማድረግና ተግቶ በመሥራት የውርስ ንብረት የክፍያና ድልድል ሐሳብ ለዳኞች እንዲያፀድቁለት መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1079 ንኡስ አንቀጽ 2 በግልጽ የተደነገገው ነው፡፡

ሁለተኛው የሚች ወራሾች የሚችን ውርስ ተስማምተው በሚካፈሉበት ጊዜ አንደኛው ወራሽ ወይም ወኪሉ ያልተገኘ በሆነ ጊዜ ወራሾቹ ተስማምተው የሚያደርጉት የውርስ ንብረት ክፍያ ለዳኞች ቀርቦ ካልፀቀደ በስተቀር ፈራሽ እንደሚሆን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1080 ንኡስ አንቀጽ 1 በግልጽ የተደነገገ ነው፡፡ ከእነዚህ ሁለት መሰረታዊ ሁኔታዎች ውጭ የሚችን የሚንቀሣቀስም ሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት ለማካፈል በወራሾች መካከል የሚደረግ ስምምነት ለዳኞች ቀርቦ መጽደቅ የሚያስፈልገው አለመሆኑን ስለውርስ ንብረት አከፋፍል የተደነገጉትን ደንቦች በማየት ለመረዳት

እንችላለን፡፡ ስለሆነም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስለውርስ ንብረት ክፍያ የተደነገጉትን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ሳያገናዝብ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ስህተቱን ሣያርም ማለፉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16181 ጥቅምት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 61796 ጥር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመረዳት በሌሎች ነጠቦች ላይ የቀረበውን ክርክር በመመርመርና የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመዘን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 341 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ኅዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁጥር 37251

ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- ሌንጫ ዘገዬ ከጠበቃ አበበ ወርቁ ጋር ቀረበ

ተጠሪ፡- ፌደራል ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

ለዚህ ችሎት ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ለተጠሪ ደርሶ ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ መደምደሚያና ለዚህም መሠረት ከሆነው የሕግ ትንታኔ አንፃር ተመርምሮ ውሣኔው ጉድለት የሌለበት ሆኖ ስለተገኘ በፌ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት መዝገብ ቁጥር 36140 በሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕግ/ሥ/ሥ/ቁ 195/2/ለ/2/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡ ግራ ቀኙ ኪሣራቸውን ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 37375

ኀዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ ሽምሱ ከድር አህመድ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- የኤፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር - አልቀረቡም

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻቸው እንደገለፁት የኤፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር በቁ. 12 ጥ/2029/2037 ታሕሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ለአመልካች ባሳወቀው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ. 62758 የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 ይግባኙን በመሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟልና ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች መስከረም 9 ቀን 2000 ዓ.ም ለተጠሪ በፃፉት ማመልከቻ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ለመውሰድ እንዲፈቀድላቸው ቢያመለክቱም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአመልካች ጥያቄና ማስረጃ በማገናዘብ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በሕግ ዲፕሎማ ከተመረቁ በኋላ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች

ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 8/1/ መሰረት በሙያው 5 ዓመት ያላገለገሉ ናቸው በማለት የአመልካች ጥያቄን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ በማሳደር ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 62758 ካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 ሰርዞታል፡፡

አመልካችም ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም አግባብነት ባለው የሕግ ሞያ ከ12 ዓመት በላይ ማለትም ከሰኔ 01 ቀን 1981 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1985 ዓ.ም በአውራጃ አቃቤ ሕግነት፣ ከሐምሌ 01 ቀን 1985 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1988 ዓ.ም ድረስ በወረዳ አቃቤ ሕግ ሐላፊነት እንዲሁም ከጥቅምት 01 ቀን 1989 ዓ.ም እስከ ግንቦት 14 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በነገረ ፈጅነት ያገለገልኩና በ1981 ዓ.ም ለአውራጃ አቃቤ ሕግነት የተሰጠውን ስልጠና በመከተታል የሕግ ስርተፍኬት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ ያሉኝ ማለትም የኢትዮጵያ መሰረታዊ ሕጐች የማወቅ ነኝ፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 8/1/ ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ ለማግኘት ወደ ፈተና ለመቀመጥ የሚያበቃኝ ሆኖ እያለ ተጠሪው እና የስር ፍርድ ቤቱ ሕጉን አላግባብ በመተርጐም ዲፕሎማው ካገኘህበት ጊዜ ወዲህ ቢያንስ 5 አመት ማገልገል ይጠበቅብሐል ማለታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፤ በተጠቀሰው አንቀጽ የተመለከተው መስፈርት በተለይም ደግሞ በሞያው 5 ዓመትን የማገልገል ሁኔታ በህግ ዲፕሎማ ከተመረቅኩ ወዲህ ብቻ ሳይሆን ከመመረቄ በፊት የሰጠኋቸውን አግባብነት ያላቸውን አገልግሎቶቼም የሚጨምር ነው፤ስለሆነም የፊፀሙት የሕጉን የአተረጓጐም ስህተት ታርሞልኝ የጠየቀኩትን የጥብቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችሉኝን ፈተና እንድወስድ ሆኖ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሰጠ ሲሆን ይዘቱም አመልካች የሕግ ዲፕሎማውን ካገኙ በኋላ የ5 ዓመት ግልጋሎት ስለሌላቸውና ከዚያ በፊት የነበሯቸው አገልግሎቶች ለተፈለገው የጥብቅና ፍቃድ ብቃት ስለሌላቸው ቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ 8/1/ መሰረት የተመለከቱትን መስፈርቶች ያልተሟሉ ሆኖ ስላገኘው የአምልካች ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ በመሆኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም የሚል ነው።

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጡ ከላይ እንደተገለፀው ሆኖ ፍርድ ቤቱም አመልካች ላቀረቡት የጥብቅና ፈቃድ ጥያቄ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ያሟላሉ ወይስ አያሟሉም? የሚል መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፣

ከላይ እንደተጠቀሰው የአመልካች ጥያቄ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት ሲሆን ይህ የጥብቅና ደረጃ የሚመለከቱ መስፈርቶች በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 8/1/ በግልጽ የተዘረዘሩ ሲሆኑ እነዚህም በሕግ ዲፕሎማ ያለው፣ የኢትዮጵያ መሰረትዊ ሕጐችን ማወቅ እንዲሁም አግባባነት ባለው ሞያ ቢያንስ 5 ዓመታትን ማገልገል የሚሉ ናቸው፣ የአመልካች ጥያቄ ከእነዚህ መስፈርቶች አኳያ ሲታይ ደግሞ ቀደም ብሎ የሕግ ሰርተፍኬት (በ1981 ዓ.ም የተሰጠ) የነበራቸውና ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በሕግ ዲፕሎማ ማግኘታቸው የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የትምህርቱን መስፈርት ያሟሉና የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህጐች እንደሚያውቁ ነው። የሰጡት ግልጋሎትም ሲታይ በአውራጃ አቃቤ ህግነት ለ4 ዓመታት፣ በወረዳ አቃቤ ሕግ ሐላፊነት ለ2 ዓመት ከዘጠኝ ወራት እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ ነገረ ፈጅነት ለ6 ዓመት ከ8 ወራት አካባቢ በጠቅላላ ወደ 13 ዓመታት መስራታቸውን ስለሚያሳይ ከዚሁ ውስጥም ለጠየቁት የጥብቅና ደረጃ ከ5 ዓመታት በላይ ማገልገላቸው ያሳያል፤ ቀጥሎ መታየት ያለበት

ነጥብ በተጠቀሰው አንቀጽ የሰፈረው የ5 አመታት አገልግሎት የግድ መቆጠር ያለበት ዲፕሎማ ካገኙበት ነው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ሕጉ በግለጽ እንደሚያሳየው የ5 አመታት አገልግሎት የግድ በዲፕሎማ ከተመረቁ በኋላ የሰጡት መሆኑ አያሳይም፣ እነዚህ መስፈርቶች ራሳቸውን ችለው የተቀመጡ እንጂ የአገልግሎት ዘመኑ መቆጠር ያለበት የሕግ ዲፕሎማ ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ለጠየቁት የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ በሕጉ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟሉ ሆነው እያሉ ተጠሪው ሚኒስቴርም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስፈርቱን እንዳላሟሉ በማድረግ ያስቀመጡት የሕጉ አተረጓጎም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ተጠሪ በቁ. 12 ጥ/2029/2037 ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ለአመልካች ያሳወቀው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 62758፣የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ለጠየቁት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጥብቅና ፈቃድ በአዋጅ ቁ. 199/1992 አንቀጽ 8/1/ የተዘረዘሩትን የትምህርት ደረጃ፣ የአገልግሎት ዘመንና የሕግ እውቀት የሚያሟሉ ስለሆነ ተጠሪው ፈተና ሊፈትናቸው ይገባል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ ጉዳዩ ያለቀ ስለሆነ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ን

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 37639

ህዳር 11 ቀን 2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ ወኪል ሁሴን መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ግርማ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10358 ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 6033 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ የአሁን ተጠሪ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርባ አባቱ ወታደር ግርማ ብሩ በመንግሥት ጥሪ ምክንያት ዘመቻ ዘምቶ እስካሁን አለተመለሰም፡፡ በዚህ ምክንያት የመጥፋት ውሣኔ አስወስኛለሁ፡፡ ስለዚህ ወላጅ አባቱ በቀወት ወረዳ በዚጢ ከተማ ቀበሌ 03 ቁጥር 840 የሆነውን ቤት እና የይዞታ ቦታ በእጀመናኛ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ የያዘች በመሆኑ ቤቱን እንድትለቅ ውሣኔ ይሰጥልኝ ወይም የቤቱን

ግምትና ቤት ኪራይ 50,000 እንድትከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ነው። አመልካች በተከሣሽነት ቀርባ ክርክር የተነሣው ቤት 1977 ዓ.ም ጀምሮ የያዝኩት ነው። ቦታውን የተረከብነው እቦታው ላይ የነበረውን የሣር ጎጆ አቶ ግርማ ማሩ ስለሸጡልን ነው። አሁን ያለውን ቤት ያሠራነው እኔና ሚች ባለቤቱ ስለሆን የቤት ግምት ይከፈለኝ በማለት ያቀረበችው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ ሰጥታለች። ተጠሪ በቦታው ላይ በአቶ ግርማ ማሩ ስም በቦታው ላይ ግብር የተከፈለ መሆኑን የሚያሣይ ማስረጃ ያቀረበች ሲሆን አመልካች በበኩሏ በአቶ ግርማ ማሩና በእሷ ባለቤት መካከል ነሐሴ 15 ቀን 1977 ዓ.ም የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ስምምነት አቅርባለች። የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ አመልካች የቤቱን አንድ አራተኛ ካሣ ተቀብላ እንድትለቅ ወስኗል።

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታን ያቀረበች ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በማለት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል። አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሥር ፍርድ ቤት እኔ ያቀረብኩትን የይርጋ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአግባቡ አይደለም እኔ የውርስ ሕግ የይርጋ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ በሚገባ ተከራክሬአለሁ። ፍርድ ቤቱ ይህንን በማለፍ ከሃያ አንድ ዓመት በኋላ የሠራሁትን ቤት እንድለቅ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ደረጃ ታይቶ ይታረምለኝ በማለት አመልክታለች።

ተጠሪ በበኩሏ አመልካች የንብረቱ ባለቤት አይደለችም በቦታው ላይ ግብር የተገበረው በአባቱ ስም ነው። አባቱ ዘመቻ ሲሄድ እኔ ሕፃን ነበርኩ መጥፋቱን ያስወሰንኩት 1998 ዓ.ም ነው ስለዚህ በአመልካች በኩል የቀረበው የይርጋ ጥያቄ

ተቀባይነት የለውም የሚል ክርክር አቅርባለች፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ በአቤቱታ ያቀረበችውን መከራከሪያ በማጠናከር ተከራክራለች፡፡

በአጠቃላይ በሥርና በሰበር ደረጃ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በመጀመሪያ ተጠሪ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበችው ክስና ባቀረበችው ማስረጃ መሠረት የተረጋገጠ ጉዳይ የተጠሪ ጥያቄ ባህሪ በምን መልክ ለመፈረጅ የሚያስችል እንደሆነና የተጠሪ ጥያቄ ባህሪ በተሟላ መልኩ ከተለየ በኋላ ጥያቄው በይርጋ የሚቋረጥ መሆን አለመሆኑን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግንተነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረበችው ክስ 42,600 /አርባ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ብር/ የሚያወጣ የወላጅ አባቷን ቤት አመልካች እንደያዘች ክስ ያቀረበች ቢሆንም፣ ይህንን ተጠሪ ክስ ያቀረበችበትን ቤት የሠሩት አመልካችና ሟች ባለቤቷ መሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪ የጠፋው አባቴ ንብረት ነው በማለት ክስ የቀረበችበት ቤት በጠፋው አባቷ ያልተሠራና የጠፋው አባቷ የአቶ ግርማ ማሩ ንብረት አለመሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሕግ ፊት ውጤት የለውም ብሎ ውድቅ ባደረገው ሰነድ መሠረት አመልካችና ሟች ባለቤቷ ቤት በሠሩበት ቦታ ላይ የነበረችው አንዲት ሣር ጎጆ ቤት እንደነበረች ማስረጃው የሚያሣይ ሲሆን ክርክር በሚካሄድበት ጊዜም ሣር ቤቱ በቦታው ላይ ያልነበረ፣መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው ተጠሪ የወላጅ አባቷ የወታደር ግርማ ማሩ የመጥፋት ወሣኔ የካቲት 25 ቀን 1998 ዓ.ም ስታስወስን በቦታው ላይ ሟች የሰራውና ያፈረሰው ምንም ዓይነት ንብረት አልነበረም፡፡ 1977 ዓ.ም ሟች የሠሩት ሣር ቤትም በቦታው አልነበረችም፡፡ በቦታው ላይ የተሠራው ቆራቆሮ ቤትም ሟች የሰራው የሟች ንብረት

ሣይሆን አመልካችና ሚች ባለቤቷ የሠሩት ቤት ነው። ስለዚህ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826/2/ መሠረት ተጠሪ የመጥፋቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ወላጅ አባቷ በውርስ ሊተላለፍላት የሚችል ቤት በቦታው ላይ አልነበረም።

የተጠሪ አባት ወታደር ግርማ ማሩ በፍርድ መጥፋቱ ሲረጋገጥ ለተጠሪ የባለቤትነት መበት የሚያወርስበት ምንም አይነት ንብረት በቦታው ላይ ያልነበረ ከሆነና በቦታው ላይ ያለው ንብረት አመልካችና ሚች ባለቤቷ የሠሩት ከሆነ አመልካች በውርስ እንዲተላለፍላት የምትጠይቀው መብት ምንድነው የሚለው ነጥብ መመለስ ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል። አመልካች በውርስ እንዲተላለፍላት የምትጠይቀው በንብረት ላይ ያለ የባለቤትነት መብት ሣይሆን አባቷ በቦታው ላይ የነበረው የይዞታ መብት ነው። የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ውሣኔ የሰጠው አመልካች ባለይዞታ የሆኑ ሲሆን ያለፈቃድ ቤት የገነቡ ስለሆነ አንድ አራተኛውን የቤቱን ዋጋ ወስደው ይለቃሉ በማለት ነው። ሆኖም እዚህ ላይ መነሣት ያለበት የተጠሪ አባት በእርግጥ የቦታው ባለይዞታ ነው የሚለው ነው?

የተጠሪ አባት እስከ 1977 ዓ.ም ድረስ የቦታው ባለይዞታ የነበረና በዚያም ሣርቤት ሠርቶ ይኖር የነበረ መሆኑ አያከራክርም ሆኖም ከዚያ በኋላ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1140 መሠረት በእርግጥ በእጃቸው አድርገው በቦታው ላይ ቤት ሠርተውና በቦታው ላይ እያዘዙበት የሚገኙት አመልካችና የአመልካች ሚች ባለቤት የነበሩ መሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ የቦታን ባለይዞታነት በማስረከብ ብቻ የይዞታ መብትን ለማስተላለፍ እንደሚቻል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1143 ይደነግጋል። ስለሆነም አመልካችና ሚች ባለቤቷ ቦታውን ተረክበው ለረዥም ጊዜ የቆዩ በመሆናቸው የቦታው ባለይዞታዎች መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

ተጠሪ በቦታው ላይ በአባቷ ስም ግብር እየተከፈለ የቆየ መሆኑን በመከራከሪያነት አንስታለች፡፡ ሆኖም ግብር መክፈልና ሰነዶችን ይዞ መገኘት ከቦታው ባለይዞታ የሆነ ሰው በላይ ብልጫ ያለው መብት የማያስገኝ መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1144 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ የተጠሪ አባት በቦታው ላይ የነበረውን የይዞታ መብት 1978 ጀምሮ የቀረ ሲሆን ተጠሪ በወቅቱ አመልካች የአባቷን የይዞታ መብት እየተጋፉ ነው የሚል ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገው የሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልጠየቀች በመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1140 በሚደነግገው መሠረት ተጠሪ በውርስ እንዲተላለፉላት የጠየቀችውን ቦታ በሕጉ መሠረት ባለይዞታ ሆነው የኖሩት አመልካችና ሟች ባለቤቷ እንጅ የተጠሪ አባት አይደለም፡፡

ስለሆነም መጥፋቱ በፍርድ የተረጋገጠው ወታደር ግርማ ማሩ ክርክር የተነሣበት ቤት ባለቤትና ባለሀብት አለመሆኑን በማስረጃ ተረጋግጦ እያለና 1978 ዓ.ም ጀምረው አመልካችና ሟች ባለቤቷ ክርክር የተነሣበትን ቦታ ለሀያ አንድ ዓመት ያህል በይዞታቸው አድርገው መኖራቸው እየታወቀና ተጠሪም አባቷ በይዞታው ላይ የነበረውን የይዞታ መብት በፍርድ ለማስከበር በወቅቱ ያቀረበችው ምንም አይነት ክስ ሣይኖር አመልካች ለሃያ አንድ ዓመት ያህል በይዞታዋ ስር የነበረውን ቦታና በቤቱም ላይ የሰራችውን ቤት ለተጠሪ እንድታስረክብ የሰጠው ፍርድ ከላይ የተቀመጡትን የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 6033 የካቲት 19 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2. የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10358 ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል ይፃፍ፡፡
3. አመልካች ለሃያ አንድ ዓመት ያህል በይዞታዋ ሥር የነበረውን ቦታና በቦታው ላይ የሠራችውን ቤት ለተጠሪ የምታስረክብበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ቤቱንና ቦታውን ለተጠሪ እንድታስረክብ አትገደድም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 37665

ኅዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወል

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ እንግዳሸት ታከለ - ጠበቃ ሚዛነወርቅ አታክልት ቀርበዋል፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አበራ ገመቹ - በሌሉበት

2. አቶ አበበ ቢሆነኝ - በሌሉበት

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ተጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 29602 ሰኔ 20 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58315 መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለተፈፀመባቸው ይታረምልኝ በማለት ግንቦት 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ አመልካች በመጠየቃቸው ነው፡፡

የዚህ ክርክር አመጣጥም በፍርድ ባለሐብት አቶ አበራ ገመቹ (1ኛ ተጠሪ) እና በፍርድ ባለ እዳ አቶ አበበ ቢሆነኝ (2ኛ ተጠሪ) መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር የባለእዳው ንብረት የሆነች የታርጋ ቁጥር 2-31493 የሆነች መኪና ለአፈፃፀሙ የተያዘች ሲሆን፣ይሁን እንጂ ይች የተጠቀሰችው መኪና ቀደም ብሎ ለአሁኑ አመልካች በባለ እዳው (2ኛ ተጠሪ) ተሸጦላቸው ወደ ስማቸው ሳያዛውሩ በመቆየታቸው

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት በአፈፃፀም ክርክሩ ጠልቃ በመግባት እስከ ፌደራል ሰበር ችሎት በመሄድ ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የተጠቀሰችው መኪና የአመልካች እንድትሆንና በአፈፃፀሙ እንዳትሸጥ ብሏል፤ በዚህ ውሳኔ መሰረትም መኪናዋ እንዳትሸጥ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ግንቦት 08 ቀን 1999 ዓ.ም ለአፈፃፀም መምሪያ ትእዛዝ አስተላልፏል፣ ይሁን እንጂ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያው ሰኔ 06 ቀን 1999 ዓ.ም መልሶ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ የተጠቀሰችው መኪና እንዳትሸጥ የሚያመለክተው ትእዛዝ ከመተላለፉ በፊት ማለትም የካቲት 28 ቀን 1999 ዓ.ም በተከናወነ የሐራጅ ሽያጭ በብር 13,500 (አስራ ሦስት ሽህ አምስት መቶ ብር) ለአቶ በዳሳ ያደሳ እንደተሸጠች ገልጿል። የመቃወም አመልካች የነበሩት የአሁኑ አምልካችም በመኪናዋ ላይ የተደረገው የሐራጅ ሽያጭ እንዲፈርስላቸው ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ቢጠይቁም ፍ/ቤቱ ከሶ/መ/ቁ. 29602 ሰኔ 20 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የሐራጅ ሽያጩ እንዳይካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418/4/ መሰረት ታግዶ እንዲቆይ ባለመደረጉ በተለይም እስከ ሰበር ችሎት ክርክር ሲደረግም የሕራጅ ሽያጩ መታገድ ሲገባው ባለመታገዱ የተጠቀሰችው መኪና ልትሸጥ በመቻሏ በሕጋዊ መንገድ በጨረታ ከገዛት ሦስተኛ ወገን (የኋለኛው ገዢ) ማስመለስ አይቻልም በማለት ወስኗል።

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመኪናዋ ላይ የተካሄደው የጨረታ ሽያጭ ሊፈርስ አይገባም በማለቱ የአሁኑ አመልካች ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢሉም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቶታል።

አመልካችም የስር ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው በማለት እንዲሻሩላቸው ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዙቱም ሰበር የሰጠው እግድ ወደ አፈፃፀም መምሪያ ከመድረሱ

በፊት የተጠቀሰችው መኪና በሐራጅ ብትሸጥም ሽያጩ እንዲፈርስልኝ ወይም በፍ/ቤት ተይዞ የሚገኘው የመኪናዋ ሽያጭ ገንዘብ ይስጡኝ ብል የስር ፍ/ቤቶቹ አልተቀበሉትም፤ይህ አድራጐት ደግሞ የሰበር ችሎቱ ያስተላለፈውን ውሳኔ የሚፃረር በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ስለሆነም ሽያጩ ፈርሶ መኪና ማግኘት እንድችል ወይም በፍርድ ቤቱ ተይዞ የሚገኘው የመኪናዋ የሽያጭ ገንዘብ እንዲሰጡኝ ሆኖ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎቹ ለአቤቱታው መልስ እንዲሰጡ ትእዛዝ ቢላክላቸውም መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ክርክር ለማቅረብ ያላቸውን መብት እንደተው ተቆጥረው ታልፈዋል፡፡

እንግዲህ በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የነበረው የክርክር ነጥብ ከላይ እየተገለፀ እንደመጣው ሆኖ ይህ ፍርድ ቤትም በመኪናዋ ላይ የተከናወነው የሐራጅ ሽያጭ ሊፈርስ ይገባል ወይ? ጨረታው አይፈርስም የሚባል ከሆነ በስር ፍርድ ቤቱ ተይዞ የሚገኘው የመኪናዋ የሽያጭ ገንዘብ ለአመልካች ሊሰጥ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነችው የሰሌዳ ቁጥሯ 2-31493 የሆነችው መኪና የ2ኛ ተጠሪ አቶ አበበ ቢሆነኝ ስትሆን እኚህ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪው አቶ አበራ ገመቹ በነበራቸው ክርክር ምክንያት በአፈፃፀም ተይዛ እዳን ለመክፈል የሐራጅ ማስታወቂያ የወጣላት ስትሆን በሌላ በኩል የአሁኑ አመልካች መኪናዋ ከ2ኛ ተጠሪ እንደገዛትና ገና ስም በማዛወር ሂደት ያለ መሆኑ ገልፆ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ጣልቃ በመግባት የመኪናዋ ባለመብት መሆኑ የፌደራል ሰበር ችሎት አረጋግጦለት መኪናዋም በሐራጁ እንዳትሸጥ እግድ እንዳስተላለፈ ነው፣ ይሁን እንጂ መኪናዋ በወጣው የሐራጅ ሽያጭ መሰረት አስቀድማ የተሸጠች መሆኗ በመግለጽ እግዱን ተግባራዊ ማድረግ እንዳልቻለ

የአፈፃፀም መምሪያ በማረጋገጡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ የከፍተኛው ፍርድ ቤቶቹ ይህንን ተቀብለው እንዳፀደቁ ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎት መኪናዋ እንዳትሸጥ እግድ ያስተላለፈው ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን፣ የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤትም ይህ እግድ ተግባራዊ እንዲሆን ለአፈፃፀም መምሪያው ትእዛዝ ያስተላለፈው ግንቦት 8 ቀን 1999 ዓ.ም ነው፣ይሁን እንጂ መኪናዋ በሃራጅ የተሸጠችው የካቲት 28 ቀን 1999 ዓ.ም መሆኑ የአፈፃፀም መምሪያው ገልጿል፤ይሕ የሚያሳየው ደግሞ የአሁኑ አመልካች በመኪናዋ ላይ መብት ያለው መሆኑ ለማረጋገጥ እስከ ሰበር ችሎት ሲከራከር መኪናዋ አስቀድማ እንድትታገድ አላደረገም፣ በመሆኑም የሰበር ፍ/ቤቱ እቅድ ከማስተላለፉ በፊት ከአንድ ወር ከ18 ቀናት አስቀድማ በህጋዊ መንገድ በጨረታ የተሸጠችን መኪና ለማስመለስ አመልካች ያቀረበው ጥያቄ የኋለኛው ገዢ መብት የሚያጣብብ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶቹ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም፣ ስለሆነም አመልካቹ ከዚህ አኳያ ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል መኪናዋ በሐራጅ ማስታወቂያው መሰረት በብር 13,500 (አስራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) እንደተሸጠችና ገንዘቡም ታግዶ እንደሚገኝ አመልካች እየገለፀ ስለሆነና ይህ የሰበር ችሎትም ቀደም ብሎ ማለትም ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መኪናዋ ለአመልካች እንደምትገባ አረጋግጦ ስለነበር ከላይ የተጠቀሰው የመኪናዋ በፍርድ ቤቱ ታግዶ የሚገኝ ከሆነ ሊሰጠው ይገባል፤ የስር ፍርድ ቤቶቹ ከዚህ አኳያ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ በከ/መ/ቁ. 29602፣ሰኔ 20 ቀን 1999 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 58315 መጋቢት 25 ቀን

2000 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንተዋል፤ ይፃፍ፡፡

2. የሰሌዳ ቁጥር 2-31493 የሆነች አከራካሪ መኪና በሐራጅ የተሸጠችው የካቲት 28 ቀን 1999 ዓ.ም ስለሆነና ይህም ይህ የሰበር ችሎት ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም እንዳትሸጥ እግድ ከማስተላለፉ በፊት ስለሆነና የሽያጩ ሂደት እንዲፈርስ ማድረግ በኋላኛው ገዢ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ አመልካች ከዚህ አኳያ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤ይሁን እንጂ የመኪናዋ ሽያጭ ገንዘብ 13,500 (አስራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ይህ የሰበር ችሎት ባስተላለፈው የእግድ ትእዛዝ መሰረት በአፈፃፀም መምሪያው ታግዶ እንደሚገኝ ስለተገለፀ ለአመልካች ወጪ ሆኖ ይሰጣቸው ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

https://chilot.me

የሰበር መ.ቁ. 37879

18.3.2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አየሁሽ አስፈራው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አስካለ ገ/እየሱስ
2. ወ/ት ቅዱሣን ገ/እየሱስ
3. አቶ ኪዳነማርያም ገ/እየሱስ } ቀረቡ
4. አቶ ሐብቴ ገ/እየሱስ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ወላጅ አባታችን አቶ ገ/እየሱስ አምባዬና ወላጅ እናታችን ወ/ሮ ምግብነሽ በየነ በሕይወት እያሉ በጎንደር ከተማ ቁጥር 260 የሆነ ቤት በእናታችን ስም ሠርተዋል አባታችን በ1973 ዓ.ም እናታችን ደግሞ በ1997 ዓ.ም የሞቱ ሲሆን ወራሽነታችንን አረጋግጠናል፡፡

ሆኖም ተከሣሽ ምንም መብት ሣይኖራት በውርስ የተላለፈልንን ይህንኑ ቤት ይዛ ስለምትገኝ እንድትለቅ ብንጠይቃት ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልሆነችም፡፡ ስለዚህ ቤቱን እንድታስረክበን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽ ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ ተከሣሽ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱት ክርክር በሰበር ችሎት የሚመረመር ባለመሆኑ ዝርዝሩን መመዝገብ ባለማስፈለጉ ታልፏል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም ተከሣሽና የከሣሾች ወንድም ሟች ፍስሐ ገ/እየሱስ ጋር ጋብቻ መሥርተን በዚሁ ክስ በቀረበበት ቤት እየኖርን 4 ልጆችን ወልደናል፡፡ ስለሆነም እነዚህ 4 ልጆች ሟች አባታቸውን ተክተው ወ/ሮ ምግብነሽ በየነን የመውረስ መብት አላቸው ይባልልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተከሣሽ ከከሣሾች ወንድም ሟች ፍስሐ ገ/እየሱስ 4 ልጆች ስለመውለዳቸው የተረጋገጠ ስለሆነ ሟች አባታቸውን በመተካት መውረስ ስለሚችሉ ተከሣሽ የልጆቿን ድርሻ 1/5 /አንድ አምስተኛ/ በማስቀረት ቀሪውን ለከሣሾች ታስረክብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሣሾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባዮች በሥር ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት መ/ሰጭ የውርስ ንብረት ታስረክበን በማለት ሲሆን የመ/ሰጭ ልጆች ሟች አባታቸውን ተክተው ስለመውረሣቸውና ሊያገኙ የሚችሉትን መበት በተከሣሽ ከሣሽነት ዳኝነት ያልጠየቁ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ መ/ሰጭ የቤቱን 1/5 አስቀርተው ቀሪውን ለይግባኝ ባይ ያስረክቡ ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት በመሻር መ/ሰጭ ክርክር የቀረበበትን ቤት ለይግባኝ ባዮች ያስረክቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር የተነሣበትን ቤት

የአመልካች ልጆችና ተጠሪዎች ድርሻቸውን እንዲካፈሉ በማለት የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መሻሩ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው ማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍ አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት አኳያም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ክስ ያቀረቡት የውርስ ቤት ይዛ የምትገኝ ስለሆነ ታስረክበን በማለት ነው፡፡

አመልካችም በበኩላቸው የተጠሪዎች ወንድም ከሆኑት ሟች ፍስሐ ገ/የሱስ ጋር በጋብቻ ተሳስረው ለክርክሩ ምክንያት በሆነው በዚሁ ቤት ሲኖሩ አራት ልጆችን እንደወለዱ ጠቅሰው ከሟች የተወለዱት ልጆች አባታቸውን ተክተው ሊወርሱ ስለሚገባ በዚሁ መሠረት ክፍፍሉ ሊፈፀም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ከተጠሪዎች ወንድም ሟች ፍስሐ ገ/እየሱስ አራት ልጆች መውለዳቸው ከተረጋገጠ የተጠሪዎች ጥያቄ የውርስ ሐብት የሆነውን ቤት ታካፍለን የሚለን መሆን ሲገባው ቤቱን በጠቅላላ ልታስረክበን ይገባል በማለት አቤቱታ ማቅረባቸው ቅን ልቦና እንደጎደለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም ተከሣሽ የሆነ ወገን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ማቅረብ የሚጠበቅበት ከሣሽ ከሆነው ወገን የሚጠይቀው መብት ወይንም ጥቅም በሚኖርበት ጊዜ ሲሆን ከሣሾች/የአሁን ተጠሪዎች/ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ድርሻቸውን ለይተው ክስ ማቅረብ እየቻሉ ጠቅላላ ንብረቱ ይገባናል በማለት ክሱን ባቀረቡበት ሁኔታ ተከሣሽ /አመልካች/ ይገባኛል የሚሉትን ድርሻ በተመለከተ በመልስ ክርክራቸው በማስረጃ አስደግፈው ከማንሣት አልፈው ዳኝነት ከፍለው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ማቅረብ ነበረባቸው ማለት የሥነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማና ግብ መሠረት ያደረገ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም የአመልካች ባለቤት የነበሩት ሟች ፍስሐ ገ/እየሱስ የተጠሪዎች ወንድም ስለመሆናቸው በተጠሪዎች አልተካደም በውርስ ሕጉ መሠረት ለመውረስ ከሚያበቁ ችሎታዎች /capacity to succeed/ መካከል አንደኛው ችሎታ አውራሹ በሞተ ጊዜ የወራሹ ወይንም የኑዛዜ ተጠቃሚው በሕይወት መገኘት /the condition of survivorship/ ሲሆን ወራሹ ወይንም የኑዛዜ ተጠቀሚው ከአውራሹ በፊት ቀድሞ ከሞተ በሕይወት ያሉ ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆቹ ክሱን ተክተው እንደሚወርሱና ይህም የመርሁ ልዩ ሁኔታ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842/3/ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ባለቤት ከእናታቸው ከሟች ወ/ሮ ምግብነሽ በየነ ቀድመው ወይንም ዘግይተው ስለመሞታቸው ከመዝገቡ መረዳት ባይቻልም ቀድመው ሞተዋል ቢባል ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 842/3/ ድንጋጌ መሠረት ልጆቻቸው ተተክተው መውረስ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ ከእናታቸው ሞት በኋላ ሞተዋል ቢባልም የመውረስ ችሎታቸውን አረጋግጠው ስለሞቱ በድርሻቸው የወረሱትን ንብረት ለወራሽ ልጆቻቸው የማይተላለፍበት ሁኔታ አይኖርም፡፡

በዚህ መሠረትም የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ወገኖች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የውርስ ቤት እንደየድርሻቸው ሊከፋፈሉ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያለው ሆኖ ሣለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በማቅረብ ድርሻቸውን አልጠየቁም በሚል ምክንያት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር ክስ የቀረበበትን ቤት ለተጠሪዎች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 14390 በ13/10/99 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ አጽንቶን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 13340 በ30/7/2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ ሽረናል፡፡
2. ይህ ችሎት ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን የዕግድ ትእዛዝ በማንሣት የፍርድ አፈፃፀም የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔና ይህ ችሎትም በፀናው ፍርድ መሠረት እንዲፈፀም የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 39789

ቀን 17/3/2001

ዳኞች፡- አሠግድ ጋሻው

ደስታ ገብሩ

ብርሃኑ አመነው

ይግባኝ ባይ፡- የአቶ ደነቀው ቢተው ወራሾና ሚስት - ጠበቃ ግርማ ኃ/መስቀል ቀረቡ፡፡

1. ወ/ት ዓለም ደነቀው
2. አቶ ያየህ ደነቀው
3. ወ/ት ኢትዮጵያ ደነቀው
4. ወ/ት እንደገና ደነቀው
5. ወ/ት ራሔል ደነቀው
6. ተማሪ ድሜጥሮስ ደነቀው
7. ተማሪ መርቆርዮስ ደነቀው
8. ወ/ሮ ገነት በሻህውረድ /የሚች ሚስት/

መልስ ሰጪዎች፡- የአቶ ይኩኖ ውብሸት ወራሾችና ሚስት - ጠበቃ ፍቃዱ አስፋው ቀረቡ፡፡

1. ወ/ሮ ትዕግሥት ይኩኖ
2. ወ/ሮ ተስፋዬ ይኩኖ
3. አቶ ሁነኛው ይኩኖ
4. ወ/ሮ እመቤት ይኩኖ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ብይን እና ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ብ ይ ን

ይግባኙ ሊሰማ በተቀጠረ ዕለት ማለትም በ2/3/2001 የ3ኛ መልስ ሰጭ ወኪል ነን በማለት ወ/ሮ ነጠሩ ውክልናቸውን ይዘው የቀረቡ ቢሆንም የይግባኝ ባይዎች ጠበቃ ወኪል ፍ/ቤት ቀርበው ለመከራከር አይችሉም በማለት ተቃውመዋል፡፡

በኛም በኩል ውክልናቸውን እንዳየነው በራሣቸው ፍ/ቤት ቀርበው ለመከራከር የተወከሉ ሣይሆን ጠበቃ ቀጥረው ለመከራከር እንደሚችሉ ተረድተናል በ3ኛ መልስ ሰጭ ጋር

የተወካይዋ ዝምድናም ተጠይቆ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 58/ሀ/ ሥር የሚወድቅ ያለመሆኑን ተመረድተናል፡፡

በመሆኑም 3ኛ መልስ ሰጭ መጥሪያው ሲደርሣቸው ራሣቸው መቅረብ ወይም ፍ/ቤት ለመከራከር የሚችል ሕጋዊ ወኪል ወይም ጠበቃ ወክለው ባለመከራከራቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70/ሀ/ መሠረት በሌሉበት ጉዳዩ ይታያል ብለናል፡፡

በመሆኑም የይግባኙን ቅሬታ የሌሎቹን መልስ ሰጭዎች ክርክር በአጠቃላይ መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ይግባኝ መነሻ የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁጥር 46961 በ2/10/2000 በዋለው ችሎት የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭዎች በይግባኝ ባይዎች ላይ ባስፈረዱት ፍርድ መነሻ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሆነው በወረዳ 27 ቀበሌ 10 በካርታ ሊዝ 0025 የተመዘገበው ድርጅት ለሀራጅ ሁለት ጊዜ ቀርቦ ገዢ ስላልተገኘ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 428/2/ መሠረት የፍርድ ባለመብቶች ድርጅቱን እንዲረከቡ የሥር ፍ/ቤት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መዝገብና ቀን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የሥር የፍርድ ባለዕዳዎች /የአሁን ይግባኝ ባይዎች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ሐምሌ 12/2000 የተፃፈ የይግባኝ ቅሬታ በማቅረባቸው ይህ ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 338 እና 339 መሠረት ግራ ቀኙ እንዲቀርቡ በማድረግ ከ3ኛ መልስ ሰጭ በቀር የተቀሩትን ክርክር ሠምቷል፡፡

የይግባኝ ባይዎች ቅሬታ መልስ ሰጭዎች የፍርድ ባለመብት የሆኑበት የገንዘብ መጠን ብር 552,218.40 ብቻ ከወለዱ ሂሣብ በስተቀር ስለሆነ በሥር ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲረከቡት የታዘዘው ንብረት ግን ግምቱ ዋጋው ብር 7,479,378.23 የሆነ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ንብረት ሆኖ የሊዝ ሥህተት ያለበት ስለሆነ ይግባኝ ባይዎቹ ንብረቱን በማከራየት ወይም በዋስትና በማስያዝ የፍ/ባለመብቶችን ገንዘብ እንድንከፍል ያቀረበውን አቤቱታ የሥር ፍ/ቤት ውድቅ ያደረገው ያለአግባብ ስለሆነ የ3 ወራት ጊዜ ተሠጥቶን ተሳስበን ገንዘቡን እንድንከፍል እንዲወሰንልን፡፡

የጨረታ ማስታወቂያ በበቂ ሁኔታ ለሕዝብ ሣይገለጽ ተጫራቾች አልቀረቡም መባሉና የማይንቀሳቀስ ንብረቶች ከነእዳቸው ግልጽ ትዕዛዝ ሳይሰጥ በዝምታ ይረከቡት መባሉ ሥህተት እና ይግባኝ ባይዎችን ለጉዳት የዳረገ ሰለሆነ እንዲታረምልንና የፍ/ባለመብቶች በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ባስወጡት የጨረታ ማስታወቂያ ላይ የተገለፀውን ብር 7,479,378.23 በማቀናነስ በፍ/ባለሀብቶች ባስወሰኑት ገንዘብ መጠንና በተጨማሪ እስከተረከቡበት ጊዜ ድረስ ታስቦ ያልታየውን የሊዝ ዕዳ ጭምር እንዲረከቡ እንዲታዘዝልን ወጭና ኪሣራም እንዲከፍሉ ይወሰንባቸው በማለት በዝርዝር አመልክተናል፡፡

መልስ ሰጪዎች በበኩላቸው በባለዕዳዎቹ /ከይግባኝ ባይዎች የምንፈልገው ዕዳ 90,436.00 ነው ወጭና ኪሣራ ይደመራል በጠቅላላው 901,470.00 ብር ነው፣ ሀራጅ አወጣጡ አንዳችም ችግር የለበትም የሀራጅ ሽያጩ በተደጋጋሚ ነው የተደረገውን የሚያዝያ 3/99 ሀራጅ በአንድ ወር በላይ ለሕዝብ በጋዜጣ ተገልጿል ሌሎችም የሀራጅ ማስታወቂያዎች ከ1 ወር በላይ በጋዜጣ ለሕዝብ ይፋ ሆነዋል ንብረቱ የተገመተው ብር 4,234,000 ብር /አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሠላሣ አራት ሺህ ብር አካባቢ ነው ንብረቱ የሊዝ ዕዳ እስከ የካቲት 99 ድረስ 3,245,174.50 /ሦስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰባ አራት ብር ከሀምሣ ሣንቲም/ አለበት፣ በተጨማሪ የመሬት አስተዳደር 884,087.50 ዕዳ ይከፈልበታል ንብረቱን ስንረከብ ተቀናንሶ 104,738.00 ብር ስለሆነ ከተወሰነልን በታች ነው ተረክበን ለጊዜው ፍርድ የተፈፀመልን፣ ይግባኝ ባይዎች በሌላ መዝገብ ባለመብት የሆኑት በአንደኛ ወራሽ ላይ ብቻ ነው በዚህ ስሌት በሷ ድርሻ ላይ ይግባኝ ባይዎች መጠበቅ ይቻላሉ በማለት በዝርዝር ተከራክረዋል፡፡

በኛ በኩል ለዚህ ጉዳይ አወሣሠን 1ኛ/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በወረዳ 27 ቀበሌ 10 በካርታ ሊዝ 0025 የተመዘገበውን ድርጅት ሁለት ጊዜ ሀራጅ ወጥቶ ገዢ አልተገኘም በሚል ብቻ ድርጅቱ የተለያዩ ዕዳዎች ያሉበት መሆኑ እየተገለፀ በዝምታ በማለፍ መልስ ሰጭዎች ይረከቡት ሲል የሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ? ነው አይደለም፡፡

2ኛ/ ይግባኝ ባይዎች ከመልስ ሰጭዎች ጋር ተማስበን ጊዜ ተሰጥቶን ዕዳውን እንክፈል ንብረቱን በማከራየት፣ በማየትና በማስያዝ ዕዳዎችን እንክፈል ሀራጅም በበቂ ሁኔታና ጊዜ ለሕዝብ አልተገለፀም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት አለው የለውም? የሚሉትን ጭብጦች ከግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎችና ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በቅድሚያ ይግባኝ ባይዎች ከመልስ ሰጪዎች ጋር እንተማሠብ ጊዜ ተሰጥቶን ዕዳችንን እንክፈል ለሚሉት አፈፃፀሙ ረዥም ጊዜ የወሰደና ዕዳቸውን ባለመክፈላቸው ባለመብቶች ንብረት ወደማሸጥ የደረሱበት መሆኑ የሥር መዝገቡ የሚያስረዳ ሲሆን በዕርግጥ ባለዕዳዎቹ /ይግባኝ ባይዎቹ ዕዳውን ለመክፈል ፍላጎት ያላቸው ቢሆን ኖሮ በዚህ ረጅም ጊዜ ለመጠቀም በቻሉ ነበር ይሁንና አሁን አፈፃፀሙ ለረዥም ጊዜ ከተጓተተ በኋላ ያቀረቡት ጥያቄ የተጨማሪ ጊዜ ለማግኘትና አፈፃፀሙን የበለጠ ለማዘግየት ስለሆነ አልተቀበልናቸውም፡፡

ንብረቱንም አስይዘን ወይም አከራይተን ዕዳችንን እንክፈል የሚለው ጥያቄም በተመሣሣይ መልስ ሰጭዎች ያስፈረዱትን ገንዘብ በአፋጣኝ እንዲያገኙ ለማድረግ የታቀደ መሆኑን አመልካች ከመሆኑ በቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ስላልሆነ ክርክራቸውን ውድቅ አድርገናል፡፡

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በወረዳ 27 ቀበሌ 10 በካርታ ሊዝ ቁጥር 0025 የተመዘገበውን ድርጅት ባለመብቶች /መልስ ሰጪዎች/ እንዲረከቡት በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በተመለከተ ይግባኝ ባይዎች ድርጅቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የወጣው ማስታወቂያ በበቂ ጊዜና ሁኔታ ለሕዝብ አልተገለፀም የሚል ክርክር ቢያነሱም ድርጅቱ በሀራጅ እንዲሸጥ 3 ጊዜ የሀራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዢ ያለመገኘቱን የሥር መዝገቡ ሰለሚያስረዳ ቅሬታቸው ተቀባይነት የለውም ሆኖም ይህ ድርጅት በሚሊዮን የሚቆጠር የሊዝ ዕዳና የመሬት አስተዳደሩም በድርጅቱ ላይ የሚልገው ዕዳ ያለበት መሆኑን በግራ ቀኙ የታመነ ሲሆን በሀራጅ ማስታወቂያው ላይ ጭምር ይህ ዕዳ በድርጅቱ ላይ የሚፈለግ መሆኑን ተገልፆ እያለ የሥር ፍ/ቤት ድርጅቱን መልስ ሰጭዎች /ባለመብቶች ይረከቡ ሲል በድርጅቱ ግምት ልክ ወይም በሀራጁ መነሻ ግምት ልክ መሆን ያለመሆኑን ወይም በተፈረደው ገንዘብ ልክ መሆን ያለመሆኑን በድርጅቱ ላይ የሚፈለገው የሊዝ

ዕዳም ሆነ ሌሎች የአስተዳደር መ/ቤት ዕዳዎችን ድርጅቱን እንዲከፈቡ የተወሰነላቸውን መልስ ሰጭዎች የሚመለከት ስለመሆን ያለመሆኑ ግይገልጽ በደፈናው ባለመብቶቹ /መልስ ሰጭዎቹ/ ድርጅቱን ይረከቡ ብሎ የሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ስላልሆነ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

ው ሣ ኔ

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/ቁጥር 46961 በ2/10/2000 በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት አሻሽለን በወረዳ 27 ቀበሌ 10 በካርታ ሊዝ ቁጥር 0025 የተመዘገበውን ድርጅት ባለመብቶቹ /መልስ ሰጭዎቹ/ በሚረከቡበት ጊዜ የሊዝ ዕዳ እና ሌሎች የአስተዳደር መ/ቤት ዕዳዎችን ግን መክፈል እንደሚገባው ባለመብቶቹ ድርጅቱን ከነ እዳው ስለመረከብ ያለመረከባቸው፣ ድርጅቱን በተፈረዳላቸው ዕዳ ልክ ወይስ በድርጅቱ ግምት ልክ /በሀራጅ መነሻ ግምት/ ስለመረከብ ያለመረከባቸው አጣርቶ ተገቢውን ትዕዛዝ እንዲሰጥ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሠረት ታዟል፡፡

እንደውሣኔው እንዲፈፀመ የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይድረሰው፡፡

ይህ ፍ/ቤት ጥቅምት 10/2001፣ ጥቅምት 17/2001 በዋለው ችሎት የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይላፍ፡፡

ይግባኝ ባይዎች በዚህ ፍ/ቤት በሞ/85 በቁጥር 33900 በ18/2/2001 ያስያዝሁት ብር 6396.40 /ስድስት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከአርባ ሣንቲም/ ወጭ ሆኖ ይመለስላቸው፡፡

- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

- መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

ውሣኔው በ18/3/2001 ከሰዓት በኋላ ለግራ ቀኙ ተነበበ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ውሣኔ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የወ/ይ/መ/ቁ.39905

ሕዳር 22 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ዳኜ መላኩ

አቶ አማረ አሞኜ

አቶ ከድር አልይ

ይግባኝ ባይ፡- መሐመድ ሰይድ ከማ/ቤት ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ አቶ ሽበሽ ይግዛው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሠጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

ይህ ይግባኝ የቀረበው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ.60736 ሰኔ 06 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ባይ ቅር ተሰኝተው ሐምሌ 17 ቀን 2000 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ ማመልከቻ ስላቀረቡ ነው፡፡

የስር ፍ/ቤት የፌዴራሉ ዐ/ሕግ በይግባኝ ባይ ላይ የወ/ሕግ አንቀጽ 540ን ጠቅሶ መስከረም 01 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ላይ በአቃቂ ቃሊት ክ/ከተማ ሣሪስ ጉልት ከሚገኘው አረቂ ቤት ወስጥ ሚች በቦክስ መቶኛል በሚል ሰበብ ሚች ብርሃኑ ዓለሙን በአረቂ ጠርሙስ ጭንቅላቱን መትቶ በመግደሉ በፈጸመው የሰው መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ክስ ቀርቦባቸው ፍ/ቤ ቀርበው በመከዳቸው ዐቃበ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ምስክሮች አቅርቦ ከሠሚ በኋላ ይግባኝ ባይ እንዲከላከሉ ብይን ቢሠጣቸውም መከላከያ የለኝም በማለታቸው መዝገቡን መርምሮ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ የተላለፍ ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኋላ በ5 /አምስት/ ዓመት እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡

ይግባኙ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ይህ ፍ/ቤት በወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁጥር 192 በደነገገው መሠረት ግራ ቀኙን አስቀርቦ የይግባኝ ክርክራቸውን ሠምቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በይግባኝ ቅሬታቸው የሚያነሱት ቅሬታ ሚች በእኔ ምት ይሙት ወይም በሌላ የተረጋገጠ ነገር ሣይኖር በነፍሰ ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ መባል አልነበረብኝም፣ የወንጀል ሪኮርድ የሌለብኝ ፣ ያልተማርኩና ሚች ሲመታኝ በሠጠሁት ምላሽ ለተፈጸመ በነፍሰ ግዳይ ጥፋተኛ መባሌ በአግባቡ ስላልሆነ በነፃ ልሠናበት ይህ

የሚታለፍ ቢሆን ደግሞ ቅጣት ያቅልልኝ ያሉ ሲሆን ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ ሟች ይግባኝ ባይን በቦክስ የተማታ ቢሆንም ይግባኝ ባይ በአረቂ ጠርሙስ መማታታቸው ከመከላከል ወሠን ያለፈና በአረቂ ጠርሙስ ጭንቅላቱ የተመታሠውም ሊሞት እንደሚችል ሟችም በዚሁ ምክንያት መሞታቸው ተረጋግጧል፡፡ ሮብ ማታ ተመተው በህይወት የቆዩት አንድ ቀን ብቻ ነው ይህ የሞቱን መንስኤ ከተመቱት ውጭ ወደ ሌላ መወሠድ አይቻልም ስለሆነም ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ ነው ቅጣቱም ጥፋተኛ የተባሉበት የሕግ አንቀጽ የያዘውን ዝቅተኛ መባላቸው በአግባቡ ነው ቅጣቱም ጥፋተኛ የተባሉበት የሕግ አንቀጽ የያዘውን ዝቅተኛ መነሻ ስለሆነ በዛ የሚባል ስላልሆነ በስር ፍ/ቤት የተሠጠው ውሣኔ ይጽናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ለኛም ሟች በይግባኝ ባይ ድርጊት መሞታቸው ተረጋግጧልን አልተረጋገጠም ተረጋግጧል ቢባልስ ጥፋተኛ የተባሉት ጥፋተኛ መባል ባለባቸው የሕግ አንቀጽ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦችን ይዘን ክሱን፣ ማስረጃውንና ግራ ቀኙ ያሣዬዱትን ክርክር አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል

እንደመረመርነው ዐቃቤ ሕግ በምስክርነት ያቀረባቸው ሶስት ምስክሮች የሠጡት ምስክርነት ቃል ተመሣሣይ ሲሆን ይዘቱም ሟችና ይግባኝ ባይ በአንድ ላይ አረቂ ቤት እንደነበሩ፣ ሟች ሞቅ ብሎት ጠጭዎችን ሁሉ ሲረብሹ ይግባኝ ባይ አትረብሽን በማለታቸው ሟች ተነስተው በቦክስ ይግባኝ ባይን እንደተማቱ እና ይግባኝ ባይም የአረቂ ጠርሙስ አንስተው የሟችን ጭንቅላት እንደመቱ የሟች ጭንቅላት ደምቶ እና አብጦ እንደነበር ሐኪም ቤት ሄደው የታከሙ ቢሆንም በበነጋው ህይወታቸው እንዳለፈ መስክረዋል፡፡

ይህ የምስክሮች አመሠካከር ሟች ለሞት የቀቁት በይግባኝ ባይ ድርጊት መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ ምክንያቱም በሌላ መንገድ በተቃራኒ እስካልተረጋገጠ ድረስ መጠጥ ቤት በደህና ገብቶ ሲጠጣ ቆይቶ በአረቂ ጠርሙስ ከተመታና ከአንድ ቀን በኋላ ህይወቱ ካለፈ ይህ ሰው በደረሠበት ጉዳት ምክንያት ሙቷል ከማለት አልፎ ሌላ ነገር ማሠብ የሚቻል አይደለም፡፡ ይግባኝ ባይም ይህን እንዲከላከል ብይን ቢሠጣቸውም መከላከያ የለኝም ብለዋል፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ሟች የሞቱት በይግባኝ ባይ በተፈጸመባቸው ምት ነው በማለቱ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ሟች የሞተው በእኔ ምክንያት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የሚያነሱት ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በመቀጠልም ይግባኝ ባይ ሟችን መትተው መግደላቸው ቢረጋገጥ ለጥፋተኛ የተባሉት ጥፋተኛ መባል ባለባቸው የሕግ አንቀጽ ነው ወይ? የሚለውን መርምረናል፡፡ ማችና ይግባኝ ባይ የቆየ ጥል የላቸውም ይግባኝ ባይና ሟች ድርጊቱ በተፈጸመበት ዕለት በአንድ ላይ አረቂቤት እንደገቡ እና አብረው በሰላም ሲጠጡ እንደነበር 1ኛ የዐ/ሕግ ምስክር አስረድተዋል፡፡ ከዚያ በኋላ በተፈጠረው የሟች ሞቅትና ጠጭወችን መረበሽ ሣቢያ ይግባኝ ባይ አትረብሽ በማለታቸው ሟች ተነስተው ይግባኝ ባይን በቦክስ የመቱበት ኑኔታ በተመችው ወገን የሚሠነዘር ቅጽበታዊ ምላሽ ሞትን ቢያስከትልም ይህ ሁኔታ ይግባኝ ባይ ጥፋተኛ የተባሉበትን የሕግ አንቀጽ የሚሸፍን መሆን አለመሆኑ ሲመዘን አድራጐቱ ቅጽበታዊ እና ደምን የሚያፈላ ድንገተኛ በሆነ ሁኔታ በደረሠባቸው የቦክስ ምት አጠገባቸው ባገኙት ጠርሙስ ሰንዝረው ሟችን የመቱበት ሁኔታ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 541/ለ/ ላይ የተመለከተውን የሚሸፍን አንድ የወንጀል ህግ አንቀጽ 540 አይደለም፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ባይ ድርጊት አንቀጽ 540 ይሸፍናል በማለት ጥፋተኛ መባላቸው በአግባቡ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ይግባኝ ባይን ጥፋተኛ ያለበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሆነ ሥርዓት ቁጥር 113/2/ መሠረት ለውጠን ይግባኝ ባይ የወ/ሕግ አንቀጽ 541/ለ/ የተላለፈ ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡

በመጨረሻም በተመለከትነው ይግባኝ ባይ ጥፋተኛ የተባሉበት የሕግ አንቀጽ ስለተለወጠ ቅጣቱም በዚያው መጠን ተስተካክሎ መወሠን ስላለበት በይግባኝ ባይ ላይ ሊወሠን የሚገባው ቅጣት ምን ያህል መሆን አለበት? የሚለውን ነው፡፡

ይግባኝ ባይ ተለወጠ ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ አንቀጽ የያዘው የቅጣት መጠን ከ5 ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በይግባኝ ባይ ላይ የተወሠነው 5 ዓመት ጽኑ እስራት ነው፡፡

ቅጣት ሊወሠን ደግሞ ስለ ቅጣት አወሣሠን በወንጀል ሕጉ የተቀመጠውን መርህ በመከተለል የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን እና የወንጀለኛውን ሁኔታ፣ የአፈጻጸሙንና የፈጸመበትን መሣሪያ ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር በይግባኝ ባይ ላይ ሊወሠን የሚገባው ቅጣት ምን ያህል መሆን አለበት የሚለውን ለመወሠን በይግባኝ ባይ ላይ ቅጣትን ለማክበድ የሚያስችል ምክንያት ሊታይ የቀረበ የለም፡፡ በአንፃሩ ግን ይግባኝ ባይ ሟችን የመረተት በመጀመሪያ ሟች ከመቷቸው በኋላ መሆኑ እና ከመቱም በኋላ ሟች በህክምና

እንዲረዱ ያደረጉት ጥረት ቅጣትን ለማቅለል እንደሚያገለግሉ በህጉ በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም በሕጉ ላይ ስለቅጣት አወሣሠን የተደነገገውን መሠረት አድርገን ይግባኝ ባይ ለፈጸሙት ድርጊት ያርማችዋል ያስተምራቸዋል ባልነው ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ የታሠሩት የሚታሠብላቸው ሆኖ በ3 /ሶስት/ ዓመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ በወ/መ/ሕግ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት ተወስኗል፡፡

ት እ ዛ ዝ

- የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት በይግባኝ ባይ ላይ ተሻሽሎ የተወሠነውን ቅጣት ተቆጣጥሮ እንዲያስፈጸም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
- የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ባይ ላይ አስተላልፎት የነበረው ውሣኔ መሻሻሉን እንዲያውቀው የውሣኔው ግልባጭ ይላክለት ብለናል፡፡
- መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

<u>ተጨማሪ ትዕዛዝ</u>

- ቁጥሩ 60736 የሆነው የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ ብለናል፡፡

የዳኞች ፊርማ - ዳኜ መላኩ

አማረ አሞኜ

ከድር አልይ

ወ/ፈ

https://chilot.me

የወ/ይግ/መ/ቁ. 40638

ኅዳር 26 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

አማረ አሞኜ

ከድር አልይ

ይግባኝ ባይ፡- ወ/ገብርኤል አስገዶም ቀረቡ፡፡

መልስ ሰጪ፡- የፌ/ዓቃቤ ሕግ አቶ ሺበሺ ይግዛው ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

ይህ ይግባኝ የቀረበው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 60132 ሐምሌ 15 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ባይ ቅር ተሰኝተው ነሐሴ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. የተዛፈ የይግባኝ ማመልከቻ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ዓቃቤ ሕግ በይግባኝ ባይ ላይ 1ኛ የወ/መ/ሕግ ቁጥር 526/2/ የተመለከተውን ተላልፈው ግንቦት 21 ቀን 1994 ዓ.ም. ከቀኑ 7፡30 ሰዓት ቱርቦ ገልባጭ መኪና እያሽከረከሩ ከአዲስ አበባ ወደ አቃቂ አቅጣጫ ሲጓዙ ቃሊቲ ገብርኤል ፊት ለፊት ከተቃራኒ አቅጣጫ መሉ ሰው ጭኖ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ የነበረን ሎንቺና የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ገጭተው ከመንገድ ውጭ ወጥቶ እንዲገለበጥ አድርገው በሎንቺናው ውስጥ ከነበሩ ተሣፋሪዎች መካከል 5 /አምስቱ/ በማድረጋቸው በፈጸሙት ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት ሰው በመግደል ወንጀል ተከሣዋል 2ኛ/ የወ/መ/ሕግ ቁጥር 543/2/ የተመለከተውን ተላልፈው ከላይ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ቀን፣ ጊዜና ቦታ ላይ ገጭተው በገለበጡት መኪና ውስጥ ከነበሩት ተሣፋሪዎች መካከል ስማቸው በክሱ ላይ በተዘረዘሩ 9/ዘጠኝ/ ሰዎች ላይ በቸልተኝነት የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ፈጽመዋል የሚሉ ሁለት ክሶች መስርቶባቸው ፍ/ቤት ቀርበው ድርጊቱ ተፈጽሟል ጥፋተኛ ግን አይደለሁም ስላሉ ዓቃቤ ሕግ አለኝ ያለውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ አቅርቦ ካሠማ እና ይግባኝ ባይም የበኩላቸውን የመከላከያ ማስረጃ ካሠሙ በኋላ መዝገቡን መርምሮ አልተከላከሉም በማለት

የተከሰሱባቸውን አንቀጾች ማለት የወ/መ/ሕግ ቁጥር 526/2/ ወደ 526/1/ እና 543/2/ ወደ 543/1/ ለውጦ ጥፋተኛ ካለ በኋላ ሁሉቱንም አጣምሮ በ3 /ሦስት/ ዓመት ከ6 /ስድስት/ ወር እስራት እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡

የአሁኑ ይግባኝ የቀረበው በዚህ የፍ/ቤቱ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ሲሆን ይህ ፍ/ቤትም የወ/መ/ሕግ ሥ/ሥ/ቁጥር 192 በደነገገው መሠረት ግራ ቀኙን አስቀርቦ የይግባኝ ክርክራቸውን ሠምቷል፡፡

ይግባኝ ባይ ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ያነሷቸው የቅሬታ ነጥቦች ድርጊቱ የተፈጸመው በድንገተኛ አጋጣሚ እንጂ በእኔ ቸልተኝነት አይደለም፡፡ ስለሆነም ጥፋተኛ ያለኝ ባግባቡ አይደለም ቅጣቱም እኔ ምንም የወንጀል ሪኮርድ የሌለኝና የብዙ ቤተሰብ አስተዳዳሪ ስለሆንኩ የተወሰነብኝ ቅጣት በጣም በዝቷል፡፡ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ኢንሹራንስ ካሣ የከፈለው አደጋው ከቁጥጥር ውጭ መሆኑን ተገንዝበን ነው፡፡ በመሆኑም በደረሰብኝ አደጋ እኔም ሆነ ቤተሰቤ በከፍተኛ ችግር ላይ ስለወደቅን በበቂ ያሠናብተኝ ይህንን ቢያልፈው ቅጣት ያቅልልኝ ያሉ ሲሆን የመሠረትነውን ክስ በባለ ሙያ ምስክርነት አስደግፈን ከጥርጣሬ ውጭ አስረድተናል ቅጣቱ ካደረሱት ጉዳት አንፃር በዛ የሚባል አይደለምና የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ይጽናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም ይግባኝ ባይ የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ቸልተኛነታቸውን ያቋቁማል? ወይንስ አያቋቁምም? ያቋቁማል ከተባለስ የተወሰነባቸው ቅጣት ተመጣጣኝ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦችን ይዘን ክሱን፣ የቀረበውን ማስረጃ እና ግራ ቀኙ ያካሄዱትን ክርክር አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

በመጀመሪያ የመረመርነው የይግባኝ ባይ ድርጊት የቸልተኝነት ወንጀልን ያቋቁማል? ወይንስ አያቋቁምም? የሚለውን ሲሆን ክሱን ለማስረዳት የዐቃቤ ሕግ 8 ምስክሮችን አቅርቦ ያስመሰከረ ሲሆን አብዛኞቹ በመኪና ውስጥ /በሌሎች/ የነበሩ በመሆኑ የአደጋ ሰለባ መሆናቸውን ሲሆን አደጋው በደረሰበት ስፍራ ከውጭ የነበሩት 22ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር

ኃይለማርያም ገዛኸኝ ይግባኝ ባይ መኪናቸውን በፍጥነት ሲያሽከረክሩ ከፊት ለፊታቸው ካለ መኪና ሲደርሱ የመኪናውን ፍጥነት ለመግታት ተስኗቸው መስመራቸውን ለቀው ግራ መንገድ ላይ በመግባት በተቃራኒ አቅጣጫ ቀኝ መስመሩን ይዞ የመጣ የነበረውን ሰው የጫነ መኪና ገጨትና መኪናው ተገለበጠ በማለት የመሠከሩትና የአደጋ ቦታ ፕላኑን እያዩ የመሰከሩት የሙያ ምስክር ይግባኝ ባይ ቀኝ መስመራቸውን ለቀው በተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣን መኪና መንገድ 2 ሜትር ከ35 ሳ/ሜትር የራሣቸው ባልሆነ መንገድ ገብተው ገጭተዋል ይህም በጥንቃቄ ጉድለት በቸልተኛነት ሲያሽከረክሩ ያደረሱት አደጋ ነው በማለት መስክረዋል፡፡

ይህ የዓይን ምስክሩ እና የሙያ ምስክሩ የሰጡት ቃል በአንድ ላይ ሲታይ ተመሣሣይና አንዱ የሰጠውን ምስክርነት በሚደግፍ መልኩ ሌላኛውም የደገመው በመሆኑ የይግባኝ ባይ ድርጊት የቸልተኝነትን ወንጀል የሚያቋቁም በመሆኑ ድርጊቱ ድንገተኛ አጋጠሚ እንጂ ቸልተኝነትን አያሣይም በማለት የሚያነሱት ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በመጨረሻ የመረመርነው የቅጣቱን ተመጣጣኝነት ሲሆን ይግባኝ ባይ ጥፋተኛ የተባሉባቸው ድንጋጌዎች ጥፋተኛ የተባሉበት የወ/መ/ሕግ ቁጥር 526/1/ በገንዘብ መቀጮ ወይም በእስራት እና የወ/መ/ሕግ ቁጥር 543/1/ ከ6 ወር በማይበልጥ እስራት ወይም በገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጡ የተደነገገ ሲሆን ይግባኝ ባይ የተቀጠሩት የሁለቱ ተጣምሮ በ3 ዓመት ከ6 ወር እስራት ነው፡፡ ይህም ጥፋተኛ የተባለባቸው ድንጋጌዎች የያዙትን የእስራት አማራጭ ጣሪያውን ነው፡፡

የወንጀል ቅጣት ሲወሰን በወንጀል ሕጉ ስለ ቅጣት አወሣሠን የተደነገጉትን በመከተል መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ፍ/ቤትም የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን በተመለከተ ይግባኝ ባይ የፈጸሙት ድርጊት ተደራራቢነት እና የደረሰውም ጉዳት ከባድነት ቅጣት እንደሚያከብድባቸው በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ በተከሣሽ ላይ የቅጣት ሪከርድ አለመቅረቡ ይህንን ወንጀል እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የዘወትር ጠባዩ መልካም

እንደነበር ይገመታል በማለት ካሠፈረ በኋላ ተከሣሽ አንዳችም የቅጣት ማቅለያ በሕግ የተደገፈ ምክንያት አላቀረበም በማለት ጥፋተኛ የተባለባቸው አንቀጾች የያዙትን ከፍተኛውን ቅጣት ወስኖባቸዋል፡፡

ነገር ግን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82/1ሀ/ የዘወትር መልካም መሆንና ያጠፋውም በእውቀት ማነስ፣ ባለማወቅ፣ በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ እንደሆነ የቅጣት ማቅለያ ሆኖ እንደሚያገለግል የተደነገገና የይግባኝ ባይ ድርጊትም ያልታሰበና ድንገኛ አጋጣሚ ለመባል የሚችል እንደመሆኑ የይግባኝ ባይ ያለፈ ጠባይም መልካም እንደነበር የስር ፍ/ቤት ክስ እስከተረጋገጠ ድረስ የቅጣት ማቅለያ አንድ ምክንያት ሆኖ ከማክበጃ ምክንያቶች በተቃራኒ በማመዛዘኛነት ሊጠቀምበት ሲገባ ይህ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መታለፍ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በይግባኝ ባይ ላይ ያስተላለፈውን የጥፋተኛነት ውሣኔ በማጽናት ቅጣቱን በተመለከተ ከፍ ሲል የጠቀስነውን የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ግምት ውስጥ በማስገባት በስር ፍ/ቤት የተወሰነባቸውን የ3 ዓመት ከ6 ወር እስራት በወ/መ/ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195/2/ለ/2/ መሠረት በማሻሻል ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ የታሠሩት እየታሰበላቸው በ2 /ሁለት/ ዓመት እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት በይግባኝ ባይ ላይ ተሻሽሎ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት ተቆጣጥሮ እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

የሥር ፍ/ቤት በይግባኝ ባይ ላይ አስተላልፎት የነበረው ውሣኔ ቅጣቱ ብቻ መሻሻሉን እንዲያውቀው የዚህ ውሣኔ ግልባጭ ይላክለት ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የዳኞች ፊርማ፡- ዳኜ መላኩ
አማረ አሞኜ
ከድር አልይ

ነ/ዓ

https://chilot.me

የሰበር መ.ቁ. 29363

18/03/2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ አምደ - ጠበቃ አስናቀ ከፋለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥላሁን አርምዴ ከጠበቃ ሰብስቤ ባልቻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ የወንድሜ ልጅ በመሆኑ ከባለቤቱ ሞት በኋላ አብሮኝ እንዲኖር በወረዳ 23 ቀበሌ 10 በሚገኘው ቁጥር 190 በሆነው ቤት አስጠግቼው ሲኖር የግል ሀብቴን ለመውሰድና ለመጠቀም አስቦ ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም አሞኝ በነበረበት ወቅት እንደማላነብና መሐይም መሆኔን በማወቅ የስጦታ ውል አዘጋጅቶ አስፈርሞኛል፡፡ ከዚያም በጥር ወር 1991 ዓ.ም ቤተክርስትያን ሄጄ ስመለስ ወደ ቤቴ እንዳልገባ ከልክሎኛል ስለሆነም ነሐሴ 9/1984 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱት ክርክርም በዚህ ጉዳይ አስቀድመው በከተማ ነክ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ተቀባይነት ሣያገኝ የቀረ ሲሆን በዚያው ጉዳይ በድጋሚ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም፡፡ የስጦታ ውሉ ይሻርልኝ ተብሎ የቀረበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚሉ ናቸው፡፡ በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም የስጦታ ውሉ በሕግ አግባብነትና በአመልካች ሙሉ ፈቃደኛነት እንደተደረገ ጠቅሰው ሊሻር ይገባል ተብሎ የቀረበ አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ አስቀድሞ ጉዳዩ ውሣኔ አግኝቷል በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ አስቀድሞ ለከተማ ነክ ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረው አቤቱታ ሁከት ይወገድልኝ በማለት እንጂ የስጦታ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ስላልሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 መሠረት መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ይርጋን አስመልክቶ ተጠሪ ያቀረቡትን መቃወሚያ በተመለከተም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 መሠረት የይርጋ መቃወሚያ ማቅረብ የሚቻለው ውሉ ሲመሰረት የችሎታና የፈቃድ ጉድለት አለበት በሚባልበት ጊዜ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁት ችሎታና ፈቃድ መሠረት አድርገው ሣይሆን መሐይም ነኝ በማለት ስለሆነ የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 ሥር ስለማይሸፈን አቤቱታው በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ የማይንቀሣቀስ ንብረት ስጦታ በሚደረግበት ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 መሠረት ግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት ሥርዓት ሊደረግ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443 ላይ የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን በማስረጃነት የቀረበው የስጦታ

ውል ሲታይ ግን ስጦታ አድርገውና ምስክሮች ባሉበት ከተነበበ በኋላ የተፈረመ ስለመሆኑ ስለማያስረዳ ፈራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይ የስጦታ ውሉ እንዲፈረስ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት በይርጋ ቀሪ አልሆነም ማለቱ ተገቢነት በሌለው ሁኔታ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በአመልካች በኩል የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ግራቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙ አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት የስጦታ ውል ይፍረስልኝ አቤቱታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይርጋ ቀሪ ሆኗል መባሉ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከዚሁ ጭብጥ አኳያም አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም ታምሚ በነበረበትና መሐይም መሆኔንም በማወቅ የመኖሪያ ቤት የስጦታ ውል ያስፈረመኝ ስለሆነ ይሄው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ይባልልኝ በማለት ነው፡፡

ስጦታ እንዲቀነስ ወይም እንዲሻር የሚቀርብ አቤቱታ ስጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ እስከ 2 ዓመት ባለው ጊዜ ለዳኞች ካልቀረበ ዋጋ እንደሌለው / በይርጋ እንደሚቋረጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡

አመልካች የስጦታ ውሉ ተፈርሟል የሚሉት ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም ሲሆን ይሄው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ይባልልኝ በማለት ክስ ያቀረቡት ደግሞ ሰኔ 1 ቀን 1993 ዓ.ም ዘጠኝ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ወራት ሲቀር ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም የተፈረመው ሰነድ የስጦታ ውል መሆኑን ያወቅሁት የካቲት 8 ቀን 1991 ዓ.ም በሚመለከታቸው ክፍሎች አቤቱታ ሣቀርብ ነው ያሉትን በመውሰድ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንኳ ክስ እስካልቀረቡበት ሰኔ 1 ቀን 1993 ዓ.ም ያለው ሲታሰብም 2 ዓመት እንዳለፈው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም የፌዴራል ከፍ/ቤት አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል ያለው በፍ/ብ/ቁ. 1810 ላይ እንደተመለከተው በ2 ዓመት ጊዜ አልቀረበም በማለት ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው የስጦታ ውል እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ ግንኙነት በተለይ የሚገዛው በፍ/ብሔር ሕጉ ስጦታን አስመልክቶ በተደነገጉት ድንጋጌች መሠረት ሲሆን ወደ ጠቅላላ የውሎች ሕግ ድንጋጌዎች መሄድ የሚቻለው በልዩ ሕግ ላይ ተመስርቶ ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት ካልተቻለ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ከስጦታ ውል ድንጋጌዎች አኳያ መርምሮ ለይርጋ ክርክሩ እልባት መስጠት ሲገባው ስለ ውሎች በጠቅላላው በሚለው ምዕራፍ ሥር የተደነገገውን የይርጋ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠቱ ከሕግ አተረጓጎም መርህ አንፃር ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1810 ላይ የተመለከተውና ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ ከ2 ዓመት በኋላ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ አይቀርብም ተብሎ የተመለከተውም ውሉ በችሎታና በፈቃድ ረገድ ጉድለት በሚኖረው ጊዜ ነው፡፡ መሐይምነትን ወይንም ዓይነስውርነትን አስመልክቶ የሚቀርብ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ከውሉ የአፃፃፍ ሥርዓት /ፎርም/ ጋር ተያይዞ እንደሚነሣ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1719 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል እንደመሆኑ መጠን

የዚህ ዓይነቱ ጥያቄም በይርጋ የሚታገደው በቁጥር 1845 እንጂ በቁጥር 1810 ላይ እንደተደነገገው ስላልሆነ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ለድንጋጌው የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 64 በ17/6/95 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡

2/ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 18957 ጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጠው ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ሲሆን ከውጤት አኳያ የሚነቀፍ ስላልሆነ እንደዚሁም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23712 ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም ይህንኑ ውሣኔ ማጽናቱ ከውጤት አኳያ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡

3/ አመልካች የስጦታ ውል ይፍረስልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441/1/ መሠረት በ2 ዓመት ጊዜ ስላልቀረቡ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስነናል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሀሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2434 ድንጋጌዎች መሠረት ጥብቅና በግሏ ብቻ አመልካች ሆነ ብላና አስባበት ልትፈጽመው የሚገባው ተግባር /ስጦታ/ አልፈፀምኩም እያለች ተከራክራለች። አመልካች ተጠሪ አሳስቶ የስጦታ ውል ያስፈረምኩኝ መሆኑን ያወቅሁት በጥር ወር 1991 ዓ.ም ነው በማለት ተከራክራለች። እንደዚህ ከሆነ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከጥር ወር 1991 ጀምሮ መሆን ይገባዋል። ውሉ በተንኮል ተቀነባብሮ አመልካች ሣታውቅ የተፈረመ ነው የሚል ክርክር ያለበት በመሆኑ የይርጋ የጊዜ ገደቡም በተንኮል የተዘጋጀ ውል ይታወቅ መፈረሙን ካወቀችበት ከጥር ወር 1991 ዓ.ም ጀምሮ ባለው አስር ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት። ምክንያቱም ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 እንጅ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2441 አይደለም የሚል አምነት አለኝ። ስለሆነም ወደ ዋናው ጉዳይ ተገብቶ የስጦታው ሕጋዊነት መመርመር አለበት። የይርጋ ጊዜ አልፎበታል ተብሎ መዘጋቱ ተገቢ አይደለም የሚል እምነት ስላለኝ ከሙያ አጋሮቸ በሃሣብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ተ.ወ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 31906

4/3/2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ሒሩት አሥራት

ተጠሪ፡- የአቶ መርስኤ መንበሩ ወራሾች አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ለዚሁ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሚች አባታችን በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 3 ቀበሌ 53 ክልል ቁጥር 849 የሆነውን ቤት በ1957 ዓ.ም. ከቀድሞ ባለ ርስት በጭሰኝነት ተመርተው ተገቢው ኪራይ እየከፈሉ ሲገለገሉ የቆየ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ የባለርስትና የጭሰኛ ግንኙነት በመቋረጡ የአፈር ግብር ለመንግሥት እየከፈሉ የቆዩ ቢሆንም የቤት ባለቤትነት ደብተር ለማውጣት በቦታው ላይ ይዞታ እንደነበራቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከፍ/ቤት አስመስክረንና አረጋግጠን እንድንቀርብ የተጠየቅን በመሆኑ የቤት ባለቤትነት ደብተሩን ማግኘት እንድንችል በቦታው ላይ ይዞታ ያለን ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጠን በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በተጠሪነት ያጣመሩት ባለመኖሩ ፍ/ቤቱ የአመልካካቾችን ምስክሮች ሰምቶ የአመልካቾች አባት ቦታውን በ1959 ዓ.ም. ከልዕልት ተናኘ ወርቅ ላይ በጭሰኝነት ተመርተው ውሃና መብራት በማስገባት ቤት ሠርተው የጋራዥ ድርጅት አቋቁመው ሲሰሩበት እንደበር አዋጅ ቁጥር 47/67 ከታወጀ በኋላ የቦታና የቤት ግብር

ለመንግሥት ሲከፍል እንደነበር በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ይሄው ተገልጾ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍላቸው በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ በወቅቱ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት አመልካቾች በይዞታቸው ሥር እንደሆነ ተገልጾ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ የተሰጠበት ድርጅት በአዋጅ 47/67 መሠረት የተወረሰና የሚያስተዳድረው መሆኑን ገልጾ በሌለበት የተሰጠው ትዕዛዝ መብቱን እንደነካ በመግለጽ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት በተቃዋሚነት ወደ ክርክሩ ለመግባት ጠይቆ በተፈቀደለት መሠረት ወደ ክርክሩ በመግባት ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ክርክር የተነሳበት ድርጅት በአዋጅ 47/67 መሠረት ተወርሷል አልተወረሰም የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር መወረሱ ስለተረጋጠ አመልካቾች ከአዋጅ 47/67 መንፈስ ውጭ ተወስዶብናል የሚሉ ከሆነ ይህንኑ ጥያቄያቸውን በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ከሚያቀርቡ በስተቀር በተያዘው መዝገብ እንደማይስተናገድ ጠቅሶ አስቀድሞ ለአመልካቾች ይዞታ ያላቸው መሆኑ ተጠቅሶ እንዲፃፍላቸው የተሰጠው ትዕዛዝ ሊነሳ ይገባል በማለት አንስቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙ አከራክሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጅት በይግባኝ ባዮች ይዞታ ሥር እንደነበርና በአዋጅም እንዳልተወረሰ የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያረጋግጡ እንደመሆኑ መጠን መልስ ሰጭው ድርጅቱ መወረሱን ባላረጋገጠበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት ድርጅቱ መወረሱ ተረጋግጧል በማለት አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ ማንሣቱ በአግባቡ አይደለም ሲል በመሻር የቀድሞው ትዕዛዝ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ሰበር ችሎትም ይሄው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ሳይቀረበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ በሚያከራክረው ንብረት ላይ ተጠሪዎች የይዞታ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ነው ተብሎ የአመልካች መቃወሚያ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን ጠርቷል፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች በአድራሻቸው ሊገኙ ባለመቻላቸው በጋዜጣ ተጠርተው ስላልቀረቡ በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ በቃል ክርክርም ጊዜ ስላልቀረቡ ችሎቱ የአመልካችን የቃል ክርክር ብቻ አዳምጧል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆነ ችሎቱም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በቅድሚያ ችሎቱ የተመለከተው አመልካቾች አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችልና ዳኝነት የሚያፈልገው /Justicable/ መሆኑን በተመለከተ ነው፡፡

ተጠሪዎች በከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የንግድ ድርጅት ላይ የይዞታ መብት ያለን መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጠን በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች የዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ከፍ/ቤቱ እንዲሰጣቸው የጠየቁትም የቤት ባለቤትነት ደብተር ከሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ለማግኘት እንደሆነም በአቤቱታቸው ላይ ጠቅሰዋል፡፡

የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 ላይ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በመንግሥት የአስተዳደር መ/ቤት በኩል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደዚሁም የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት ሥርዓት የአስተዳደር መስሪያ ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት እንደሚወሰንም በዚሁ ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ሰው በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ማግኘት የሚችለው ከሚመለከተው የመንግሥት አስተዳደር መስሪያ ቤት በኩል ሲሆን የሚመለከተው የመንግሥት አስተዳደር መ/ቤት የምስክር ወረቀት አሰጣጡን አስመልክቶ በሚያወጣው የምስክር ወረቀትም እንደሚሰጥ መረዳት ይቻላል፡፡

ሕጉ በዚህ መልኩ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት እንደሚሰጥ ከደነገገ የምስክር ወረቀቱን ለማግኘት እንዲቻል የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰጥ ፍ/ቤትን መጠየቅ ከነመነሻውም ቢሆን ጉዳዩ በፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት የሚያስፈልገው /Jusciable matter/ እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት በፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ቤት ሊስተናገድ እንደማይችል ግልጽ በመሆኑ ከመነሻውም ቢሆን ፍ/ቤቱ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት መመለስ ሲገባው ጉዳዩን ማስተናገዱ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ የቀድመውን ትዕዛዝ መሰረዙ ከውጤት አኳያ ተቀባይነት ነበረው፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይህንኑ ትዕዛዝ ምክንያቱን ለውጦ ሊያጸናው ሲገባ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጅት መወረሱ አልተረጋገጠም በማለት መሻሩ ጉድለት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከተማው ይግባኝ ሰማ ሰበር ችሎትም መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ይህንኑ ጉድለት ሳያርም መቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አላገኘነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. ዐ1998 ሚያዝያ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እንደዚሁም ይግባኙ ችሎቱ በመ/ቁ. ዐዐ682 በ30/3/97 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት በአብላጫ ድምጽ ሽረነዋል፡፡
2. ተጠሪዎች የቤት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት እንድችል የይዞታ መብት ያለን መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከፍ/ቤቱ ይሰጠን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ለፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት ሊሰጥበት የማይችል ጉዳይ /Justicable matter/ ስላልሆነ አቤቱታው ከመነሻውም ቢሆን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ነበር በማለት ወስነናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡንዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የሀሣብ ልዩነት</u>

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ በመጀመሪያ ተጠሪዎች ክርክር የተነሳበትን ቤትና ቦታ በከፍተኛ 3 ቀበሌ 53 ፍርድ ሸንጎ ውሣኔ መሠረት መያዛቸውን አንስተው የተከራከሩ በመሆኑና አመልካችም በበኩሉ ተጠሪዎች ኪራይ እንዲከፍሉ ሚያዝያ 5 ቀን 1981 ዓ.ም. በቀበሌ ሸንጎ አስወስኛለሁ የሚል ክርክር ያለው በመሆኑ የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ጥር 26 ቀን 1973 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና ሚያዝያ 5 ቀን 1981 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት ይህ ሰበር ችሎት በተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በትዕዛዙ መሠረት መዝገቡ አልተገኘም የሚል ምላሽ የቀረበ ሲሆን እነዚህን አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች የፍርድ ባለ መብት ሁነንባቸዋል የሚላቸውን ውሣኔዎች

በማግኘት የሚያስችል ሌላ ተለዋጭ ትዕዛዝ መስጠቱን በአዋጅ ቁጥር 47/1967 በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የቀበሌ ሽንጎዎች የሰጡት አስገዳጅ ውሣኔ መኖር አለመኖሩን በማጣራት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ይገባ ነበር። ይህ ሣይደረግ መዝገቡ አሁን ባለበት ሁኔታ መርምሮ ውሣኔ መስጠቱ፣ ተገቢ አይደለም የሚል ዕምነት አለኝ።

በሁለተኛ ደረጃ የአንድ ቦታና ንብረት ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኔ በፍርድ ይረጋገጥልኝ የሚል ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ወይም በፍርድ ቤት ክስ ሊቀርብበት ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችል /Justicable/ አይደለም የሚለውና የአብላጫው ድምጽ መደምደሚያ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነው ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም ይዞታን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት የመስጠት ስልጣን የአስተዳደር አካላት መሆኑ የማይካድና የይዞታ የምስክር ወረቀትም በአስተዳደር ደንብ መሠረት መከናወን ያለበት መሆኑ ያማያከራክር ቢሆንም የሕጉን ሥርዓትና ደንቡን ያሟላ ባይዞታዎች በአስተዳደር በኩል የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ጠይቀው አላግባብ ቢከለከሉ ይህንንም እስከ መጨረሻው አስተዳደራዊ እርከን ድረስ ለማሣረም ሞክረው የይዞታ የምስክር ወረቀት አታገኙም ተብሎ ቢወስንባቸው ይህንን አስተዳደራዊ ውሣኔ በመቃወም ሕጉንና ደንቡን አሟልተው በቦታው ላይ የሚገኙ ሕጋዊ ባለይዞታዎች መሆናቸውን በፍርድ እንዲረጋገጥላቸው ከመጠየቅ የሚገድባቸው ሕግ የሌለ በመሆኑ ጉዳዩ የክስ ምክንያት የለውም በሚለው መደምደሚያ ባለመስማማት ከሙያ አጋሮቼ በሀሣብ ተለይቻለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረትና ቦታ ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኔ በፍርድ ይረጋገጥልኝ የሚለው ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም የሚባል ከሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አንድ የማይነቀሳቀስ ንብረት በይዞታቸው ሥር በማድረግ ለአስራ አምስት ዓመት ግብር እየገበሩ የኖሩ ሰዎች አስተዳደሩ ለአስራ አምስት ዓመት የቦታውና የንብረቱ ባለይዞታ መሆናቸውን እና

በስማቸው ግብር መክፈላቸውን የሚያረጋግጥ የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ባይቀርብላቸው ይህንን በማስረጃ በማጣራት ፍርድ ቤቱ የንብረቱ ባለይዞታ ብቻ ሣይሆኑ የንብረቱ ባለቤት መሆናቸውን በፍርድ እንዲያረጋግጥላቸው የሚያቀርቡትን ጥያቄ በፍርድ ቤት ሊወሰን አይችልም በሚል መንገድ፣ የሚዘጋበት የሕግ አተረጓጎም እና መደምደሚያ የሚያስከትል ይሆናል። ይህ ደግሞ ሰዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 ንዑስ አንቀጽ 1 የተረጋገጠላቸውን መብት በአስተዳደር አካላት ቢጣስ በፍርድ ቤት ክስ አቅርበው መብታቸውን እንዲያረጋግጡ የሚያደርግ በመሆኑ በጥንቃቄ መታየት አለበት የሚል ሀሣብ አለኝ።

በአጠቃላይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ከዚህ በፊት ስልጣን ባላቸው አካላት ታይቶ የተወሰነ መሆኑን ተከራካሪዎቹ ካደረጉት ክርክር ለመረዳት የሚቻል ሲሆን፣ ይህ ችሎትም እነዚያን ውሣኔዎች ይዘትና ምንነት በመመርመር ለመወሰን የሚያስችለውን ሥርዓት መከተል ነበረበት። በሌላ በኩል የይዞታ መብት ጥያቄና ይዞታን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የማግኘት ጥያቄ በባሕሪው በፍርድ ቤት የማይታይና ክስ የማይቀርብበት ጉዳይ አይደለም። አስተዳደሪዊ መፍትሔዎችን አሟጥጦ የጨረሰ ሰው እስከመጨረሻው እርካን ድረስ ባለው አስተዳደራዊ መዋቅር የተሰጠው ውሣኔ ሕጋዊ የይዞታ መብቱ እውቅና የማይሰጥና መብቴን የሚሸራርፍ ነው ብሎ ሲያስብ በበቂ ማስረጃ ለፍርድ ቤቶች ክስ ማቅረብና የቦታውና የነብረቱ ሕጋዊ ባለ ይዞታ መሆኑን፣ በፍርድ እንዲረጋገጥለት መጠየቅና ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን አይተው ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን አላቸው በማለት አብላጫው ድምጽ ከሰጠው የሕግ ትንተና ከደረሰበት መደምደሚያ በሀሣብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ

https://chilot.me

የሰ/መ/ቁ. 32865

ኅዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሰ
ተሻገር ገ/ስላሴ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- 1. ወ/ሪት ሸዋነሽ ተስፋዬ ┐ ጠበቃ ወ/ሰማያት ገ/ወልድ ቀረበ
2. ተማሪ ፍቃዱ ተስፋዬ ┘

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ፀዳለ ወርቁ
2. አበራ ሞላ ጠበቃ ወ/ስላሴ ብርቱ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የንግድ ቤት እንዲለቀቅ በሚል የቀረበውን ክስ መሰረት ተደርጉ የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት የአሁኖቹ አመልካቾች ናቸው በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱትም 1ኛ ተጠሪ አከራይ፤2ኛው ደግሞ ተከራይ በመሆን ከአባታችን በውርስ የተላለፈልንን ንግድ ቤት ያለአግባብ የያዘብን ስለሆነ መልሰው ያስረክቡን፣ለተጠቀሙበት ጊዜ ሊከፈል የሚገባው ኪራይም ይክፈሉን በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ከሣሾች የንግድ ቤቱ የተከራየ ስለመሆነ አላስረዱም፡፡ 1ኛ ተጠሪም እንደከሣሾች ወራሽ ስለሆነች ንግድ ቤቱን አስረክቢ ልትባል አይገባም፡፡ በማለት ወስናአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካቾች ነሐሴ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በግራ ቀኝ ወገኖች ያለውን ክርክር ሰምተናል፡፡

https://chilot.me

1ኛ ተጠሪ ሞታለች ስለተባለ እና ወራሾችም ሊገኙ ስላልቻሉ ክርክሩ የተደረገው በአመልካቾች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ነው። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎች አንስተው ባልተከራከሩበት ነጥብ ላይ ውሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ለመመርመር ነው። በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

ከላይ እንደአመለከትነው አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት ያለአግባብ ተይዞብኛል የሚሉት ንግድ ቤት እንዲወሰንላቸው እና ኪራይም እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ነው። 2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ የንግድ ቤቱን (የሉካንዳ ንግድ ቤት) ከ1ኛ ተጠሪ ተከራይቶ እንደነበር፣ነገር ግን መልሶ እንዳስረከበ በመግለጽ እንደተከራከረ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በግልጽ ተመልክቶአል። 1ኛ ተጠሪም ብትሆን ቤትን ለማከራየቱ የጽሑፍ ማስረጃ አልቀረበም ከማለት ውጪ ለ2ኛ ተጠሪ አሳልፋ አለመስጠትዋን በማስመልከት ያቀረበችው ክርክር እንዳልነበር ለመገንዘብ ችለናል። በአጠቃላይ ተጠሪዎች ከአከራይ እና ተከራይ በመሆን ለክሱ ምክንያት የሆነውን ንግድ ቤት አለመያዛቸውም ሆነ ለአመልካቾች እንዲመልሱ የሚገደዱበት ሕጋዊ ምክንያት እንደሌለ በመግለጽ አልተከራከሩም። የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠውም ይህን መሰል ክርክር መሆኑን እየተገነዘበ እንደሆነ ከውሳኔው መገንዘብ የሚቻል ነው።

ማንኛውም ፍ/ቤት ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል የተነሣውን አከራካሪ ነጥብ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ወደውሳኔ የመራው በተጠሪዎች የተሰጠውን መልስ እንዳላየ በማለፍ ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካቾች ያቀረቡት የመብት ጥያቄ ግልጽ ሆኖ ሳለ ይህን በዝምታ በማለፍ አከራካሪ ሆኖ ባልተነሳ ነጥብ ላይ ተመስርቶ መወሰኑ በክርክሩ አመራር ረገድ ጭምር ከፍተኛ ስህተት እንደተፈጸመ ለመገንዘብ ችለናል። ነገሩን አጠቃለን ስንመለከት ለክሱ መነሻ የሆነው

https://chilot.me

በቁጥር 1036 የሚታወቀው ንግድ ቤት የአመልካቾች አባት እንደሆነ አላከራከረም፡፡ ይገባናል በማለት ክስ ሊመሰርቱ የቻሉት በወራሽነታቸው እንደሆኑም ግልጽ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ 1ኛ ተጠሪ በሕይወት የሌለች ሲሆን፣ 1ኛ ተጠሪ ንግድ ቤቱን ለአመልካቾች ስለማስረክቡ ምንም ያቀረበው ማረጋገጫ የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም 2ኛ ተጠሪ ከሃላፊነት ነፃ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 127/87 ጥቅምት 29 ቀን 1993 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ይህን ውሳኔ በማጽናት በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04145 በሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት የኪራይ ይከፈለን ጥያቄ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባ በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን በተከፈተው መዝገብ እንዲቀጥል እዲያደርግ፤ለአመልካቾች ሊከፍል የሚገባ የኪራይ ገንዘብ አለ ወይስ የለም? እንዴትስ ይከፈላል በሚሉት ጭብጦች ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች ካከራከር በኋላም የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ተጠሪዎች በቁርጥ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ለአመልካቾች ይክፈሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የመጡት ማሕደሮች ወደ መጡበት ይመለሱ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

https://chilot.me

የሰበር መ/ቁ. 33200

11/3/2001

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አቶ አወል አማን - ከጠበቃ ሙሉጌታ ከበደ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ናሥር አማን

2. .. ማህሙድ አማን } ጠበቃ ደጉ ሰሊማ ..

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የውርስ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪዎች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ ሟች አባታችን አቶ አማን ይስሐቅ በአ.አ ከተማ በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል ቁጥር 355 የሆነውን ቤትና ሌሎችንም ንብረቶች አፍርተው የነበረ ሲሆን ንብረቶቹን ለመካፈል እንድንችል የውርስ አጣሪ ይቋቋምልን በማለት ጠየቀዋል፡፡

አመልካችም ቀርበው በሰጡት መልስ ሟች አባታችን የሞቱት በ29/8/1961 ዓ.ም ስለሆነ ከ34 ዓመት በኋላ የሚነሣ የውርስ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ክርክር ረገድም የተጠቀሰው ቤት በአመልካችና በባለቤቱ ዓማካኝነት ሟች ከሞቱ በኋላ በ1965 ዓ.ም የተሰራና የግል የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ንብረቱ የውርስ ሀብት ስላልሆነ የሚጣራ ባለመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሣሾች በተከሣሽ ላይ ያቀረቡት ጥያቄ ቤት ያስረክቡን በማለት ሣይሆን በጋራ ይዘነው የሚገኝና ሌሎችም የሚች የሆኑ ንብረቶች ተጣርተው የውርስ ክፍፍል እንዲደረግ በማለት ስለሆነ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ሣይቀበለው ቀርቷ። በፍሬ ጉዳዩ ክርክር ረገድም ተከሣሾች በሚች ስም የተመዘገበ ንብረት ስለሌለ ውርስ አጣሪ ሊሾም አይገባም ቢሉም አጣሪ የሚያጣራው ንብረቶችን ብቻ ሣይሆን እዳዎችንም አጣርቶ ውሣኔ የሚሰጥ ስለሆነና ቤቱም ቢሆን በማጣራቱ ሂደት የተከሣሽ ይሁን የሚች ስለሚወሰን ውርስ አጣሪ ሊቋቋም ይገባል ካለ በኋላ አጣሪውን በመሾም አጣሪውም ወርሱን አጣርተው በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘው የቤት ቁጥር 355 የሆነው ቤት የአመልካች እንደሆነና ሚች በዚህ ቀበሌ ቤት እንዳልነበራቸው በመግለጽ ሪፖርቱን ለፍ/ቤቱ አቅርበዋል።

ሪፖርቱ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አዋጅ 47/67 ሲታወጅ ተጠሪው ቤቱን ይዘው የነበረው የቤቱ ባለቤት ሆነው ሣይሆን በሞግዚትነትና በንብረት አስተዳዳሪነት ሥልጣናቸው ስለነበር አዋጅ ሲታወጅ የያዙት የውርስ ሐብት ነው በማለት የአጣሪውን ሪፖርት ሣይቀበለው ቀርቷል።

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል።

የሰበር አቤተታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ሚች ከሞቱ ከ34 ዓመት በኋላ የቀረበው የውርስ ይጣራ አቤቱታ በይርጋ ቀሪ አይሆንም መባሉ ተጠሪዎች ባሉበት ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል።

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም ጭብጥ አቤቱታው ያስቀርባል የተባለበትና የውርስ ይጣራልኝን ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ይሆናል ወይንስ አይሆንም የሚለው ነው።

ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል።

ግራ ቀኙ የሚያደርጉት ክርክር በውርስ ሀብት ክፍፍል ላይ የተመሠረተ ስለሆነ የይርጋ ክርክሩም መታየት ያለበት ከውርስ ሕጉ ድንጋጌዎች አንፃር ነው።

በዚህም መሠረት በውርስ ሕጉ ላይ ለአንዳንድ አቤቱታዎች የተለያዩ የይርጋ ድንጋጌዎች የሚገኙ ሲሆን ነገር ግን የውርስ ማጣራትን በተመለከተ ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት አልተመለከተም የግራ ቀኙን ግንኙነት በተለይ በሚገዛው የውርስ ሕጉ ላይ የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ በምን ያህል ጊዜ መቅረብ እንዳለበት ካልተደነገገ ወደ ጠቅላላ ሕግ በመሄድ ለጉዳዩ ዕልባት መስጠት በሕግ አተረጓጎም መርህ /principles of legal interpretation/ የተፈቀደ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ጉዳዩን በፍ/ብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለውሎች ከተደነገገው አንፃር ተመልክተነዋል። በዚህ ክፍልም ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆኑም እንኳን በውል ሕግ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በቁጥር 1677/1/ ላይ ተመልክቷል። በውል ሕግ ደግሞ ዋናው የይረጋ ደንብ በቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የአመልካችና የተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት ግለሰብ የሞቱት በ1961 ዓ.ም እንደሆነ ግራ ቀኙ ተማምነዋል። ተጠሪዎች ውርስ ይጣራልን በማለት ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት በ1995 ዓ.ም እንደሆነና ከ34 ዓመት በኋላ አቤቱታውን ማቅረባቸውን ተገንዝበናል።

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚለውን የአመልካች አቤቱታ ሣይቀበለው የቀረው ተጠሪዎች ያቀረቡት አቤቱታ ቤቱን ያስረክቡን በማለት ሣይሆን በጋራ ይዘነው ያለንና ሌሎችም የሟች ንብረቶች ተጣርተው

የውርስ ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በመጠየቅ ስለሆነ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ነው፡፡

ይሁንና ንብረቱ በጋራም ተያዘ በተናጠል የተጠየቀው ዳኝነት የውርስ አጣሪ ተቋቁሞ ንብረት ለመከፋፈል እስከሆነ ድረስ ይሄው ጥያቄያቸው በሕግ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ካልቀረበ በይርጋ የማይታገድበት ምክንያት አይኖርም ጥያቄው ይርጋ የለውም ማለትም የይርጋን ዓላማ ውጤት አልባ ከማድረግ የተለየ አይሆንም፡፡

ስለሆነም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበለትን የይርጋ መቃወሚያ ሣይቀበለው መቅረቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሣያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1.የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05655 በ10/2/97 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና በ20/11/97 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.91670 በ23/11/89 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪዎች ውርስ ይጣራልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ 33368

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሻምበል አሰፋ በላይ ዘገየ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ወታደራዊ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ክርክርን ይሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በ1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መ/ሕ በቁ. 386 እና 642 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ስለፈጸመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት ይገባል በማለት ነው፡፡ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤቱም አመልካችን አስቀርቦ ከአከራከረ በኋላ አመልካች በተጠቀሱበት የሕግ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች ለስመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጫለሁ የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመቀጠልም በአመልካች ላይ የስድስት (6) ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም

ክርክሩ የተሰማ ሲሆን በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው ቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 30 ቀን 99 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች ተፈጽሞአል የተባለው ወንጀል በወታደራዊ ፍ/ቤት የስረ - ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ለጉዳዮ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ሰበር ችሎት አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ጭብጥ በአመልካች ላይ የተመሠረተው ክስ በወታደደራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ ጉዳዮ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት ስልጣን ምንጭ (በአጠቃላይ) ምንድነው? አንድ ፍ/ቤት ከስልጣኑ ውጪ ጉዳይ ተቀብሎ ዳኝቷል ማለት ምን ማለት ነው? የዳኘው ከስልጣኑ ውጪ ሆኖ ከተገኘስ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚያስነሳ በመሆኑ በጥንቃቄ ለመመርመር የሚባው ነው፡፡

እንደሚታወቀው ፍ/ቤቶች በሕግ የሚቋቋሙ እንደመሆናቸው የዳኝነት ስልጣናቸው የሚመነጨውም ከሕግ ነው፡፡ ከዚህ እንግደህ መገንዘብ የሚቻለው የማንኛውም ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን በሕግ ተወስኖ የተሰጠ (የሚሰጥ) መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ (ክስ) ተቀብሎ ከማስተናገዱ በፊት በጉዳዮ (ክሱ) ላይ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የሚሰጥ ውሳኔ ይሕግ መሠረት ያለው

ነው ወይም ሕጋዊ ውሳኔ ነው ለማለት እንደማይቻልም በአግባቡ መገንዘቡ ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወታደራዊ ፍ/ቤቶች እንደ ሌሎቹ ፍ/ቤቶች በሕግ የተቋቋሙ እና የዳኝነት ስልጣናቸውም በሕግ ተወስኖ የተሰጠ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ.27/1988 በአንቀጽ 25 እንደተመለከተው ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ተቋሙመዋል ለፍ/ቤቶቹ የተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 26፣27 እና 28 በዝርዝር ተገልጿአል፡፡ በ1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መሕግ ከቁ.296 እስከ ቁ.331 በተዘረዘሩት ወንጀሎች ተጠያቂ የሚሆኑ ሰዎች ላይ በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር በሚፈጽማቸው በማናቸውም ወንጀሎች ላይ በውጪ አገር በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ካለ ወታር ጋር አብረው በሚዘምቱ ሲቪሎች ላይ እና በጦር ምርኮኞች ላይ ከተፈፀመ ወንጀል ላይ የወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው አንቀጽ 26 በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተከሣሹ ከቀረቡበት ክሶች መካከል አንዱ በወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል በሆነ ጊዜ ሁሉም ክሶት የሚቀርቡት ለወታደራዊ ፍ/ቤቶች እንደሆነ በአንቀጽ 28/ተመልክቶአል፡፡

በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ስንመለከት ፍ/ቤቶቹ በዚህ ጉዳይ አመልካች በተከሰሰበት የዳኝነት ስልጣን የላቸውም ለሚለው ክርክሩ በዋቢነት የጠቀሰው ከላይ በተመለከተው አንቀጽ 26/1/ የተቀመጠው ድንጋጌ ነው፡፡ በእርግጥም ይህ ንዑስ አንቀጽ ለብቻው ተወስዶ ሲታይ በወ/መ/ሕጉ ከቁ.296 እስከ ቁ.331 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎች ብቻ ስለሚጠቅስ በአመልካች ላይ በቀረበው ክስ የተጠቀሱትን ቁ.386 እና ቁ. 642 አያካትትም፡፡ ከዚህ የተነሣም የአመልካቹ ክርክር ተገቢነት ያለው ነው ሊባይ ይችላል፡፡ በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3) እና (4) የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ስንመለከት ግን

ለወታደራዊ ፍ/ቤቶች የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በንዑስ አንቀጽ /1/ ከተመለከተው የሰፋ እንደሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ በንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከተውን ድንጋጌ እንኳን ወስደን ስናየው በንዑስ አንቀጽ /1/ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በግዳጅ ላይ ያለ ወታር በሚፈጽማቸው በማናቸውም ወንጀሎች ላይ ጭምር ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ነው የምንገነዘበው፡፡ የአመልካቹ ክርክር በጽሑፍ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል ብሎ መደምደሚያ የማይቻለውም (ትክክል የማይሆነውም) በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ‹‹ ግዳጅ›› የሚለው ቃል በአዋጁ ባለመተርጐሙ እና አመልካችም የተከሰሰው ከፋይናንስ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ወንጀል በመሆኑ አመልካቹ በአዋጁ አንቀጽ 26 (2) አባባል በግዳጅ ላይ እንዳለ በፈጸመው ወንጀል ነው የተከሰሰው ወይም የተከሰሱበት ወንጀል የተፈጸመው በግዳጅ ላይ ሳለ ለማለትም ይቻላል ወይ የሚለው ነጥብ አከራካሪ ይሆናል፡፡

የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ.27/88 በመከላከያ ሠራዊት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ.343/95 ተሻሽሎአል፡፡ ይህ አዋጅ በግልጽ ካሻሻላቸው አንቀጾች መካከል የቃላትን ትርጓሜ በተመለተ የተደነገገ ነው አንቀጽ 2 እና የወታራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚመለከተው አንቀጽ 26 ይገኛሉ፡፡ በዚህም በቀድሞው በትርጓሜ ውስጥ ተካቶ ያልነበረው ‹‹ግዳጅ›› የሚለው ቃል ‹‹ማንኛውም የሠራዊት አባል ከተቀጠረበት ጊዜ አንስቶ ከሠራዊቱ እስኪሰናበት ጊዜ ድረስ በመከላከያ ውስጥ የሚያከናውነው የውትድርና ተግባር ነው›› በሚል በማሻሻያው አዋጁ ቁ.343/95 አንቀጽ 2(9) ተተርጐሞአል፡፡ አንቀጽ 26(2)ም በትርጓሜ ክፍሉ በተተረጐመው ‹‹ግዳጅ›› ከሚለው ቃል በሚስማማ መልኩ ተሻሽሎአል፡፡ በዚህም የወታራዊ ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን ከቀድሞው የበለጠ ሰፍቶአል፡፡ አዋጅ ቁ.27/88‹ን› ማሻሻል ካስፈለገበት ምክንያቶች አንዱም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ በወታደርነት በማገልገል ላይ ያለ የሠራዊቱ አባል የሚፈጽማቸው

ወንጀሎች በወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር እንዲወድቁ በመታሰቡ እንደሆነ ከአዋጁ ማሻሻያ አዋጅ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል ፈጸመ በተባለበት ጊዜ ሠራዊቱ አባል (ወታደር) ሆኖ ይሠራ እንደነበረ ተረጋግጦአል፡፡ ይህም ማለት በማሻሻያው አዋጅ ቁ.343/95 አንቀጽ 2(9) እንደተደነገገው በግዳጅ ላይ ነበር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ፈጸመው የተባለው የወንጀል ድርጊት በአዋጁ አንቀጽ 26/1/ በተመለከቱት የወ/መ/ሕጉ ድንጋጌዎች ስር የማይወድቅ ቢሆንም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ተቀጥሮ (በውትድርና) የሚያከናውነውን የውትድርና ተግባር ሲሰራ በነበረበት ጊዜ የፈጸመው በመሆኑ ክሱ ለወታደራዊ ፍ/ቤት መቅረቡ ትክክል ነው፡፡ ሲጠቃለል የወታደራዊ ፍ/ቤቶች ይህን ክስ ለማስተናገድ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት ይግባኝ ሰሚ ወታራዊ ፍ/ቤት የመቁ.014/99 መጋቢት 18 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ክሱ ለወታደራዊ ፍ/ቤት መቅረቡ በሕጉ መሠረት ሆኖ ስላገኘነው የአመልካችን ክርክር አልተቀበልንም፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰበር መ/ቁ 33369

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ሻለቃ መሐመድ ሐሰን - ጠበቃ ፍፁምብርሃን ገ/ክርስቶስ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወታደራዊ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው 1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መ/ሕግ ቁ.387(1)(ሀ) እና (ሐ) 414፣642 እና 664 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ስለፈጸመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት ይገባል በማለት ነው፡፡ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤቱም አመልካችን አስቀርቦ ከአከራከረ በኋላ አመልካች በተጠቀሱበት የሕግ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች ስለመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጫለሁ እሚል መደምደሚያ በላይ ደርሶአል፡፡ በመቀጠልም በአመልካች ላይ የ10(አስር) ዓመት ጽኑ እሥራት እና የብር 5,000 መቀጮ ወስአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሕግ/ቁ.642

መሠረት የቀረበውን ክስ ብቻ በመሠረዝ በሌሎቹ አመልካቾች ጥፋተኛ ነው ብሎአል። በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት የተሰጠው የቅጣት ውሳኔም እንዳለ በማጽናት ወሰኖአል የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው።

እኛም አመልካች ሐምሌ 30 ቀን 99 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች ተፈጽሞአል የተባለው ወንጀል በወታደራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ አለመሆኑ ለመመርመር ነው። በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ለጉዳዮ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል።

እንደምንመለከተው በዚህ ሰበር ችሎት አከራካሪ ሆኖ የቀረበው ጭብጥ በአመልካች ላይ የቀረበው ክስ በወታራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ወይስ አይዳለም? የሚለው ነው። ጉዳዮ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት ስልጣን ምንጭ (በአጠቃላይ) ምንድነው? አንድ ፍ/ቤት ከስልጣኑ ውጭ ጉዳይ ተቀብሎ ዳኝቶአል ማለት ምን ማለት ነው? የዳኘው ከስልጣኑ ውጪ ነው ከተባለስ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚያስነሳ በመሆኑ በጥንቃቄ ሊመረመር የሚገባው ነው።

እንደሚታወቀው ፍ/ቤቶች በሕግ የሚቋቋሙ እንደመሆናቸው የዳኝነት ስልጣናቸው የሚመነጨውም ከሕግ ነው። ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻልው የማንኛውም ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን በሕግ ተወስኖ የተሰጠ መሆኑን ነው። በመሆኑም ማንኛውም ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉደይ (ክስ) ተቀብሎ ከማስተናገዱ በፊት በጉዳዮ (ክሱ) ላይ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት ።

በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይም ሕጋዊ ውሳኔ ነው ለማለት እንደማይችልም በአግባቡ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወታደራዊ ፍርድ ቤቶች እንደ ሌሎቹ ፍ/ቤቶች በሕግ የተቋቋሙ እና የዳኝነት ስልጣናቸውም በሕግ ተወስኖ የተሰጠ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ.27/1988 በአንቀጽ 25 እንደተመለከተው ቀዳማዊ ወታደራዊ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ተቋቁመዋል፡፡ ለፍርድ ቤቶቹ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን በተመለተም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 26፣ 27 እና 28 በዝርዝር ተገልጾአል፡፡ በ1949 ዓ.ም በወጣው የወ/መ/ሕግ ከቁ.296 እስከ ቁ.331 በተዘረዘሩት ወንጀሎች ተጠያቂ በሚሆኑ ሰዎች ላይ በግዳጅ ላይ ያለ ወታደራዊ በሚፈጽማቸው በማናቸውም ወንጀሎች ላይ በውጪ አገር በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ካለ ወታር ጋር አብረው በሚዘምቱ በሲቪሎች ላይ እና በጦር ምርኮኞች ላይ ከተፈጸመ ወግጀል ላይ የወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው አንቀጽ 26 በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተከሣሹ ከቀረቡበት ክሶች መካከል አንዱ በወታደራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል በሆነ ጊዜ ሁሉ ክሶች የሚቀርቡት ለወታደራዊ ፍ/ቤት እንደሆነ በአንቀጽ 28 ተመልክቷአል፡፡

በአመልካች በኩል የቀረበው ክርክር ስንመለከት ፍ/ቤቶቹ በዚህ ጉዳይ (በአመልካቹ በተከሰሰበት) የዳኝነት ስልጣን የላቸውም የሚለውን ክርክሩ በዋቢነት የጠቀሰው ከላይ በተመለከተው አንቀጽ 26(1) የተቀመጠው ድንጋጌ ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ንዑስ አንቀጽ ለብቻው ተወስዶ ሲታይ በወ/መ/ሕጉ ከቁ.296 እስከ ቁ331 ድረስ ያሉትን ድንጋጌዎች ብቻ ስለሚጠቅስ በአመልካች ላይ በቀረበው ክስ የተጠቀሱትን የወ/መ/ ሕ/ቁ/.387፣414፣642 እና 664 ‹ን› አያካትትም፡፡ ከዚህ የተነሣም የአመልካቹ ክርክር ተገቢነት ያለው ነው ሊባይ ይችላል፡፡ በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3) እና (4)

የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ስንመለከት ግን ለወታራዊ ፍ/ቤቶቹ የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት የሰፋ እንደሆነ ነው የምንገነዘበው፡፡ በንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን ድንጋጌ እንኳን ወስደን ስናየው በንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በግዳጅ ላይ ያለ ወታር የሚፈጽማቸው በማናቸውም ወንጀል ላይ ጭምር ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ነው የምንገነዘበው፡፡ የአመልካቹ ክርክር በድፍኑ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል ብሎ መደምደም የማይቻለውም (ትክክል የማይሆነውም) በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ‹‹በግዳጅ›› የሚለው ቃል በአዋጁ ባለመተርጐሙ እና አመልካችም የተከሰሰው 107ኛ ኮር ተብሎ በተሰየመው መምሪያ የኮሩ የፋይናንስ ሃላፊ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ጊዜ በፈጸመው ወንጀል በመሆኑ አመልካች በንዑስ አንቀጽ (2) አባባል በግዳጅ ላይ እንዳለ በፈጸመው ወንጀል ነው የተከሰሰው ወይም የተከሰሰበትን ወንጀል የፈጸመው በግዳጅ ላይ ሳለ ነው፡፡ ለማለት ይቻላል ወይ የሚለው ነጥብ አከራካሪ ይሆናል፡፡

የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁ.27/88 በመከላከያ ሠራዊት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁ.343/95 ተሻሽሎአል፡፡ ይህ አዋጅ በግልጽ ካሻሻለው አንቀጾች መካከል የቃላትን ትርጓሜ በተመለከተ የተደነገገው አንቀጽ 2 እና የወታራዊ ፍረድ ቤቶችን የዳኝነት ስልጣን የሚመለከተው አንቀጽ 26 ይገኛሉ፡፡ በዚህም በቀድሞው አዋጅ በትርጓሜ ውስጥ ተካቶ ያልነበረው ‹‹ግዳጅ የሚለው ቃል›› ማንኛውም የሠራዊት አባል ከተቀጠረበለት ጊዜ አንስቶ ከሠራዊት እስከሚሰናበትበት ጊዜ ድረስ በመከላከያ ውስጥ የሚያከናወነው የውትድርና ተግባር ነው ‹‹በሚል በማሻሻያው አዋጅ ቁ.›› 343/95 አንቀጽ 2(9) ተተርጕሞአል፡፡ አንቀጽ 26(2)ም በትርጓሜ ክፍሉ ከተተረጐመው ‹‹ግዳጅ›› ከሚለው ቃል በሚስማማ መልኩ ተሻሽሎአል፡፡ በዚህም የወታደራዊ ፍ/ቤቶቹ የዳኝነት ስልጣን ከቀድሞው የበለጠ ሰፍቷል፡፡

አመልካች ወንጀሎቹን ፈጸመ በተባለት ጊዜ የሠራዊት አባል (ወታደር) ሆኖ ይሠራ እንደነበረ ተረጋጋጧአል፡፡ ይህም ማለት በማሻሻያው አዋጅ ቁ.343/95 አንቀጽ 2(9) እንደተደነገገው በግዳጅ ላይ ነበር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ፈጸሟቸው የተባሉት የወንጀል ድርጅቶች በአዋጁ አንቀጽ 26(1) በተመለከቱት የወ/መ/ሕጉ ድንጋጌዎች ሥር የማይወድቁ ቢሆኑም በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ተቀጥሮ (በውትድርና) የሚያከናውነውን የውትድርና ተግባር ሲሰራ በነበረበት ጊዜ የፈጸማቸው በመሆናቸው ክሱ ለወታደራዊ ፍ/ቤት መቅረቡ ትክክል ነው፡፡ ሲጠቃለል/ የታደራዊ ፍ/ቤቶቹ ይህን ክስ ለማስተናገድ በሕግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡ ስለዚህም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት የይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት በመ.ቁ 01599 መጋቢት 18 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ፀንቶአል፡፡
2. ክሱ ለወታራዊ ፍ/ቤት መቅረቡ በሕጉ መሠረት ሆኖ ስላገኘነው የአመልካችን ክርክር አልተቀበልንም፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ